EEA/EEPRI

Ethiopian Economic Association/ Ethiopian Economic Policy Research Institute
Tel. 251-1- 55 74 59, 251-1 12 80 77
Fax No. 251-1 56 52 52
P.O.Box 34282, A.A Ethiopia:
e-mail: eea@telecom.net .et

EEA/EEPRI

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር/
የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ ፖሊሲ ምርምር ተቋም

# የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

## ለድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት ስልጠና የተዘጋጀ

ዶ/ር ወልዳይ አመሀ
መስከረም 1994 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ማውጫ

እርእስት | ገጽ


1. የድህነት ጽንሰ-ሃሣብና መገለጫዎች 2
    1.1. ድህነት ምንድንነው? 2
2. የድህነት ትንተናናች መለኪያዎች 5
    2.1 የገቢ ማነስ የሚገለጽ የድህነት መለኪዎች 7
    2.2 የጤና የትምህርትና ድህነት ማሳያዎች 11
    2.3 ለጥቃት መጋለጥ መመዘኛዎች 14
    2.4 ተደማጭነትና አቅም ማጣት 17
3. የድህነት ወሰል ድንጸ ሃሣብ፣ መለኪያዎች፣ አፈፃፀምና የኢትዮጵያ የድህነት ገጽታ 19
4. በኢትዮጵያ በከተማና በገጠር የተንሰራፋው ድህነት ዋና ዋና መለያዎች 29
5. ድህነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ መነሻዎችና የአፈፃፀም ስልቶች 39
    5.1 የድህነት መንስኤዎች 39
    5.2 በኢትዮጵያ ድህነትን የሚወስኑ ጉዳዮች 42
    5.3 ድህነትን መታገል 46
        5.3.1 እድገትና የስራ እድል ማስፋት 47
        5.3.2 ድህነት አጠቃላይ ፓሊሲዎች 51
        5.3.4 መረጋጋትና ዋስትና ማግኘት 53
        5.3.5 እለም አቀፍ ተግባራት 56
6. ድህነትን ለመቀነስ ለሚነደፉ ፓሊሲዎች ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ ስልቶች
    6.1 ድሃውን መለየት 57
        6.1.1 አጠቃላይና ዝርዝር የመለየት ስራ 58
        6.1.2 ደህነትን የመለየት አማራጭ መንገዶች 60
        6.1.3 በዝርዝር የመለየት ተግባር የሚያጋጥሙ ችግሮች 62
    6.2 የባለጉዳዮች ተሳትፎ 67
    6.3 ያልተማከለ የስልጣን ክፍፍል 74
        6.3.1 ድንስ ሃሣብና ያልተማከለ የስልጣን ክፍፍል 75
        6.3.2 ያልተማከለ የስልጣን ክፍፍል በኢትዮጵያ 77
    6.4 ተሳትፎሃዊ የሆነ ክትትልና ግምገማ 80
        6.4.1 ክትትል 83
        6.4.2 የግምገማ ተግባራት 84
Reference 101

# የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

ድህነት እንዴት ይገለፃል?

- አንድ ወጥ ትርጉም የለውም
- አንፃራዊ ወይም ፍፁም የሆኑ አገላለጾች
- ድህነት በርካታ መገለጫዎች አሉት
    - የጥሪት እጦት
    - ዋስትና ማጣትና ለጥቃት መጋለጥ
    - አቅም ማጣትና የበታችነት ስሜት
    - ሌሎች ጉዳዮች

በአጠቃላይ መልኩ ድህነት በሚከተሉት መንገዶች ሊገለፅ ይችላል።

- ገቢ ማጣት
- ዋስትና ማጣት
- ትምህርት አለማግኘት
- የጤና አገልግሎት አለማግኘት

# 1. የድህነት ፅንሰ ሃሣብና መገለጫዎች

## 1.1 ድህነት ምንድንነው?

የድህነት ትርጉም በማስቀመጥ ላይ አጠቃላይ የሆነ መግባባት የለም። የጀርመን ፌደራል መንግስት የልማት ፖሊሲ ዘጠነኛው ሪፓርት /ሽብርት 1994 e.c/ እንደሚያመለክተው ከሆነ በድህነት የተጠቁ ሰዎች ማለት በማንኛውም መለኪያ ደህና ህይወት መምራት የማይችሉ ማለት ነው። በዚህ አገላለፅ ድህነት ማለት ጤናማ ህይወት መነፈግ ማለት ነው። ይህ ትርጓሜ አጠቃላይና በአብዛኞቹ ዘንድ ተቀባይነት የማግኘት እድሉ የሰፋ ቢሆንም እንደ አገሩ ባህል፣ ማህበራዊ ሁኔታ ትርጉሙ ይለያያል። በሌላ በኩል ድህነት በቂ ምግብ ያለማግኘት፣ አጭር የህይወት ዘመን፣ ከፍተኛ የህፃናት ሞት፣ ዝቅተኛ የመማር እድል፣ ንፁህ የመጠጥ ውሃ ያለማግኘት፣ በቂ የህክምና አገልግሎት ማጣት፣ የመጠለያ ችግር እንዲሁም በአገር አቀፋዊም ሆነ በአካባቢ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍና የመወሰን እድል ማጣት ጋር ተያይዞ ይታያል።

በማንኛውም ህብረተሰብ ዝቅተኛ ኑሮ መምራት የማይችሉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ሰዎች ካሉ ድህነት አለ ይባላል። (Ravallion 1992) ድህነት ማለት መራብ ነው። ድሃ ማለት የጤና አገልግሎት መጠለያና ልብስ ማጣት ማለት ነው። ድሃ መሆን በገንዘብ የሚተመን ብቻ ሳይሆን የትምህርት እድል ማጣትም ነው። ሆኖም በድህነት የሚኖሩ ሰዎች ህይወት ከዚህ በላይ የከፋ ነው። ምንጊዜም ቢሆን ድሃ ህዝቦች ከቁጥጥራቸው ውጭ ለሆኑ ክስተቶችና ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ ድሆች በህዝባዊና ባመንግስት ተቋማት የተገፉ፣ ዘንድ ተደማጭነትና አቅም የሌላቸው ናቸው። ገቢያቸውንና ፍጆታቸውን በመመርመር ከምንገነዘበው የቁሳዊ ህይወታቸው ጉስቁልና ባሻገር የድሃ ህዝቦች ችግር በትምህርት ውጤታችው ደካማ መሆን በጤና አገልግሎት ማጣትም ይገለፃል። በአጠቃላይ ድህነት ማለት ተደማጭነትና አቅም ማጣት ብቻ ሳይሆን ለሰቆቃ ህይወት መጋለጥ ማለት ነው።

ድህነት በአንድ በኩል መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል ገቢ ለመፍጠር እድል ማጣት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የመገለልና የመሠረታዊ መብቶች መነፈግ ውጤት ተደርጎ ይወሰዳል። በአጠቃላይ ድህነት የግለሰብም ሆነ የቡድን ክብርን በሚያሳጣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ውስጥ ይዘፍቃል። የድህነት ምክንያትና ውጤት የሆነው መገለል፣ የባህል እሴቶችን በማናጋት ግለሰባዊ ማንነት በማሳጣት በከፋ መልኩ የሚገለፀውም በድህነት ውስጥ ነው። ቀደም ብሎ ለመግለፅ እንደተሞከረው ድህነት በሰው ልጅ ላይ የሚያስከትለውን መገለልና ችግሩ በተለየዩ የህይወት ዘርፎች እንዴት እንደሚገለጽ የሚያሣይ አንድ ወጥ መመዘኛ የለም። በምእራብ አውሮፓ በሚገኙ አንዳንድ አገሮች ከተወሰነ ጣሪያ በታች ዝቅተኛ

ገቢ ላለው ሰው ድጉማ የሚሰጡበት ማህበራዊ ዋስትና (Social Security) አላቸው። አንዳንድ ወገኖች ማንኛውም ሰው በቀን ከሚያስፈልገው 2100 የካሎሪ መጠንና ከአንድ የአሜሪካን ዶላር ያነሰ እለታዊ ገቢ የሚያገኝ ከሆነ የድህነት መግለጫ አድርገው ይወስዱታል። የካሎሪ ማነስ የድህነትና የምግብ ዋስትና ማጣት ጠቃሚ መመዘኛ አድርገው የሚጠቀሙት ደግሞ በርካታ ናቸው። ለማንኛውም የድህነት ትርጉም በአንድ አገር ውስጥም ቢሆን የተለያየ መልክ የሚይዝበት ሁኔታ እንዳለ የሚከተሉት መለኪያዎች ያሳያሉ። የተመጣጠነ የምግብ አወሳሰድ መመዘኛ መሰረት ተደርጎ ሲታይ ከገቢያቸው 80% ወይም ከዚያ በላይ ለምግብ አውለው ነገር ግን የሚያገኙት የካሎሪ መጠን ከእድሜያቸው፣ ጾታቸውና አኳያ ጉልበት ለማግኘት ከሚያስፈልጋቸው የካሎሪ መጠን ከ80% ያነሰ የሚያገኙ ከሆነ እነዚህ ሰዎች በረሃብ የተጠቁ ብቻ ሣይሆኑ በከፋ ድህነት ውስጥ የሚገኙ ናቸው። በሌላ በኩል ከገቢያቸው 70% ወይም ከዚያ በላይ ለምግብ አውጥተው ከ80-100% የሚፈለገውን የካሎሪ መጠን የሚያገኙ ሰዎች ረሃብተኞች ባይባሉም እልፎ እልፎ ሊራቡና ድሆች ተብለው ሊፈረጁ ይችላሉ። ድህነት በምግብ እጥረት ብቻ የሚገለፅ ሣይሆን የመጠለያ፣ የልብስና ሌሎች ችግሮችንም ይጨምራል (Lipton 1985) ከዚህ ጋር በማያያዝ በሰፋት ጥቅም ላይ የዋሉ ሁለት የድህነት ትርጉሞችን እንመልከት።

ሀ) ፍፁም ድህነት - የሰዎችን ፍጆታ በመገምገም ለህልውና የሚያስፈልጋቸውን መሰረታዊ ፍላጎት በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን ማሟላት ያለመቻላቸውን ያመለክታል። ይኸውም ከፍጹም ድህነት በታች የሚኖሩ ሰዎች ጉልበት የሚሰጡ በአይነትም ሆነ በመጠን ተመጣጣኝ ምግብ ማግኘት አለመቻላቸውን ያሳያል።

ለ እንፃራዊ ድኅነት- በቤተሰብና በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ያለመመጣጠንን በመመርመር የመገለሉን ደረጃና ዓይነት ያሳያል። እንፃራዊ ድህነት በአንድ አገር ወይም አካባቢ ከ30-40% የሚሆኑ ድሆች የሚገኙበትን የኑሮ ደረጃ የሚገልጽ ነው። በዚህ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉት ከህብረተሰቡ አንፃር ሲታይ ድሆች ተብለው ይፈረጃሉ። ከሌላ አገር ወይም አካባቢ ጋር ሲወዳደሩ ድሆች ተብለው ላይፈረጁ ይችላሉ።

## ድህነትን እንዴት እንለካለን?

በገቢ ማነስ የሚገለፅ የድህነት መለኪያዎች

- የነፍስ ወከፍ ገቢ
- የነፍስ ወከፍ የምግብ ወጪ
- የነፍስ ወከፍ የካሎሪ ፍጆታ
- የድህነትን ወለል መገመት

የጤናና የትምህርት ሽፋን መለኪያዎች

- የህፃናት ሞት
- የጤናና የትምህርት አገልግሎት ሽፋን
  - ወንድ
  - ሴት
  - ገጠር
  - ከተማ
- የማንበብና መፃፍ ደረጃ

ከቁጥጥር ውጭ ለሆኑ አደጋና ለጥቃት መጋለጥን የሚያሳዩ መለኪያዎች /ጠቋሚ/

- ተሸጦ በፍጥነት ወደ ገንዘብ ሊቀየር የሚችል ጥሪት ፣
- የገቢ ምንጭ ደረጃና ስፋት
- የማህበራዊ ዋስትና (ሴፍቲኔት) መኖር ፣

## 2. ድህነት ትንተናና መለኪያዎቹ

ድህነትን መተንተንና መለካት የድህነትን መንስኤ ምክንያቶችና የመፍትሄ ሀሳቦችን ለማዳበርና በአንድ ወቅት ያለውን የድህነት ሁኔታ በመረዳት የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖር ያደርጋል። ይህ ግንዛቤ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋሞች ድህነትን ለማስወገድ ምን ዓይነት ጥረት ማድረግ እንደሚገባቸው ለማመላከት ይረዳል። ድህነትን የሚመለከት ፖሊሲ ለመንደፍ የድህነትን ምንነትና ገፅታውን ለመረዳት የሚጠቅሙ መመዘኛዎችን በጥንቃቄ መምረጥ ያስፈልጋል። ምክንያቱም መለኪያዎቹ ራሳቸው የሚቀመጠው ግብ ምንጮች ናቸውና! የድህነት ትንተና የሚከተሉት ሶስት አላማዎች አሉት (Lipton and Rarallion, 1995)።

ሀ) የድህነትን ትርጉምና ገፅታ ለማሳየት ፤

ለ) የድህነትን መንስዔዎች ለመግለጽና ለማብራራት፣

ሐ) ተገቢ የፖሊሲ እርምጃዎችን ለመውሰድ ፤

ቀደም ሲል ድህነትን ለመግለፅም ሆነ ደረጃውን ለመለካት ያስችላሉ የሚባሉ የተለያዩ መንገዶች ተጠቁመዋል። ድህነት በማንኛውም ደረጃ በህፃናት ፤ በቤተሰብ ፤ በማህበረሰብ፣ በክልል ወይም በአገር ሊገለፅና ስፋትና ጥልቀቱም ሊለካ ይቻላል። (Bambereger m, 1996) ለዚህ ተግባር ከሚጠቅሙት መለኪያዎች ውስጥ የሚከተሉት ነጥቦች ሊጠቀሱ ይችላሉ።

- በገቅተኛ ኑሮ የሚገኙ ድሆች ለመኖር የሚያስችላቸውን የምግብ አይነትና መጠን ለመግዛት የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ መጠን ወይም የአገራቱን ገቢ ለዜጎች ሲከፋፈል የሚኖረውን ድርሻ መሰረት ያደረገ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ማሳያ፣
- የካሎሪ ፍጆታ
- የህፃናት ሞት ወይም የአንድ አገር ህዝብ አማካይ ዕድሜ ፤
- ከአካባቢ ሁኔታ ጋር የሚስማማ የተመጣጠነ ምግብ የማግኘት ሁኔታና እድገት
- የመሰረታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት ፤
- የኑሮ ሁኔታና የበው እድገት የሚያሳዩ ውሁድ መለኪያዎች ፤
- የደመወዝ ስርዓት ፤
- የገጠር ግብይትና፣ ሌሎች ናቸው።

## የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

ድህነትን የመግለፅና የመተንተኑ ተግባር ድህነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ግቦችን ለማስቀመጥና የተጠቃሚዎችን ማንነት ለመለየት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በሌላ በኩል ለዚህ ተግባር የምንጠቀምባቸው መለኪያዎች ለምን እንደመረጥናቸውና የመለኪያዎቹ አፈፃፀም ለመመርመር ይረዳል።

ድህነትን ለመለካት በተናጠል የሚደረጉት ጥረቶች በድህነት ላይ የተሻለ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚረዱ በመሆናቸው ቀልብ እየሳቡ ይገኛሉ። የድህነትን ምንነትና ደረጃ ለመገንዘብ የምንጠቀምባቸው መመዘኛዎች መንግስታትና የዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ሊለኩ ወይም ሊመዘኑ የሚችሉ ግልፅ ግቦችን አስቀምጠው አፈፃፀማቸውንና ውጤታቸውን መገምገም ያስችላቸዋል።

የአንድ አገር አጠቃላይ ምርትና የነፍስ ወከፍ ድርሻ የአንድን አገር ብልፅግና በተገቢው መንገድ የሚያሳይ መለኪያ እንዳልሆነ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ጉዳይ ነው። ጤናማ ኑሮን ወይም ህይወትን ለመለካት ከሚረዱት መመዘኛዎች ውስጥ የቤተሰብ የነፍስ ወከፍ ገቢ ፣ የነፍስ ወከፍ አጠቃላይ ወጪ ፣ የነፍስ ወከፍ የምግብ ወጪ ፣ የነፍስ ወከፍ የካሎሪ ፍጆታና አንድ ቤተሰብ ከሚያወጣው አጠቃላይ ወጪ ለምግብ የሚያወጣው ወጪ ያለውን ድርሻ የሚያሳዩ መመዘኛዎች አንዳንዶቹ ናቸው። እስከካሁን ድረስ በተደጋጋሚ እንደተገለፀው ድህነት በርካታ መገለጫዎች ያሉት እንደመሆኑ በአንድ መመዘኛ ብቻ የድሃውን ህዝብ ህይወት መግለፅ አይቻልም። የድህነትን መገለጫዎች በአንድ መመዘኛ ብቻ ለመመርመር መሞከር አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም የድህነት መገለጫ ተደርጎ የሚወሰደው አንዱ ገፅታ በተመሳሳይ ወቅት ከሌሎች መገለጫዎች በተለየ ሁኔታ ሊከሰት ወይም ሊታይ ስለሚችል ነው። ለምሳሌ የጤና ሁኔታ ሲሻሻል ገቢ በከፋ ሁኔታ ሊያሽቆለቁል ይችላል ወይም ደግሞ አንድ ግለሰብ የጤንነት ችግር ሳይኖረው ምንም አይነት የገቢ ምንጭ ላይኖረው ይችላል። ከዚህ አንፃር የድህነትን የተሟላ ስዕል ሊያሳዩ የሚችሉ የተለያዩ መለኪያዎችን አዋህደው የያዙ መመዘኛዎች ለመጠቀም የሚያስችሉ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። ከነዚህም ውስጥ አንዱ የኑሮ ገፅታን ሊያሳይ የሚችለውን የማንበብና መፃፍ ሁኔታን የህፃናት ሞትንና የአንድ ሰው አማካይ ዕድሜን በማጣመር ከአለም አቀፍ የልማት ድርጅት ከወጣው የሰው ልጅ ዕድገት መመዘኛዎች ጋር በማዋሃድ የሚመዝነው ነው። እነዚህ መመዘኛዎች ለአጠቃቀም ምቹ ይሁኑ እንጂ ፣ እያንዳንዱን የድህነት መገለጫ በተናጠል ከመመዘን ባሻገር በድህነት መገለጫዎች መካከል ያለውን ልዩነትና መስተጋብራዊ ችግር ስለማያሳዩ ችግሩን አያቃልሉትም። ከዚህ አንፃር የተለያዩ መለኪያዎች ለማዘጋጀትና ለመጠቀም ሙከራ የተደረገ ቢሆንም ሁሉም የራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን አላቸው። ለማንኛውም ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚታወቁትን አራት ዋነኛ መለኪያዎች እንመርምር።

## 2.1 በገቢ ማነስ የሚገለፅ የድህነት መለኪያዎች

የገንዘብ የገቢ መጠን ወይም ፍጆታን እንደመመዘኛ በመውሰድ ድህነትን መግለፅና መለካት ለረጅም ጊዜ ሲሰራበት የቆየ ነው። የአንድ ቤተሰብ ገቢና ወጪን በማጥናት የድህነትን ሁኔታ በመጠን መተንተንም ሆነ የፖሊሲ መነሻ ማድረግ በእጅጉ የተለመደ ነው። ሆኖም ይህ መመዘኛ በብዛት ተጠቃሚዎች ቢኖሩትም ይህን የገቢ ድህነት ለመለካት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን አሰባሰብ ላይ ችግሮች ይኖራሉ። ለምሳሌ ናሙናዎች አመራረጥ ላይና በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያለውን የገቢ ያለመመጣጠንና ሌሎች ሁኔታዎችን በማሳየት ረገድ እጥረት አለበት።

በገቢ ወይም በፍጆታ የሚታየውን ድህነት ለመረዳት ጠቃሚ ከሆኑት መለኪያዎች አንዱ የድህነት ወለል ነው። የድህነትን ወለል በማስቀመጥ ረገድ አንድ ወጥ መለኪያ የለም። ለዚህ ችግር እንደመፍትሄ ሊረዱ የሚችሉ ሁለት አማራጮች አሉ። አንደኛው አማራጭ በሁሉም አገሮች ተቀባይነት ያለውን አንድ ሰው የሚያስፈልገውን ፍጆታ ለመግዛት የሚያስችል አንድ የአሜሪካ ዶላር በቀን ማግኘት መቻሉ ነው በአንድ ህብረተሰብ ከተቀመጠ የተወሰነ ደረጃ በታች ገቢ የሚያገኙ ወይም ያነሰ ፍጆታ ያላቸው ሰዎች ምን ያህሉ እንደሆኑ ማወቅ የድህነት ወለል ደረጃን ያሳያል። ይህ ስልት የተለያዩ አገሮችን የምንዛሬ መጠን በዶላር ሲሰላ ለስህተት የሚዳርግ ቢሆንም በአገሮች መካከል ያለውን የድህነት ሁኔታ የማሳየት አቅም አለው። ሌላው አማራጭ በየአገሩ ከተቀመጠው የድህነት ወለል (አንፃራዊ የድህነት ወለል) በታች የሚኖሩትን ድሆች መለየት ነው። ይህ መመዘኛ እንደየአገሩ የእድገት ሁኔታ የሚኖረውን የድህነት ወለል ልዩነት ሊያሳይ ይችላል። ቢሆንም በአገሮች መካከል ያለውን ልዩነት የማነፃፀሩን ሂደት አስቸጋሪ ያደርገዋል።

ምንጊዜም ቢሆን በየቤቱ በሚኖሩ የተለያዩ ሁኔታዎች ምክንያት የአንድን ቤተሰብ ትክክለኛውን የድህነት ወለል መግለፅ አስቸጋሪ ነው። ስለዚህም የአንድ ቤተሰብ የድህነት ወለል ለቤተሰቡ ልዩ ሁኔታ ተገዥ ይሆናል። የአንድን ቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ የሚወስኑ የተለያዩ ጉዳዮች ግምት ውስጥ ሲገቡ የአንድ ቤተሰብ የድህነት ወለል አንድ ወጥ በሆነ መገለጫ ማስቀመጥ አይቻልም። በዚህም ምክንያት አንድ ቤተሰብ በተወሰኑ የኑሮ መመዘኛዎች በድህነት ላይ ያለ ተደርጎ ሲወሰድ በሌሎች መለኪያዎች ደግሞ ደሃ እንዳልሆነ ተደርጎ የሚወሰድበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል።ምንጊዜም የድህነትን ሁኔታ ለማወቅ ሲፈለግ የድህነቱን ስርጭትና ጥልቀት ሊያሳይ የሚችል እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ነው። የድህነት

## የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

ወለልን ለማወቅ የሚካሄድ ጥናት በድሆች መካከል ያለውን ልዩነት ማሳየት ይኖርበታል። ይህም ማለት አንዳንዶቹ ከድህነት ወለድ ቀረብ ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ ቀሪዎቹ ደግሞ ከዚህ በከፋ ሁኔታ ከድህነት ወለሉ በጣም ርቀው ሊገኙ ይችላሉ። ስለማያሳይ ችግር አለበት። በድህነት ውስጥ ያለውን ልዩነት የሚያመለክተው መመዘኛ ከደህነት ወለል በታች የሚኖሩ ዜጎች ፍጆታ ፣ የድህነቱ ስርጭትና ክብደቱን ግምት ውስጥ በማስገባት ይገመግማል። (ዝርዝር የድህነት ወለል ጉዳዮች በምዕራፍ ሶስት እናያቸዋለን)።

ለአንድ ሰው በቀን አንድ የአሜሪካን ዶላር ያስፈልጋል የሚለውን የፍፁም ድህነት መለኪያ መሰረት በማድረግ የአፍሪካን ሁኔታ ብንመለከት ግማሽ ያህሉ አፍሪካዊ ከዚህ በታች እንደሚኖርና ቁጥሩም ከቀን ወደ ቀን በፍጥነት እያደገ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን። አንፃራዊ የድህነት ወለል መሰረት በማድረግ ሲታይም በሌሎችም አገሮችም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳለ እናያለን። በ1990 ዎቹ በ21 አገሮች የተደረገው ጥናት ከገጠር ነዋሪ ከግማሽ በላይ የሚሆነው በየአገሩ ካለው የድህነት ወለል በታች እንደሚኖር አሳይቷል። በፈረንጆቹ አቆጣጠር የአለም ባንክ የ2000 ሪፖርት ጥናት በናይጀሪያና በዚምባቢዌ የድሆች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን ያመለክታል። በኢትዮጵያ ሞሪታኒያና ኡጋንዳ በተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች የድሆች ሁኔታ መሻሻሉን ያሳያል።

ዝቅ ብሎ የቀረበው ሰንጠረዥ ቁጥር 1 በ1995/96 በየቤቱ የተካሄደው የኑሮ ሁኔታ ጥናት መሠረት በማድረግ በኢትዮጵያ ያለውን የፍፁም ድህነት ሁኔታ ያሳያል። የጥናቱ ውጤት ከኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ 45.5% ያህሉ ዝቅተኛውን የኑሮ ደረጃ እንኳን መኖር የማይችልና ከድህነት ወለል በታች እንደሚገኝ ያመለክታል በዚህ መሰረት ከገጠሩ ህዝብ 47.5% ከከተማው ነዋሪ 33.2% ከድህነት ወለል በታች እንደሚኖሩ ያሳያል። በድህነት መካከል ያለውን ልዩነት የሚያሳየው መመዘኛ በድሆቹ መካከል የ13% ልዩነት እንዳለና 13% የሚሆኑት ድሆች ለኑሮ የሚያስፈልገውን በጣም አነስተኛ ፍጆታ የማግኘት ችግር እንዳለባቸው ያሳያል። በድሆች መካከል ያለው ልዩነት ወይም የድህነት ክብደትም ከከተማው ይልቅ በገጠሩ የከፋ እንደሆነ ያመለክታል። የድህነቱ ቀንበር በከፋ መልኩ የሚገለፀውም እንደዚሁ ከከተማው ይልቅ በገጠር ነው። የድህነት ወለል ዝርዝር ጉዳዮችን በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከታለን።

**ሰንጠረዥ 1 ፦ ፍፁም ድህነት በኢትዮጵያ** (1995/1996)

| | % ከአጠቃላይ ህዝብ | የድህነት ወሰል | የድህነት ጥልቀት | የድህነት እስከፊነት (ክብደት) |
|---|---|---|---|---|
| **ገጠር** | 86.0 | 47.5 | 0.13 | 0.05 |
| **ከተማ** | 14.0 | 33.2 | 0.10 | 0.04 |
| **በአገር ደረጃ** | 100.0 | 45.5 | 0.13 | 0.05 |

የተለያዩ መረጃዎችን ስንመለከት በኢትዮጵያ ያለው አንፃራዊ ድህነት ከ31% እስከ 45.5% ባለው ውስጥ ይዋኝ ቃል። ድህነት ከከተማው ይልቅ በገጠሩ እየተስፋፋ መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶችም አሉ። ከክልሎች አንፃር ሲታይ ለድርቅና ለተለያዩ ችግሮች በተጋለጡት በትግራይና በአማራ እንዲሁም ብዙ ህዝብ በሚገኝባቸው የደቡብ ክልል አካባቢዎች የድሆች ቁጥር በዝቶ ይታያል።

ሰንጠረዥ 2 ፦ የማንበብና መፃፍ ሁኔታ በኢትዮጵያ(1996,1998,2000)

| ሪፖርት | ፆታ | የመኖሪያ ስፍራና ጥናቱ የተካሄደበት አመት | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አጠቃላይ | | | ገጠር | | | ከተማ | | |
| | | 1996 | 1998 | 2000 | 1996 | 1998 | 2000 | 1996 | 1998 | 2000 |
| አገር | ወ | 34.8 | 36.4 | 39.7 | 27.9 | 28.8 | 32.8 | 77.5 | 81.0 | 81.8 |
| | ሴ | 16.9 | 17.2 | 19.4 | 8.4 | 8.8 | 11.0 | 56.7 | 59.0 | 60.6 |
| | ወ+ሴ | 25.8 | 26.6 | 29.2 | 18.8 | 21.7 | 65.7 | 69.0 | 69.9 | |
| ትግራይ | ወ | - | - | 37.8 | 28.2 | 29.5 | 30.6 | - | - | 79.1 |
| | ሴ | - | - | 22.5 | 9.8 | 10.2 | 15.6 | - | - | 52.0 |
| | ወ+ሴ | - | - | 29.3 | 18.8 | 19.7 | 22.5 | - | - | 62.5 |
| አፋር | ወ | - | - | 22.6 | 18.7 | 9.2 | 10.4 | - | - | 74.9 |
| | ሴ | - | - | 13.7 | 6.4 | 2.9 | 2.1 | - | - | 48.1 |
| | ወ+ሴ | - | - | 18.5 | 13.0 | 3 | 6.7 | - | - | 60.5 |
| አማራ | ወ | - | - | 30.9 | 21.2 | 23.9 | 26.0 | - | - | 80.7 |
| | ሴ | - | - | 15.6 | 5.9 | 8.1 | 9.7 | - | - | 57.2 |
| | ወ+ሴ | - | - | 23.1 | 13.7 | 16.1 | 17.9 | - | - | 66.9 |
| ኦሮሚያ | ወ | - | - | 38.4 | 29.5 | 28.9 | 33.6 | - | - | 78.8 |
| | ሴ | - | - | 16.0 | 8.5 | 7.8 | 10.0 | - | - | 58.7 |
| | ወ+ሴ | - | - | 26.9 | 19.2 | 18.3 | 21.6 | - | - | 67.7 |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ወ | - | - | 47.9 | 28.5 | 38.4 | 45.8 | - | - | 73.5 |
| | ሴ | - | - | 16.1 | 6.6 | 9.9 | 12.8 | - | - | 54.8 |
| | ወ+ሴ | - | - | 31.3 | 16.9 | 24.3 | 28.7 | - | - | 63.5 |
| ደቡብ ክልል | ወ | - | - | 43.3 | 35.6 | 35.4 | 40.6 | - | - | 76.2 |
| | ሴ | - | - | 16.5 | 11.2 | 11.0 | 13.0 | - | - | 56.4 |
| | ወ+ሴ | - | - | 29.6 | 23.3 | 23.0 | 26.5 | - | - | 65.8 |
| ጋምቤላ | ወ | - | - | 62.4 | 44.6 | 45.7 | 57.2 | - | - | 80.5 |
| | ሴ | - | - | 30.8 | 18.5 | 17.5 | 22.7 | - | - | 57.2 |
| | ወ+ሴ | - | - | 46.0 | 31.0 | 31.4 | 39.5 | - | - | 68.1 |
| ሃረሪ | ወ | - | - | 67.4 | 29.9 | 34.5 | 36.8 | - | - | 89.8 |
| | ሴ | - | - | 44.6 | 5.2 | 6.4 | 11.6 | - | - | 65.7 |
| | ወ+ሴ | - | - | 54.7 | 17.8 | 20.3 | 23.2 | - | - | 76.0 |
| አዲስ አበባ | ወ | - | - | 89.1 | 37.6 | 46.4 | 38.8 | - | - | 90.0 |
| | ሴ | - | - | 70.6 | 30.4 | 30.4 | 25.9 | - | - | 71.2 |
| | ወ+ሴ | - | - | 78.9 | 34.3 | 38.5 | 32.8 | - | - | 79.5 |
| ድሬደዋ | ወ | - | - | 64.5 | 22.1 | 21.7 | 21.3 | - | - | 83.5 |
| | ሴ | - | - | 45.9 | 4.9 | 6.0 | 4.2 | - | - | 58.3 |
| | ወ+ሴ | | | 54.9 | 13.2 | 14.1 | 13.2 | - | - | 69.1 |

ምንጭ Zenaselasie Siyoum (2001)

## 2.2 የጤና የትምህርት አገልግሎት መለኪያዎች

ሰንጠረዥ 2 እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ዜጎች በ1996 ከነበረው 25.8% በ 2000 ወደ 29.2% ማደጉን ያሳያል። ማንበብና መፃፍ የሚችሉት ዜጎች ቁጥር ባለፉት አምስት አመታት በገጠርም ሆነ በከተማው በሁለት ያታዎች ጨምሯል። ሆኖም ይህ እድገት ጉልህ ወይም ትልቅ ትርጉም ያለው ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም። ማንበብና መፃፍ የሚችሉት ዜጎች ቁጥር የመጨመሩ ጉዳይ በክልሎቹ መካከል ብቻ ሳይሆን በገጠርና በከተማም ከፍተኛ ልዩነት ይታይባቸዋል።

ሰንጠረዥ 3 ፡- የትምህርት ሽፋን በኢትዮጵያ

| የነዋሪዎች ሰፍራና ፆታ | የትምህርት ሽፋን በትምህርት ደረጃ | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አጠቃላይ ሽፋን | | | | | | ዝርዝር የሽፋን ሁኔታ በተናጠል | | | | | |
| | አንደኛ ደረጃ | | | ሁለተኛ ደረጃ | | | አንደኛ ደረጃ | | | ሁለተኛ ደረጃ | | |
| | 1996 | 1998 | 2000 | 1996 | 1998 | 2000 | 1996 | 1998 | 2000 | 1996 | 1998 | 2000 |
| አገር- ወንድ | 44.9 | 63.2 | 69.8 | 13.7 | 17.4 | 19.0 | 24.0 | 32.5 | 35.8 | 8.8 | 10.9 | 12.2 |
| ሴት | 29.4 | 40.7 | 52.0 | 12.3 | 13.8 | 15.2 | 17.9 | 24.9 | 31.6 | 8.7 | 9.6 | 10.9 |
| ወ+ሴ | 37.4 | 52.3 | 61.1 | 13.0 | 15.6 | 17.1 | 21.0 | 28.7 | 33.8 | 8.8 | 10.2 | 11.6 |
| ገጠር- ወንድ | 37.0 | 56.8 | 64.5 | 4.2 | 7.2 | 8.9 | 17.4 | 27.0 | 30.7 | 1.9 | 3.6 | 5.0 |
| ሴት | 17.5 | 31.0 | 42.8 | 1.6 | 2.4 | 3.8 | 9.4 | 17.8 | 25.2 | 0.9 | 1.5 | 2.6 |
| ወ+ሴ | 27.6 | 44.3 | 54.0 | 3.0 | 4.8 | 6.4 | 13.7 | 22.5 | 28.0 | 1.4 | 2.6 | 3.9 |
| ከተማ- ወንድ | 97.4 | 114.6 | 109.0 | 68.3 | 70.8 | 74.7 | 67.6 | 76.0 | 74.1 | 48.6 | 48.6 | 52.2 |
| ሴት | 107.1 | 105.4 | 113.7 | 53.1 | 61.7 | 62.9 | 70.2 | 70.2 | 74.8 | 38.6 | 44.0 | 45.3 |
| ወ+ሴ | 102.1 | 109.7 | 111.5 | 59.6 | 65.9 | 68.2 | 68.9 | 68.9 | 74.5 | 42.9 | 46.1 | 48.4 |

ምንጭ Zenaselassie Seyom /2001/

/ሰንጠረዥ 3/ የኢኮኖሚና ልማትና ትብብር ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያሳየው በ1997 በኢትዮጵያ ት/ቤት መሄድ ከሚገባቸው ህፃናት ሦስት አራተኛዎቹ የመማር እድል የላቸውም በአንደኛ ደረጃ መማር ከሚገባቸው ከአራቱ አንዱ ብቻ የመማር እድል አለው።

## የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

እንደሚያመለክተው በ1996 ዓ.ም. 21.0% የነበረው የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሽፋን በ2000 ወደ 33.8% ማደጉን ያመለክታል። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሽፋን ከ8.8% ወደ 11.6% እድገት አሳይቷል። ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት በአገር ደረጃ 33.8% የትምህርት ሽፋን እንደነበረና እድሚያቸው ከ7-12% ከሆኑት የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ውስጥ 1/3ኛ ብቻ የመማር እድል እንዳገኙ ያሳያል። በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ነበረው የገልግሎት ሽፋን በገጠርና በከተማ ሲታይ ትርጉም ያለው ልዩነት ይታይበታል።

በ1995/96 በየቤቱ የተካሄደው ጥናት መፃፍና ማንበብ የሚችሉት 22.3% እንደ ነበሩ ያሳያል። ከዚህ ውስጥ ሴቶች 15.3% ሲሆኑ የወንዶቹ 29.2% ብልጫ ያሳያል። በኢትዮጵያ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሽፋን 21.2% ሲሆን ማንበብና መፃፍ የሚችሉት ቁጥር ከገጠሩ ይልቅ በከተማው ይበልጣል። በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት 24% የሆነው የወንዶች ድርሻ 18.2 ከሆነው የሴቶች ድርሻ ልቆ ይታያል። የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች መስፋፋት በከተማ 68.2% ሲሆን በገጠር 15.1% ነው። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሽፋን በአገር ደረጃ 10% ሲሆን ከተሳትፎ አንፃር 9% ከሆነው የሴቶች ድርሻ 10% የሆነው የወንዶች ድርሻ በልጦ ይታያል።

የጤና አገልግሎትና የትምህርት እድል ማግኘትን የሚመዝኑ መለኪያዎች የድህነትን ደረጃ የሚያሳዩ ጠቃሚ መመዘኛዎች ናቸው። ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ሞት እንዲሁም አጠቃላይና ዝርዝር የአገልግሎት ሽፋን መለኪያዎች በስፋት አገልግሎት ላይ የሚውሉ የትምህርት ሁኔታ መለኪያዎች ናቸው። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ትርጉም ያለው የትምህርት መሻሻል ይታያል በ1999 በአንደኛ ደረጃ ያለው አጠቃላይ የትምህርት ሽፋን ከነበረው በ46% ተሻሽሏል። ቢሆንም ከዚሁ ጎን ለጎን የትምህርቱ ጥራት የሚያግዘው የትምህርት ቤቶች መስፋፋት አልታየም። ከዚህም ሌላ ብቃትና ፍላጎት ያላቸው መምህራን እጥረት፣ በአንድ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር መብዛትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ማነስ የትምህርቱን ጥራት ቀንሰውታል።

ሰንጠረዥ 4 ፦ በኢትዮጵያ በአቅራቢያ ከሚገኝ የጤና አገልግሎት መስጫ ጣቢያ
የቤተሰቦች አሰፋፈር በኪሎ ሜትር (1996,1998,2000)

| የመኖሪያ ስፍራ | በአቅራቢያ ከሚገኝ የጤና አገልግሎት መስጫ ያለው ርቀት በኪሎ ሜትር | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 0-4 | | | 5-9 | | | 10- 14 | | | 15እና በላይ | | |
| | 1996 | 1998 | 2000 | 1996 | 1998 | 2000 | 1996 | 1998 | 2000 | 1996 | 1998 | 2000 |
| አገር | 36.2 | 37.5 | 40.1 | 30.3 | 29.4 | 31.0 | 13.5 | 15.3 | 15.0 | 20.0 | 17.8 | 13.9 |
| ገጠር | 25.7 | 27.5 | 31.0 | 34.9 | 33.9 | 35.3 | 15.9 | 17.8 | 17.6 | 23.5 | 20.8 | 16.2 |
| ከተማ | 95.0 | 98.1 | 94.2 | 4.8 | 1.7 | 5.2 | 0 | 0.1 | 0.1 | 0.2 | 0.1 | 0.5 |

ምንጭ Zenaselassie Siyom (2001)

ሰንጠረዥ 4 እንደሚያመለክተው በ2000 ዓ.ም. 40.1% የሚሆኑት መኖሪያ ቤቶች አቀራቢያቸው ካለው የጤና አገልግሎት መስጫ በ4 ኪ.ሜትር ርቀት 31% ዩሚሆኑት በ5-9 ኪ.ሜትር እንዲሁም 15%ቹ በ10-14 ኪ.ሜትር ርቀት እንደሚገኙ ይጠቁማል።

የጤና አገልግሎት ለማሻሻል የተደረገው ጥረት በኤች አይ ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ ምክንያት ተገድቧል። በኢትዮጵያ ለአቅመ አዳም ከደረሰው ዜጋ ውስጥ 10.6% ቫይረስ እንዳለበት ይገመታል። ይህም ከአለም ከፍተኛ ከሚባሉት ነው።

ሰንጠረዥ 5 ፡- በኢትዮጲያ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ሁኔታ (1996,1998,2000)

| የመኖሪያ | የውሃ አቅርቦት ሁኔታና ጥናቱ የተካሄደበት አመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ንፁህ | | | ንፁህ ያልሆነ | | |
| ስፍራ | 1996 | 1998 | 2000 | 1996 | 1998 | 2000 |
| አገር | 19.1 | 23.7 | 27.9 | 80.9 | 76.3 | 72.1 |
| ገጠር | 9.6 | 13.7 | 17.1 | 90.4 | 86.3 | 82.9 |
| ከተማ | 72.1 | 83.5 | 91.7 | 27.9 | 16.5 | 8.3 |

ምንጭ Zenaselassie Siyom (2001)

ንፁህ የመጠጥ ውሃ /አቅርቦት/ ከድህነት መለኪያዎች አንዱ ነው። ሰንጠረዥ 5 እንደሚያመለክተው በኢትዮጵያ የንፁህ ውሃ አቅርቦት በ1996 ከነበረው 19.1% በ2000 ወደ 27.9% እድገት አሳይቷል። ቢሆንም የንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከገጠሩ ይልቅ በከተማው የበለጠ እድገት ማሳየቱን ጥናቶች ያሳያሉ። ለምሳሌ በከተማ በ1996 72.1% የነበረው የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ወደ 91.7% እድገት አሳይቷል። በየአመቱ የተካሄዱት ጥናቶች እንደሚያሳዮት 2.3% የሆነው የከተማ ነዋሪ የራሱ የሆነ የውሃ ቧንቧ ሲኖረው 11.7%ቱ ደግሞ የህዝብ ወይም የቦኖ ውሃ ቧንቧዎችን ይጠቀማሉ። ከዚህም ሌላ 66.3% የሆነው የከተማ ህዝብ የቧንቧ ውሃ ሲያገኝ በገጠር ግን ይህንን አገልግሎት የሚያገኙት 4.4% ብቻ ነው።

እንደ Dercon (2000) ከሆነ በኢትዮጵያ የድህነትና ሌሎች ማህበራዊ ሁኔታዎች የሚመዝኑት መለኪያዎች ቸር ወሬ እያሰሙን ነው ይላል። የረሃብ የድርቅና የጦርነት አስከፊ ገጽታ ሲያሳዩ የነበሩት ሁኔታዎች በአሁኑ ሰአት እየተቀየሩ ናቸው። የነበረውን አስከፊ ሁኔታ ለመቀየር የተወሰዱት እርምጃዎች የተሻለ ውጤት በማምጣት በከተማው የነበረውን ስራ አጥነት እያሻሻሉት ይገኛሉ። የበለጠው የተሻለ ዜና የሚደመጠው ከገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል ሲሆን የድህነት መቀነስና የአንዳንድ አገልግሎቶች ሽፋን መሻሻል ይታያል። በመሠረታዊ የጤና

አገልግሎትም ተመሳሳይ ውጤት እየተመዘገበ ነው። በከተማ ያለው ድህነት ሁኔታ መሻሻል ያሳየ ቢሆንም በመደበኛ የስራ እድልና የስራ ፈጠራ በማሳደግ በኩል ያለው ሁኔታ ተስፋ ሰጪ ነው። ይህ ሁኔታ የሚያሳየው በቅርቡ የተካሄደው የኢትዮጵያና የኤርትራ ጦርነት ኢትዮጵያ ስታካሂድ የነበረችበትን የልማት ጎዳና ላይ የፈጠረውን ጫና ነው። ቢሆንም የህብረተሰቡ ፍጆታም ሆነ ሌሎች ማህበራዊ መመዘኛዎች አሁንም ኢትዮጵያ በጣም ድሃ ከሆኑት አገሮች አንዷ መሆኗን ነው የሚያሳዩት።

## 2.3 ለጥቃት የመጋለጥ መመዘኛዎች

ለጥቃት መጋለጥ  የአንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ በገቢና በጤና ማጣት ችግር ምክንያት የሚያጋጥመውን ችግር ያሳያል። ይህ ችግር ደግሞ ከት/ቤት ለመባረር ለወንጀልና ለሌሎች የተለየዩ ጥፋቶች ያጋልጣቸዋል።

ለጥቃት መጋለጥን መለካት አስቸጋሪ ነው። ለጥቃት መጋለጥ የሚለው ጽንሰሃሳብ በተለያዩ ሁኔታዎች የተለያየ መገለጫዎች ሊይዝ የሚችል በመሆኑ የአንድን ቤተሰብ ሁኔታ ብቻ በመታዘብ ሊገለፅ አይችልም። የችግሩን አስከፊነትና  ለችግር የመጋለጡን አደጋ መለካትና መገንዘብ የሚቻለው በተወሰኑ ቤተሰቦች ላይ አትኩሮ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ በችግሩ ላይ የሚሰጡትን መረጃዎች ባግባቡ  በመመርመር ነው።

ይህንን በተወሰኑ ሰዎች (ናሙና) ላይ አትኩሮ በተለያዩ ወቅቶችና በተከታታይ የሚካሄድ የጥቃት መጋለጥ ጥናት አስቀድሞ የቤተሰቡን ለአደጋ የመጋለጥ ሁኔታ ለመረዳትና ለመጠቆም ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። እነዚህ መመዘኛዎች ቋሚ ንብረቶችን የሰው ሃብት አቅምንና የተለያዩ የገቢ ምንጮችን ማስፋት ሁኔታና ከሌሎች ማህበራዊ ስብስቦች ጋር ያሉ ትስስሮችን (Network) የሚመረምሩ ናቸው።

ቋሚ ንብረት፦ አንድ ቤተሰብ የከፋ ችግር ሲያጋጥመው ችግሩን ሊያቃልል የሚያስችል ሊሸጥ የሚችል ንብረት ያለው መሆኑን ያመለክታል። ቁም ነገሩ የንብረቶቹ ዋጋ ብቻ ሣይሆን ወደ ገንዘብ የመቀየር አቅማቸው ጭምር ነው። የነዚህን ንብረቶች ወደ ገንዘብ የመቀየር ብቃት መገንዘብ ባልታሰበ ችግር ወቅት እንደ መድን ወይም ዋስትና ለመጠቀም ያስችላል።

የሰው ሃብት፦ የተማረ የሰው ሃይል የሌለው ቤተሰብ ገቢ አሽቆልቁሎ የኑሮ ውጣ ውረድ ሲከፋ ተበድሮም ሆነ የተለያዩ የገቢ ምንጮችን ተጠቅሞ ችግሩን ለመወጣት የሚያስችለው አቅም እንደማይኖረው ያሣያል።

የተለያዩ የገቢ ምንጮችን ማስፋት- አንድ ቤተሰብ ምን ያክል ለጥቃት የተጋለጠ መሆኑን ለማወቅ ያሉትን የገቢ ምንጮች መመርመር አስፈላጊ ነው። ይሁንና ይህ መለኪያ የአንድን ቤተሰብ ችግር የመጋለጥ ደረጃ አዛብቶ ሊያቀርብ ይችላል። በማንኛውም ወቅት አጠቃላይ መናጋት ከሚጥፈፉ ብዙ ተግባሮች ይልቅ አነስተኛ አደጋ ያለውን አንድ ተግባር ማከናወን ይመረጣል።

ከሌሎች ስብስቦች ጋር ያለ ትስስር /networks/ ቤተሰባዊ ትስስሮች፣ ለጋራ ጥቅም በሞያ የተሰባሰቡ ቡድኖች ፣ እንደእቁብ የመሳሰሉት የገንዘብ ቁጠባና የብድር ማእከሉች ወይም ነፍስ ወከፍ የቤተሰብ ሃብት ለችግር ገዜ እስተዋፅኦ የሚያደርግበት የተለያየ መልክ ያለው ማህበር ወይም ስብስብ የከፋ ችግር ሲያጋጥም በገንዘብም ሆነ በአይነት ለመደጋገፍ የሚያስችሉ ትስስሮች ናቸው።

ከመድን /Safety-net/ጋር በተያያዙ ተግባሮች መሳተፍ- ማንኛውም ቤተሰብ በችግር ወቅት የሚደርስበትን ጥቃት ሊከላከል የሚችለው ማህበራዊ የስራና የጡረታ ዋስትና በሚሰጡ ወይም ማህበራዊ ድጋፍ ሊያደርጉ በሚችሉ የተለያዮ ተቋሞች ሲሳተፉ ነው።

የብድር ተጠቃሚነት እድል- አንድ ቤተሰብ ከከፋ ችግር ሊድን የሚችለው ገቢውን ለማሳደግ የሚያግዝ ፍጆታውንም ለማሻሻል የሚጠቅም የብድር አገልግሎቶች የማግኘት እድል ሲኖረው ነው።

ሰንጠረዥ 6 ፦ በሳምንት 100 ብር ለማግኘት የሚያስችሉ የገቢ ምንጮች (2000)

| 100 ብር ለማግኘት የሚያስችሉ ዋነኛ ምንጮች | አገር | | ገጠር | | ከተማ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| የቤት እንስሳትና ውጤቶቻቸው ሽያጭ | 3490052 | 30.6 | 3421034 | 34.8 | 69018 | 4.3 |
| የእህል ሽያጭ | 1601945 | 14.0 | 1569005 | 16.0 | 32932 | 2.1 |
| የደን ውጤቶች ሽያጭ | 909948 | 8.0 | 895594 | 9.1 | 14352 | 0.9 |
| የቤት ውስጥ ጥሪቶች ሽያጭ | 66151 | 0.6 | 35880 | 0.4 | 30271 | 1.9 |
| በእጅ ያለ ገንዘብ | 514523 | 4.5 | 226316 | 2.3 | 288205 | 18.1 |
| ከቁጠባ የሚገኝ ገንዘብ | 777225 | 6.8 | 676749 | 6.9 | 100477 | 6.3 |
| እቁብ | 144862 | 1.3 | 34959 | 0.4 | 109902 | 69 |
| እድር | 980784 | 8.6 | 838042 | 8.5 | 340061 | 9.0 |
| ከቤተሰብ የሚገኝ ብድር | 1922602 | 16.9 | 1582542 | 16.1 | 47148 | 21.4 |
| ከሌሎች የሚገኝ ብድር | 269601 | 2.4 | 99743 | 1.0 | 169859 | 10.7 |
| ስጦታ | 523730 | 4.6 | 312284 | 3.2 | 211447 | 13.3 |
| ሌሎች | 193474 | 1.7 | 118396 | 1.2 | 75078 | 4.7 |
| 100 ብር ማግኘት የማይችሉ ቤተሰቦች | 3986933 | 34.6 | 3323030 | 33.7 | 663905 | 39.8 |

ምንጭ Zenaselasie Siyoum (2000)

ሰንጠረዥ 6 አንድ ቤተሰብ ያልታሰበ ችግር ቢያጋጥመው በአንድ ሳምንት ውስጥ 100 ብር ማግኘት ይችል እንደሆን ለቀረበ ጥያቄ የተሰጠውን ምላሽ ያመለክታል። ለጥያቄዎቹ የተሰጡት መልሶች የተቸገሩ ቤተሰቦች ምን ያክል ለአደጋ የተጋለጡ መሆናቸውን እንድንረዳ ያደርጋል። በ2000 ዓ.ም በየተለያዩ ቤተሰቦች የተካሄደው የኑሮ ሁኔታ መጠይቅ ውጤት እንደሚያመለክተው ከሆነ በኢትዮጵያ ካሉት ቤተሰቦች ውስጥ 34.6% ወይም 1/3ኛ ያህሉ በሳምንት 100 ብር ማግኘት እንደማይችሉ ያመለክታል። ይህ እውነታ በገጠሩም ሆነ በከተማ ብዙም ልዩነት የለውም። በጥናቱ እንደታየው በሳምንት 100 ብር ማግኘት የሚችሉት ቤተሰቦች ብሩን ለማግኘት የሚያስችሏቸው ዋነኞቹ ሶስት የገቢ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. የቤት እንስሳትና ውጤቶቻቸውን በመሸጥ /30.6%/

ለ. ከቅርብ ዘመዶች በሚያገኙት ብድር /16.9%/ እንዲሁም

ሐ. የእህል ምርቶችን በመሸጥ /14.0/ ነው።

## 2.4 ተደማጭነትና አቅም ማጣት

የተደማጭነትን አቅም ማጣትን መመዘን የሚቻለው የምርጫ ሁኔታና የነፃ ሚዲያ መኖርን፣ የሲቪሉ ህብረተሰብ የፖለቲካ ነፃነትና የፍትህ ስርአቱን ግልጽነት የሚያሳዩ አገራዊ ሁኔታዎችን ለማጥናት የሚያስችሉና የባለጉዳዩቹን ተሳትፎ የሚያረጋግጡ የተለያዩ መለኪያዎችን በመጠቀም ነው። ቀደም ሲል በተገለፁት የተለያየ ገጽታዎችን የሚያሳዩ መመዘኛዎች ላይ በመመርኮዝ የድህነትን ሁኔታ በትክክለኛውና ዘላቂ በሆነ ሁኔታ መመዘን በተለያዩ አገሮች ያለውን ሁኔታ ለማነፃፀር ያስችላል። ከዚህ አንፃር በኢትዮጵያ የድህነትን ሁኔታ የሚያሳዩት የተለያዩ መመዘኛዎች ያሉት መረጃዎች በጣም ውስን ናቸው።

*የድህነት ገጽታ በኢትዮጵያ*

ድህነትን መለካት

- ድህነት እንዴት ይገለፃል?
- የድህነት ወለል ምንድንነው?
- የድህነት ወለል እንዴት ይገለፃል?
- የድህነት ወለል
- የድህነት ጥልቀት እንዴት ይለካል ?
- የድህነት ክብደት ምንድንነው?

*ድሃውን ለይቶ ማወቅ*

- ድሃው ማነው?
- ድሆች የሚገኙት የት ነው?
- የድሆች እለታዊ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል? አቅማቸውስ ምንድንነው?

*በሂደት የሚታዩ ለውጦች*

- በቁልፍ የድህነት መለኪያዎች በሂደት የታዩ ለውጦች?
- የድህነት ባህርያት

## 3. በኢትዮጵያ የድህነት ገጽታና የድህነት ወለል ጽንሰ-ሃሣብ መመዘኛዎች

ለአንድ ሰው ህልውናና ጉልበት አግኝቶ እንዲሰራ የሚያስፈልገው ምግብና የሌሎች መሰረታዊ ፍላጎቶች ዋጋ ላይ በመመስረት የድህነት ወለልን መለካት በስፋት የተለመደ አሰራር ነው። ይህ መመዘኛ አንድ ሰው በዝቅተኛው ደረጃ ሰርቶ ለመኖር የሚያስፈልገውን የተለያየ የምግብ መጠንና ዓይነት ለመግዛት እንዲችል ማግኘት ያለበትን የገንዘብ መጠን ያስቀምጣል። መመዘኛው የምግብ መጠኑን የሚያሰላው ለሰው ልጅ ያስፈልጋሉ የተባሉትን የካሎሪ መጠኖች ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በዝቅተኛ ደረጃ ለመኖር የሚያስፈልገውን የምግብ መጠንና ዓይነት ለማግኘት የሚጠይቀውን አጠቃላይ ወጪ ለመገመት የሚረዱ ሁለት አማራጮች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. አንድ ቤተሰብ በዝቅተኛ ደረጃ ለመኖር የሚያስፈልገውን የተለያየ የምግብ መጠንና ዓይነት ፍጆታንና ከፍጆታው ያገኘውን የካሎሪ መጠን ወይም ያገኘውን ጉልበት ማስላት ፣

ለ. የተለያዩ ቤተሰቦች የሚፈልገውን የካሎሪ መጠን ለማግኘት የሚያወጡትን አጠቃላይ የወጪ ናሙና በመውሰድ አማካይ ወጪ ማስላት፤

መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን የማስላቱ ዘዴ የሚመሰረተው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙትን 40% ድሆች በዝቅተኛ ደረጃ ለመኖር ተመሳሳይ ለሆኑ የምግብና መጠን ዓይነት የሚያወጡትን ወጪ በመለየት ነው። በሌላ በኩል ምግብ ነክ ያልሆኑ ወጪዎችን ለማስላት የምንጠቀምበት ስታትስቲካዊ ዘዴ አለ። ዋነኛው ሀሳብ የሚያተኩረው እያንዳንዱ ድሃ ግለሰብ ለምግብ የሚያወጣውን ወጪ ከአጠቃላዩ ወጪው ጋር ማነፃፀር ነው። ይሄም Engel Function ተብሎ ይታወቃል።

ድህነትን መለካትና መመዘን ፖለቲካዊ ይዘት ያለውና ጥንቃቄ የሚጠይቅ ተግባር ነው። መንግስታት ድህነትን በመቀነስ ውጤታማ ስራ እየሰሩ መሆናቸውን ለማሳየት የሚፈልጉ ሲሆን በሌላ በኩል ድህነት እየቀነሰ መሆኑን ለማረጋገጥ የተለያዩ አካላት ጫና ያርፍባቸዋል። ከዚህም ሌላ በተለያዩ አካባቢዎች የሚቀርቧቸው ወይም የሚደግፏቸውን ተጠቃሚ ለማድረግና የማይፈልጓቸውን ለማግለል እንዲችሉ የድህነት ትርጉም በሚፈልጉት መንገድ

## የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

እንዲቀመጥ የሚፈልጉ ወገኖች አሉ። የገንዘብ ተቋሞችም ክፍያዎችና ጥቅሞች ያገኛሉ ተብለው የሚታሰቡት በድህነት የታቀፉ ሰዎች ቁጥር እንዲቀንስ ይፈልጋሉ። እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ ብዙ አገሮች ግልፅ የሆነ የድህነት መመዘኛ በማውጣት እንደመፍትሄ ለመጠቀም ሞክረዋል። ከዚህም በተጨማሪ የአንድን አገር የድህነት ወለል ደረጃ በመለየቱ ስራ ዩኒቨርስቲዎችና ሌሎች ነፃ የሆኑ ተቋሞችን ያሳትፋሉ።

የ1995/96 በየቤቱ የተካሄደው የናሙና ጥናት እንደሚያመለክተው ከሆነ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚገኘው ድሃ ከገቢው 60.2%ቱ ወይም 576.8 ብር በነፍስ ወከፍ በአመት ለምግብ ያወጣል። በአገር ደረጃ ህዝቡ 59.6% ወይም 606.8 ብር በአመት ለምግብ ያወጣል። የአገሪቱ አማካይ የተመጣጠነ የምግብ አወሳሰድ ስናይ አንድ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው በቀን 954/ካሎሪ/ እንደሚወስድና ይህም ተመጣጠኝ ነው ተብሎ ከሚታመነው 2200 ካሎሪ ያነሰ ነው። በሌላ በኩል በከተማ ለአንድ አካለ መጠን ለደረሰ ሰው በቀን በአማካይ ከሚያገኘው 1938 ሲሆን በገጠር 2050 አማካይ የካሎሪ ፍጆታ ያገኛል።

እስካሁን ሲገለፅ እንደቆየው ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ገቢ ማግኘት ተስኗቸው እጅግ አነስተኛ በሆነ ገቢ ጉስቁል ህይወት የሚገፉ የህብተረሰብ ክፍሎች ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ ድሆች ይባላሉ። እዚህ ላይ አሳሳቢው ጉዳይ የነዚህን ሰዎች የኑሮ ደረጃ እንዴት እንለካዋለን የሚለው ነው። ድሃውንና ድሃ ያልሆነው የሆነውን ለመለየት የሚያስችል መመዘኛ አንጥሮ ማስቀመጥ ፈታኝ ተግባር ነው። በድህነት አትኩረው የተፃፉ ሰነዶች እንደሚያሳዩት ድህነትን ለመለካት የሚያስችሉ ፍፁምና አንፃራዊ መመዘኛዎች አሉ።

ፍፁም የድህነት ደረጃ በአንድ በኩል በኑሮ ደረጃ መለኪያዎች በሌላ በኩል ደግሞ በአጠቃላይ የድህነት ማነፃፀሪያ ላይ በመመስረት የሚገለፅ ነው ( Ravallion, 1992) ፍፁም ድህነትን ለመለካት የሚጠቀመው ሌላው አማራጭ በካሎሪ ፍጆታና ለሰው ልጅ ጤናማ ህይወት የሚያስፈልገውን ካሎሪ ለማግኘት የሚያስችል ለምግብ በሚወጣ ወጪና ከምግብ ውጭ ለኑሮ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ፍላጎቶች መካከል ያለውን ተግባራዊ ቁርኝት ወይም ትስስር ማየት ነው።

በኢትዮጵያ ያለው የድህነት ወለል ከላይ በተገለፁት መለኪያዎች ላይ ተመስርቶ የተቀመጠ ነው። የነዚህ መለኪያዎች እንዱ ውስንነት በተለያየ ወቅት ለተለያዩ ግለሰቦች የሚያስፈልገው ዝቅተኛ ሀይል ሰጪ የምግብ ዓይነትና መጠን የሚለያይ መሆኑን ስለማያሳይ ነው። ይህ መለኪያ በአብዛኛው በምግብ እጥረት በሚታየው ድህነት ላይ ያተኮረ ነው። እንደሚታወቀው የሰው ልጅ ፍላጎት በተመጣጠነ ምግብ ማግኘት ላይ ብቻ የታጠረ አይደለም። ምንም እንኳ የተለያዩ የአመዛዘን (የመለኪያ) ችግሮች ቢኖሩም በኢትዮጵያ የተካሄዱት ጥናቶች የድህነት

ወሰልን ለማሳየት ሞክረዋል። የፍፁም ድህነት ማሳያዎች በህዝቡ ኑሮ ወስጥ ያለውን የገቢ ክፍፍልና ያለመመጣጠንን ያመለክታሉ። ይህ አሰራር የህብረተሰቡን አጠቃላይ የገቢና የወጪ ድርሻዎች በመቶኛ መዝኖ በመጨረሻ ደረጃ ዝቅተኛውን ድርሻ የሚያገኙትን በድህነት ያስቀምጣል። ይህ ከተሰራ በኋላ በመጨረሻ ደረጃ ዝቅተኛ ድርሻ የሚያገኙትን የህብረተሰብ ክፍሉች በድህነት ውስጥ የሚገኙ ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል። ይህ ቴክኒክ ለአጥኚው ህሊናዊ ፍርድ የተገዛ ነው።

በኢትዮጵያ የድህነት ወሰል የሚለካው በዝቅተኛ ደረጃ ለመኖር የሚያስችል የተለያየ የምግብ መጠንና ዓይነት ለማግኘትና ከምግብ ውጭ የሆኑትን መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት በመጨረሻ የድህነት ደረጃ ላይ የሚገኙትን 25 በመቶ የሚሆኑት ድሆች የወጪ አጠቃቀም መሰረት በማድረግ ነው። በመሰረቱ በድህነት ወሰል የሚገኙ ወገኖች የሚመገቧቸው የምግብ አይነቶች በኢትዮጵያ በምግብ እጦት የሚገለፀውን ድህነት ያሳያሉ። በዋናው ስታስቲክስ ቢሮ (CSA) በ1995/96 እንዲሁም በ1999/2000 የተካሄደው የያንዳንዱ ቤተሰብ ገቢ ፣ ፍጆታ ፣ ወጪና የኑሮ ሁኔታ የሚያመለክቱትን ጥናቶች እንዲሁም በ1994, 1995 እና 1997 የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኢኮኖሚክስ ዲፓርትመንት ከኦክስፎርድና ከጉተንበርግ ዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር በተወሰኑ ቤተሰቦች ላይ አትኩረው በተከታታይ በተለያዩ ወቅቶች ያካሄዱትን ጥናት መሰረት በማድረግ ነው። በኢትዮጵያ ያለውን የድህነት ወሰል ለመግለፅ ከላይ የተገለጹት ጥናቶች ሞክረዋል። የነዚህ የድህነት ወሰል ጥናት ቁልፍ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) አንድ ጎልማሳ በቀን የሚያገኘው የካሎሪ መጠን ፦ ይህንን ለመመዘን የዓለም የጤና ድርጅት ለአንድ ጎልማሳ ቢያንስ 2200 ካሎሪ በቀን ማግኘት ይኖርበታል የሚለውን መነሻ መሰረት ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህም በምግብ እጦት የሚገለፀውን ድኅነት መረዳት ይቻላል።

ለ) በዝቅተኛ ደረጃ ለመኖር የሚያስፈልገው የተለያየ የምግብ መጠንና ዓይነት ፦ በዚህ መሰረት በዝቅተኛ ደረጃ ለመኖር ድሃው ህብረተሰብ የሚመገባቸው የምግብ ዓ ይነቶችና መጠን በዝርዝር ማስቀመጥና ከዚህ በኋላ ለያንዳንዱ የምግብ ዓይነት የወጣውን ወጪ ከለዩ በኋላ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን የምግብ ዓይነቶች የማወቅ ስራ ይሆናል።

ሐ) የካሎሪ አወሳሰድን ማወቅ ፦ የሚያመለክተው በዝቅተኛ ደረጃ ህይወቱን የሚገፋ አንድ ጎልማሳ በቀን ከሚወስዳቸው የምግብ ዓይነቶች የሚያገኘውን ካሎሪ ፍጆታ ነው። ይሄም የድህነት ወለልና ዝቅተኛውን የካሎሪ ፍጆታ ድርሻ ያሳያል።

መ) አማካኝ የምግብ ወጪ ፦ አንድ ጎልማሳ ዝቅተኛውን የምግብ አቅርቦት ለማግኘት በዓመት የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ያሳያል።

ሠ) ከምግብ ውጭ ያሉ ፍላጎቶችን መለየት ፦ አንድ በድህነት ወለል ላይ የሚገኝ ቤተሰብ ለምግብ የሚያወጣውን ወጪና ከምግብ ውጭ ለሆኑ ፍላጎቶች የሚያወጣውን ወጪ አማካይ በመውሰድ የሚሰላ ይሆናል።

ሰንጠረዥ 7 ፦ በአገር አቀፍ በዝቅተኛ ደረጃ በሚኖሩ ድሆች ለፍጆታ የሚውሉ የምግብ ዓይነቶች ናሙና 1995/96

| የምግብ ዓይነት | የካሎሪ ድርሻ | የካሎሪ መጠን | መጠን (በግራም) | የድህነት ወለል መጠን (በብር) | የወጪ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| ያልተፈጩ ጥራጥሬዎች | 22% | 483.95 | 140.68 | 76.71 | 12% |
| የተፈጩ ጥራጥሬዎች | 48% | 1049.37 | 305.89 | 240.08 | 37% |
| ያልተፈጩ የቅባት እህሎች | 6% | 133.24 | 38.23 | 26.36 | 4% |
| የተፈጩ የቅባት እህሎች | 5% | 106.42 | 30.71 | 32.79 | 5% |
| የዘይት ፍሬዎች | 1% | 13.45 | 2.74 | 2.77 | 0% |
| የተለያዩ ጥራጥሬዎች | 0% | 0.22 | 0.15 | 0.25 | 0% |
| ዳቦና ሌሎች የተዘጋጁ ምግቦች | 2% | 39.79 | 12.94 | 10.72 | 2% |
| ስጋ | 0% | 6.88 | 3.82 | 12.52 | 2% |
| አሳ | 0% | 0.02 | 0.02 | 0.03 | 0% |
| ወተት ፣ ዓይብና እንቁላል | 1% | 18.27 | 27.07 | 17.45 | 3% |
| ዘይትና ቅቤ | 1% | 19.29% | 2.41 | 12.82 | 2% |
| አትክልቶች | 2% | 40.81 | 103.76 | 27.28 | 4% |
| ፍራፍሬዎች | 2% | 34.08 | 11.9 | 38.67 | 6% |
| ቅመማ ቅመም | 0% | 1.48 | 2.23 | 0.99 | 0% |
| ድንችና እንደ ቀይ ስር ያሉ | 8% | 177.47 | 119.72 | 59.99 | 9% |
| ቡና ፣ ሻይ | 2% | 47.92 | 26.53 | 71.49 | 11% |
| ጨው ፣ ስኳርና ሌሎች | 1% | 27.4 | 20.68 | 16.85 | 3% |
| ሁሉም ዓይነቶች | 100% | 2200.06 | - | 647.81 | 100% |

ሰንጠረዥ 7 እንደሚያሳየው በመጨረሻ ደረጃ ከሚገኙት 25 በመቶ የሚሆኑት ድሆች ውስጥ የሚመደብ ሰው 70% ካሎሪ የሚያገኘው ከጥራጥሬ ነው። ቀደም ሲል በተገለፀው ደረጃ የሚገኝ ደሃ ከተለያዩ የቅባት እህሎች የሚያገኘው ካሎሪ 12% ነው። ከድንችና ከስራስርም እንደዚሁ 8% ያገኛሉ። በኢትዮጵያ በ1995/96 በድህነት ወለል የሚገኝ አንድ ጎልማሳ ለሚመገበው ዝቅተኛ ምግብ በዓመት 647.81 ብር (100 የአሜሪካን ዶላር አካባቢ) ያስፈልገዋል።

በ1995/1996 በየቤቱ የተካሄደው መጠይቅ እንደሚያመለክተው ከኢትዮጵያ ህዝብ 50% የሚሆነው ለዕለት የሚያስፈልገውን ዝቅተኛ የምግብ መጠን አያገኝም። በምግብ እጦት የሚገለፀው ድህነት በገጠርና በከተማ ልዩነት አለው። በገጠር ከሚኖሩት 52% በከተማ ከሚኖሩት ደግሞ 36% የሚያስፈልጋቸውን ዝቅተኛ የምግብ አቅርቦት አያገኙም።

በኢትዮጵያ ፍፁም ድህነትን መግለፅ የሚቻለው ለኑሮ የሚያስፈልገውን ምግብ ብቻ በማስላት ሳይሆን ሌሎች ፍላጎቶችንም በማጣመር ነው። በሰንጠረዥ 7 በድህነት ወለል ላይ የሚገኙ ድሆች ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን አነስተኛ የምግብ አቅርቦት ተመልክተናል። አሁን የምናየው ከምግብ ውጭ ያሉ ፍላጎቶችን ነው።

በድህነት ወለል የተቀመጠውን የምግብ ፍጆታ መጠን ማሟላት የቻሉ ወገኖችን ሌሎች ወጪዎችን ለማወቅ የሚያስችለውና በስፋት ስራ ላይ የሚውለው ዘዴ የእንድን ቤተሰብ መገለጫዎች ከአካባቢው ሁኔታ ጋር በማዛመድ ይመረምራል። ይህ በቀጥታ የሚለካው በድህነት ወለል ላይ የሚገኙትን ድሆች በመውሰድና እነዚህ ድሆች ከምግብ ውጭ የሚጠቀሙትን የሚገዙትን በማስላት ይሆናል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር (MEDAC) የ1995/96 ጥናት መሰረት አድርጎ በ1999 እንዳስቀመጠው ከሆነ ለአንድ ጎልማሳ ከምግብ ውጭ ላሉ ፍላጎቶች በዓመት 427.22 ብር ያስፈልገዋል (65.7 የአሜሪካን ዶላር ያክል) ለዓመት ከምግብ ውጭ ላሉ ፍላጎቶች አንድ ጎልማሳ የሚያስፈልገውን 427.22 በዓመት ለምግብ ከሚያስፈልገው 647.81 ብር ጋር ደምረን ብናየው በድህነት ወለል ላይ ያለ ጎልማሳ ዝቅተኛውን የድህነት ህይወት ለመግፋት በዓመት 1075.03 ብር ወይም 165.4 የአሜሪካን ዶላር አካባቢ ያስፈልገዋል። ስለዚህ አንድ ኢትዮጵያዊ ጎልማሳ ከፍፁመ ድህነት ለማምለጥ በዓመት 1075.03 ብር ወይም ከዚህ በላይ 89.59 ብር በወር ማግኘት ይጠበቅበታል።
ፍፁም ድህነትን ለመለካት የሚያስችሉ ሶስት መመዘኛዎች አሉ። እነዚህም ፦

## የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

ሀ) የድህነት ወለል መመዘኛዎች ፦ ይህ መመዘኛ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ ሰዎች ምን ያህል እንደሆኑ ያሳያል። ከዚህ ውጭ የድሆችን ህይወት በጥልቀት አያሳይም።

ለ) የድህነት ጥልቀት ፦ ይህ መለኪያ በድህነትን ወስጥ ያለ ልዩነትን ይመለከታል። ይህ የድህነት መለኪያው የሚያተኩረው ከድህነት ወለል ባሉት ድሆች የድህነት ያለመመጣጠን ላይ ነው። በድህነት ወለል በታች ያሉት ድሆች በመሀከላቸው ያለውን ልዩነት ለማሳየት የተለያዩ የስታቲስቲክስ ዘዴዎች አሉ።

ሐ) የድህነት ክብደት ፦ በዚህ መለኪያ በድህነት ውስጥ ያለውን መራራ ወይም አስከፊ ህይወት ይለካል። የድህነት ክብደትን ለመለካት የምንጠቀምበት ዘዴ ከድህነት ወለል በታች ያሉትን ድሆች በመወሰድና በመሃከላቸው ያለውን ልዩነት በማስላትና ይህንን ውጤት በራሱ በማባዛት ይሆናል።

ሰንጠረዥ 8 በ1995/96 በየቤቱ የተካሄደውን ጥናት መሰረት በማድረግ በኢትዮጵያ በፍፁም ድህነት የሚገኙትን ዜጎች ያመለክታል። ከጥናቱ መረዳት የሚቻለው 45.5% የሚያህለው የኢትዮጵያ ህዝብ በዝቅተኛ የድህነት ኑሮ ለመኖር የሚያስፈልገውን በማጣት ከድህነት ወለል በታች እንደሚኖር ነው። በድህነት ውስጥ የ13% ልዩነት መኖሩንና ከኢትዮጵያ ህዝብ 13% በዝቅተኛው የድህነት ህይወት ለመኖር የሚያስችለውን ማግኘት እንደማይችሉ ጥናቱ ያሳያል። በአገር አቀፍ ደረጃ የድህነቱ ክብደት 5% መሆኑም ጥናቱ ያመለክታል።

ሰንጠረዥ 8 ፦ በኢትዮጵያ ክልሎች የሚገኙ የፍፁም ድህነት ገፅታ ፦ 1995/96

| ክልል | ፍፁም ድህነት | በድህነት ውስጥ ያለ ልዩነት | የድህነት ክብደት |
|---|---|---|---|
| ትግራይ | 57.9% | 18.0 % | 7.0 % |
| አፋር | 51.8% | 16.0 % | 6.0 % |
| አማራ | 56.7% | 17.0 % | 7.0 % |
| ኦሮሚያ | 34.7% | 8.0 % | 3.0 % |
| ሶማሌ | 34.6% | 8.0 % | 3.0የ |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | 47.6% | 14.0 % | 5.0 % |
| ደቡብ ክልል | 56.5% | 18.0 % | 7.0 % |
| ጋምቤላ | 41.8% | 12.0 % | 5.0 % |
| ሀረሪ | 29.1% | 2.0 % | 3.0 % |
| አዲስ አበባ | 30.0% | 11.0 % | 4.0 % |
| ድሬደዋ | 24.6% | 9.0 % | 2.0 % |
| ብሄራዊ | 45.5% | 13.0 % | 5.0 % |

ሰንጠረዥ 8 እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ የፍፁም ድህነት ሁኔታ በክልሎች መካከልም በተለያየ ደረጃ ነው የሚገለፀው። ለምሳሌ ከድህነት ወለል በታች የሚገኙትን ብናይ በድሬዳዋ (24.6%)

በሀረሪ 29.1 እንደሁም በአዲስ አበባ 30.0% ካሉት ይልቅ በትግራይ 57.9% እንደሚገኙ የሳያል። የድህነት ጥልቀት (ክብደት) በሀረሪ (2%) በኦሮሚያ (8.0%) ሶማሊያ (8.0%) ከሚታየው ይልቅ በትግራይ (18.0%) በደቡብ ክልል (18.0%) ጎልቶ ይታያል። በአጠቃላይ በ1995/96 ማዕከላዊ የስታትስቲክስ ጽ/ቤት ያካሄደው ጥናት የድህነቱ አስከፊነት በትግራይ በአማራና በደቡብ ክልሎች የበለጠ እንደሚታይ ይገልፃል።

(Stefan Dercon and Pramila Krishman 1996) በተወሰን አካባቢዎች የናሙና ጥናት መረጃ መሰረት በማድረግ በ1994 በኢትዮጵያ ገጠሮች ያለውን የድህነት ወሰል ፣ በድህነት ውስጥ ያለ ልዩነትና የድህነቱን ክብደት ለመመዘን ሞክረዋል። በዚህ ጥናታቸው ከ15 የተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች 1477 ቤተሰቦችን በናሙናነት አካትተዋል።

ሰንጠረዥ 9፦ በተወሰኑ ቤተሰቦች ላይ በማትኮር በተለያዩ ወቅቶችና በተከታታይ የተካሄደው ጥናት የሚያሳየው የኢትዮጵያ የድህነት ሁኔታ (1994)

| አካባቢ | ልዩ ስፍራ | የድህነት ወሰል | የድህነት ጥልቀት | የድህነት ክብደት | (በቁጥር) |
|---|---|---|---|---|---|
| ትግራይ | | 0.20 | 0.07 | 0.04 | 84 |
| ትግራይ | | 0.62 | 0.24 | 0.12 | 66 |
| ሰሜን ሸዋ | | 0.46 | 0.15 | 0.07 | 87 |
| ጎጃም | | 0.12 | 0.02 | 0.00 | 59 |
| ሰሜን ወሎ | | 0.16 | 0.03 | 0.01 | 148 |
| መካከለኛው ሸዋ | | 0.08 | 0.02 | 0.01 | 96 |
| ሃረርጌ | | 0.10 | 0.04 | 0.02 | 97 |
| አርሲ | | 0.61 | 0.26 | 0.13 | 109 |
| ደቡብ ሸዋ | | 0.14 | 0.05 | 0.03 | 101 |
| ጉራጌ | | 0.12 | 0.02 | 0.00 | 67 |
| አምባታ | | 0.09 | 0.01 | 0.00 | 75 |
| ሲዳሞ/ዲላ | | 0.15 | 0.04 | 0.02 | 130 |
| ወላይታ | | 0.76 | 0.38 | 0.22 | 96 |
| ጋሞጎፋ | | 0.60 | 0.23 | 0.12 | 72 |
| ኢትዮጵያ | | 0.27 | 0.10 | 0.05 | 1470 |
| አጠቃላይ | | | | | |
| የሰሜንደጋማ አካባቢዎች ትግራይ፣ ወሎ | | 0.25 | 0.09 | 0.04 | 298 |
| መካከለኛውደጋማ አካባቢዎች | | 0.19 | 0.05 | 0.02 | 425 |
| እንሰት አብቃይ አካባቢዎች /ጉራጌ ከምባታ ሲዳሞ | | 0.10 | 0.04 | 0.02 | 272 |
| ወላይታ ጋሞጎፎ | | 0.45 | 0.20 | 0.11 | 168 |
| ደቡብ ሸዋ አርሲ | | 0.39 | 0.16 | 0.08 | 210 |
| ሃረርጌ | | 0.10 | 0.04 | 0.02 | 97 |

በሰንጠረዥ 9 የተቀመጡት አሃዞች 27% የሚሆነው ቤተሰብ ዝቅተኛውን ህይወት መምራት እንደማይችል ያመለክታሉ። ይህ አሃዝ የአገሪቱን አጠቃላይ ሁኔታ ይገልፃል ባይባልም በተለያዩ ወረዳዎችና መንደሮች ያለውን የድህነት ሁኔታ፣ ጥልቀቱንና ክብደቱን በማሳየት

## የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

በኩል ጠቃሚ መረጃዎች ያቀርባል። በሌላ በኩል በተለያዩ ወረዳዎችና መንደሮች ያለውን ፍፁም የድህነት ሁኔታ ሰፊ ልዩነት እንዳለው መረጃው ይገልፃል። በማነፃፀሪያው ለተወሰዱት የተለያዩ የፍፁም ድህነት መገለጫዎች መረጃዎች ጠቃሚና ትርጉም ያላቸው ናቸው።

Stefan and Krishman የድህነት ወለሉን ሲመዝኑ አንድ ጎልማሳ የሚወስደው የካሎሪ መጠን ለነፍስ ወከፍ የምግብ ፍጆታ ወጪ ጋር በማገናኘት አስልተውታል። ይህንን ሲያሰሉ ለአንድ ግለሰብ ያስፈልጋል የተባለውን 2200 የካሎሪ መጠን ለማግኘት የሚወጣውን የምግብ ወጪ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በዚህ መሰረት ለአንድ በድህነት ወለል ለሚኖር ጎልማሳ ወርሃዊ ወጪ 45.8 ብር ነው። በዚህ ጥናት ከድህነት ወለሉ በታች የሚኖሩት 42% መሆኑን አሳይተዋል።

(Mekonnen 1996) ከአዲስ አበባ ፣ ድሬዳዋ ፣ አዋሳ ፣ ደሴ ፣ ባህርዳር ፣ ጂማና መቀሌ የሚኖሩ 1500 ቤተሰቦችን በናሙናነት በመውሰድ የድህነት አመልካቾችን ፣ በድህነት ውስጥ ያሉ ልዩነቶችንና ዋስትና ማጣትን ለመመዘን በ1994 ያደረጉት ጥናት ውጤት እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 10 ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 10 ፦ በከተሞች በምግብ የድህነት ወለል ሁኔታ (በመቶኛ)

| ከተሞች | ፍፁም ድህነት | የድህነት ጥልቀት | የድህነት ክብደት | ናሙና |
|---|---|---|---|---|
| አዲስ አበባ | 44.2 | 17.09 | 9.47 | 895 |
| አዋሳ | 47.9 | 12 | 11.7 | 71 |
| ባህርዳር | 30.0 | 9.54 | 6.05 | 100 |
| ድሬዳዋ | 39.8 | 14.67 | 8.05 | 93 |
| ጅማ | 34.3 | 13.57 | 6.89 | 99 |
| መቀሌ | 33.7 | 1.57 | 13.64 | 98 |
| ሁሉም ከተሞች | 38.9 | 14.09 | 8.65 | 1480 |

ሰንጠረዥ 10 በሰባቱም የኢትዮጵያ ከተሞች ከሚኖረው 39% ቱ ከድህነት ወለል በታች እንደሚኖር ያሳያል። የድህነት ወለሉ ፣ በድህነት ውስጥ ያለውን ልዩነትና የድህነቱን ክብደት የሚያሳዩት መለኪያዎች በከተሞች መካከልም የድህነቱ ሁኔታ የተለያየ መሆኑን ያሳያሉ።

በ1995/96 የተካሄደው የኑሮ ሁኔታ ጥናት ላይ በመመስረት የውጭ የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር በ1999 ባቀረበው ሪፖርት በአገሪቱ የሚገኘውን አንፃራዊ ድህነት ወይም አንፃራዊ

መገለልን ለመለካት ጥረት አድርጓል። ሪፖርቱ እንዓራዊ ድህነት ውስጥ ናቸው የሚላቸውን ሲገልፅ አንድ ጎልማሳ በዓመት የሚያወጣው አማካይ ወጪ በአገር አቀፍ ደረጃ ከተቀመጠው አማካይ ወጪ ከሁለት ሶስተኛ ያነሰ ከሆነ እንዓራዊ ድህነት ውስጥ የሚገኝ ብሉ ይገልፀዋል። ሪፖርቱ አንድ ጎልማሳ በአማካይ በዓመት 1311.4 ብር እንደሚያወጣ ታሳቢ ያደርጋል። የዚህ 2/3ኛ 874.31 ብር ሲሆን ይሄም የእንዓራዊ ድህነት ማሳያ ነው። የዚህ ሪፖርት ውጤት ከኢትዮጵያ ህዝብ 30% የሚሆነው በእንዓራዊ ድህነት ውስጥ እንደሚኖር ያመለክታል።

በኢትዮጵያ በከተማና በገጠር የድህነት ዋና ዋና ገፅታዎች

- የነፍስ ወከፍ የቤት ወጪ ፤
- ዕለታዊ የካሎሪ ፍጆታ ፤
- አንድ ቤተሰብ ለምግብ የሚያወጣው አማካይ ወጪ ፤
- የገቢ ያለመመጣጠን ፤
- በገጠርና በከተማ ድህነት የሚታዩ ለውጦች ፤
- ድህነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች መንደፉ ፤

## 4. በኢትዮጵያ ከተሞችና ገጠር የድህነት ዋና ዋና ገፅታዎች

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በግብርና ላይ የተመሰረተ ነው። ከአገሪቱ አጠቃላይ ዓመታዊ ምርት ውስጥ 50% ከግብርና የሚገኝ ነው። 85% የሚሆነው የአገሪቱ ህዝብ በግብርና ላይ የተሰማራ ነው። የአገሪቱ ተራራማ መልክአ ምድር የመገናኛ አውታሮች እንዳይስፋፉ ተፅዕኖ አድርጓል። የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር በዓመት በ3% ዕድገት ያሳያል።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ ድህነት የሚታይባት አገር ነች። የማዕከላዊ ስታትስቲክ ጽ/ቤት በ1995/96 የቤተሰብ ገቢ ፣ ወጪና የኑሮ ደረጃ ላይ ያደረገው ጥናት ችንደሚያመለክተው 50% የሚሆነው የአገሪቱ ህዝብ አነስተኛውን የምግብ አቅርቦት አያገኝም። ድህነቱ ከከተማው ይልቅ በገጠሩ ጎልቶ የሚታይ ሲሆን ከገጠሩ ነዋሪ 52% ከከተማው 36% ዝቅተኛውን የምግብ አቅርቦት እንደማያገኝ ጥናቱ ይጠቁማል። ሰንጠረዥ 8 እንደሚያሳየው 45.5% የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ከድህነት ወለል በታች ላይ ይገኛል። የከፋው የድህነት ደረጃ በትግራይ ቀጥሎም በአማራና በደቡብ ክልል ይታያል። በኢትዮጵያ የሚታየው ድህነት የበርካታ ሁኔታዎች ማለትም የህዝብ ብዛት ፣ የተፈጥሮ ሀብት መራቆት ፣ የስራ እጥነት መስፋፋት ፣ የድርቅ ፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎት ዝቅተኝነትና ፣ የሃብት እጦትና የሌሎች ችግሮች መገለጫ ነው።

በኢትዮጵያ የተመጣጠነ ምግብ ያለማግኘት ችግር እየተስፋፋና አብዛኛው ህዝብም በምግብ ዋስትና እጦት ለከፋ ችግር ተጋልጦ ይገኛል። የአገር ውስጥ ምርት እያደገ ቢመጣም ኢትዮጵያ አሁንም ከፍተኛ የውጭ የምግብ እርዳታ ላይ ነው የምትገኘው። ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ከፍተኛውን የውጭ የምግብ እርዳታ የምታገኝ አገር ስትሆን ፣ ከ1984 እስከ 2000 ድረስ ያገኘችው 10 ሚሊዮን ቶን የሚጠጋ የምግብ እርዳታ ከአገሪቱ ዓመታዊ የእህል አቅርቦት 10% ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ምግብ እርዳታ ታገኛለች።

በገጠር የተንሰራፋው የተመጣጠነ የምግብ እጦት ህፃናትን ከመቀጨቱም በላይ አማካይ የህይወት ዘመን ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጓል። በህፃናት የሚከሰተው የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ለዜጎች አካላዊና አዕምሯዊ ብቃት መዳከም አስተዋፅኦ እያደረገ ይገኛል። ከስድስት ዓ መት እድሜ በታች የሆኑ ህፃናት ሞት በ1983 ከነበረው 60% በ1992 ወደ 64% ዕድገት አሳይቷል። የዓለም ባንክ መረጃ ለዜጎች ሞት 7.8% ምክንያት የሚሆነው የተመጣጠነ ምግብ እጦት መሆኑንና 53% የሚሆነው የአገሪቱ ህዝብ የምግብ ዋስትና እንደሌለው ያመለክታል።

## የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

የ1998 የአለም ባንክ መረጃ በ1990ዎቹ በረሃማነት እየጨመረ መምጣቱንና የተመጣጠነ ምግብ እጦት ከከተማው ይልቅ በገጠሩ በስፋት እንደሚታይ ያስረዳል። አብዛኛውን ጊዜ ለምግብ ዋስትናና ለተመጣጠነ ምግብ ማጣት ምክንያቱ የምግብ አለመኖር ብቻ ሳይሆን ድሀው የህብረተሰብ ክፍል የማምረቻ መሣሪያዎችና የአገሪቱ ሃብቶች ተጠቃሚ ባለመሆናቸው ነው።

በገጠር የሚታየው የእርሻ የመሬት ጥበት ፣ የተፈጥሮና የእንስሳት ሀብት መጎዳት፣ በዝናብ ላይ ብቻ የተንጠለጠለ እርሻ ፣ የተለያዩ ተቋሞች ያለመጠናከርና መረጃ አለማግኘት ፣ የመሰረታዊ አገልግሎቶች አለመኖር ለምግብ ዋስትናና ለችግር መጋለጥ ምክንያቶች ናቸው (Middle Brook et al 2001) በሌላ በኩል የሚታዩ አንዳንድ ግጭቶች የትምህርት ፣ የጤና የመንገድና የእርሻ አገልግሎት እንዳይስፋ እንቅፋት ፈጥረዋል።

የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ማሳያዎችም ድህነት በኢትዮጵያ እየተስፋፋ መሆኑን ነው የሚያመለክቱት። በኢትዮጵያ በ1994 ከውልደት ግዜ አማካይ የህይወት ዘመን 50.6 ዕድሜ እንደነበረና ከ1000 ጨቅላዎችና ህፃናት ውስጥ 118 ጨቅላዎችና 73 ህፃናት እንደሚሞቱ እንዲሁም በወሊድ ከ100,000 እናቶች ውስጥ 700 እንደሚሞቱ ያሳያል። በ1995 77% ሴቶች 55% ወንዶች መሃይማን እንደነበሩ አጠቃላይ በአንደኛ ደረጃ የነበረው የትምህርት ዕድገት በ1993 23% እንደነበር ያመለክታል። (Interim PRSP, 2000)

ሰንጠረዥ 11 ፦ ጥናቱ በተካሄደበት ዓመት በአገር አቀፍና በክልል ደረጃ የነፍስ ወከፍ የቤት ወጪ (በብር) (1995/96 and 1999/2000)

| ክልል | መለኪያዎችና ጥናቱ የተካሄደበት ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የቤት ውስጥ ወጪ | | ሁሉም ክፍያዎች | |
| | 1995/96 | 1999/2000 | 1995/96 | 1999/2000 |
| ትግራይ - አጠቃላይ | - | 1189.45 | - | 1293.38 |
| ገጠር | 1209.60 | 1120.86 | 1280.83 | 1197.60 |
| ከተማ | - | 1536.65 | - | 1778.26 |
| አፋር - አጠቃላይ | - | 1537.71 | - | 1605.60 |
| ገጠር | 1520.46 | 1127.01 | 1587.65 | 1154.32 |
| ከተማ | - | 2302.04 | - | 2445.45 |
| አማራ - አጠቃላይ | - | 1165.59 | | 1356.45 |
| ገጠር | 974.42 | 1095.67 | 1031.59 | 1251.12 |
| ከተማ | - | 1754.39 | - | 2243.45 |
| ኦሮሞ - አጠቃላይ | - | 1208.40 | - | 1412.25 |
| ገጠር | 1282.91 | 1144.48 | 1360.92 | 1297.87 |
| ከተማ | - | 1701.01 | - | 2293.77 |
| ሶማሊ - አጠቃላይ | - | 1626.71 | - | 1772.20 |
| ገጠር | 1975.42 | 1395.12 | 2008.31 | 1442.40 |
| ከተማ | - | 2106.72 | - | 2455.81 |
| ቤንሻንጉልጉምዝ - አጠቃላይ | - | 1158.31 | - | 1266.39 |
| ገጠር | 1074.99 | 1088.44 | 1127.22 | 1176.44 |
| ከተማ | - | 2014.27 | - | 2368.40 |
| ደቡብ ህዝቦች ክልል - አጠቃላይ | - | 1080.07 | - | 1238.68 |
| ገጠር | 1021.34 | 1025.18 | 1115.01 | 1150.51 |
| ከተማ | - | 1768.86 | - | 2345.18 |
| ጋምቤላ - አጠቃላይ | - | 1330.32 | - | 1417.18 |
| ገጠር | 1706.66 | 1255.71 | 1774.10 | 1209.38 |
| ከተማ | - | 1898.10 | - | 2122.49 |
| ሀረሪ - አጠቃላይ | - | 1904.90 | - | 2063.76 |
| ገጠር | 2388.73 | 1618.71 | 2472.25 | 1763.37 |
| ከተማ | 2192.57 | 2106.19 | 2489.39 | 2275.04 |
| አዲስ አበባ - አጠቃላይ | - | 2465.66 | - | 2898.90 |
| ገጠር | 1685.89 | 1540.35 | 1774.33 | 1976.03 |
| ከተማ | 2207.96 | 2482.87 | 2399.57 | 2916.07 |
| ድሬዳዋ አስተዳደር- አጠቃላይ | - | 1766.95 | - | 2052.67 |
| ገጠር | 1682.83 | 1394.43 | 1696.84 | 1450.84 |
| ከተማ | - | 1899.32 | - | 2266.56 |
| በአገር አቀፍ - አጠቃላይ | 1222.56 | 1222.45 | 1319.08 | 1411.80 |
| ገጠር | 1136.59 | 1109.92 | 1210.30 | 1244.00 |
| ከተማ | 1696.52 | 1921.02 | 1918.83 | 2400.71 |

ምንጭ: Zenaselassie Siyoum (2001)

## የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

ሰንጠረዥ 11 እንደሚያሳየው በ1999/2000 በኢትዮጵያ የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ክፍያ 1412 ብር የነበረ ሲሆን የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ የቤት ወጪ ግን 1222 ሆኖ በ1995/96 ከነበረው ነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ወጪ ተመሳሳይ ነው። በሌላ በኩል የነፍስ ወከፍ አማካይ ዓመታዊ ክፍያ ከነበረው በ1999/2000 ዕድገት አሳይቷል። የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ የቤት ወጪ ላይ በክልሎች መካከል ልዩነት የሚታይ ሲሆን በ1995/96 በትግራይ ፣ በአፋር ፣ በኦሮሚያ ፣ በሶማሊያና በጋምቤላ ከነበረው ሁኔታ በ1999/2000 አሽቆልቁሉ ይታያል። ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ፍጆታ ከከተማ ይልቅ በገጠር ቀንሶ ይታያል።

ሰንጠረዥ 12 ፦ በክልል ደረጃ የነፍስ ወከፍ የካሎሪ ፍጆታ 1999/2000

| ክልል | ዕለታዊ የካሎሪ ፍጆታ | | |
|---|---|---|---|
| | አጠቃላይ | ገጠር | ከተማ |
| ትግራይ | 2045 | 2124 | 1646 |
| አፋር | 1743 | 1617 | 2337 |
| አማራ | 2155 | 2197 | 1801 |
| ኦሮሚያ | 2257 | 2344 | 1588 |
| ሶማሊያ | 1960 | 2002 | 1869 |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | 2245 | 2273 | 1911 |
| ደቡብ ህዝቦች ክልል | 2359 | 2401 | 1821 |
| ጋምቤላ | 2177 | 2285 | 1809 |
| ሀረሪ | 1967 | 2304 | 1730 |
| አዲስ አበባ | 1829 | 2117 | 1824 |
| ድሬደዋ | 1876 | 2198 | 1761 |
| አጠቃላይ | 2212 | 2293 | 1738 |

ምንጭ: Zenaselassie Siyoum (2001)

ሰንጠረዥ 12 እንደሚያመለክተው በ1999/2000 በኢትዮጵያ የነበረው የነፍስ ወከፍ የካሎሪ ፍጆታ 2212 ነበር። ዕለታዊ የነፍስ ወከፍ ካሎሪ ፍጆታ ከከተማ ይልቅ በገጠሩ በልጦ

ይታያል። በዕለታዊ የካሎሪ ፍጆታ አወሳሰድ በክልሎች መካከል ትርጉም ያለው ልዩነት ይስተዋላል። ለምሳሌ በአፋር የነበረው እለታዊ የነፍስ ወከፍ የካሎሪ ፍጆታ 1743 ሲሆን በደቡብ ክልል ግን 2359 ነበር።

ሰንጠረዥ 13 ፦ በ1999/2000 በኢትዮጵያ አንድ ቤተሰብ ለምግብ የሚያወጣው ወጪ ድርሻ/በመቶኛ/

| የመኖሪያ ስፍራ | የምግብ ድርሻ ሪፓርት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አጠቃላይ | | ገጠር | | ከተማ | |
| | 95/96 | 99/00 | 95/96 | 99/00 | 95/96 | 99/00 |
| ብሄራዊ | 52.7 | 52.5 | 54.2 | 57.3 | 47.1 | 35.9 |
| ትግራይ | - | 60.4 | 64.6 | | - | 43.0 |
| አፋር | - | 53.8 | - | 55?5 | - | 51.7 |
| አማራ | - | 55.5 | - | 58.5 | - | 38.3 |
| ኦሮሚያ | - | 53.1 | - | 57.5 | - | 32.9 |
| ሶማሊያ | - | 54.0 | - | 57.0 | - | 46.0 |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | - | 54.2 | - | 61.0 | - | 41.1 |
| ደቡብ ህዝቦች ክልል | - | 51.9 | - | 55.9 | - | 35.3 |
| ጋምቤላ | - | 53.9 | - | 54.2 | - | 45.7 |
| ሀረሪ | - | 52.9 | - | 58.3 | - | 58.0 |
| አዲስ አበባ | - | 33.4 | - | 60.0 | - | 33.2 |
| ድሬደዋ | - | 54.9 | - | 55.9 | - | 51.0 |

ምንጭ Zenaselassie Siyoum /2001/

ሰንጠረዥ 13 እንደሚያሳየው በ1999/2000 ከህዝቡ ገቢ ወደ 52.5% የሚጠጋው ለምግብ ይወጣ ነበር። የከተማው ነዋሪ ከገቢው ከ35.0% በታች የገጠሩ ህዝብ ደግሞ 57.3% ለምግብ ያወጣሉ። በአገር አቀፍ ደረጃ በየቤቱ ያለው የምግብ አማካይ ወጪ ባለፉት አምስት ዓመታት ለውጥ ሳያሳይ ቆይቷል። ይሁን እንጂ ለምግብ የሚወጣው ወጪ ድርሻ በገጠሩ እድገት አሳይቷል። ከአጠቃላዩ ወጪ በ1999/2000 በአዲስ አበባ የምግብ ፍጆታ 33.4% ድርሻ ሲኖረው ፣ በትግራይ ግን 60.4% ነበር። በአደጉት አገሮች አንድ ቤተሰብ ከአጠቃላይ ወጪው 20% ያነሰ የሚሆነውን ለምግብ እንደሚያውሉ ማስታወሱ ጠቃሚ ነው።

## የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

(Mekonnen Taddess et.al. (2001) የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኢኮኖሚክስ ዲፓርትመንት ከኦክስፎርድና በጉተምበርግ ዩኒቨርስቲ ከሚገኘው የአፍሪካ ኢኮኖሚ ጥናት ማዕከል ጋር በመተባበር በተወሰኑ ቤተሰቦች ላይ በማትኮር በተከታታይና በተለያየ ወቅት ያካሄዱትን ጥናት መሰረት በማድረግ በኢትዮጵያ ገጠርና ከተሞች በ1994, 1995 እና 1997 የነበረውን ድህነትና ያለመመጣጠን የሚያሳዩ ጠቃሚ መረጃዎች አቅርቧል።

ሰንጠረዥ 14 ፡- በኢትዮጵያ የነፍስ ወከፍ አጠቃላይ ፍጆታ ወጪ በብር

| | 1994 | 1995 | 1997 |
|---|---|---|---|
| ገጠር | 1089 | 1500 | 1377 |
| ከተማ | 1248 | 1320 | 1457 |
| አገር አቀፍ | 1113 | 1473 | 1389 |

ምንጭ፡ Mekonnen et al 2001/ በተወሰኑ ቤተሰቦች ላይ በተለያዩ ወቅቶች በተከታታይ በተካሄደው ጥናት ላይ በመመስረት ያዘጋጀው

ሰንጠረዥ 14 በኢትዮጵያ በ1997 ፣ 1389 ብር የነበረው የነፍስ ወከፍ የፍጆታ ወጪ በ1995 ከነበረው 1473 ብር ያነሰ ሲሆን ከ1995ቱ ብር 1113 ግን የበለጠ ነበር። በተወሰኑ ቤተሰቦች ላይ በተከታታይ በተለያዩ ወቅቶች የተካሄደው ጥናት በገጠር በ1995 ከነበረው የነፍስ ወከፍ የፍጆታ ወጪ በ1997 በልጦ እንደሚታይ ያሳያል። ይሁን እንጂ በገጠር የነበረው የነፍስ ወከፍ ወጪ ከ1995 - የ1997 እንሶ መታየቱንም ጠቁሟል።

ሰንጠረዥ 15 ፡- በኢትዮጵያ ያለው ድህነትን ያለመመጣጠን

| | 1994 | | | | 1995 | | | | 1997 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፍፁም ድህነት | በድህነት ውስጥ ያለ ልዩነት | የድህነት ክብደት | Gini | ፍፁም ድህነት | በድህነት ውስጥ ያለ ልዩነት | የድህነት ክብደት | Gini | ፍፁም ድህነት | በድህነት ውስጥ ያለ ልዩነት | የድህነት ክብደት | Gini |
| ገጠር | 41 | 16 | 8 | 39 | 37 | 16 | 9 | 56 | 36 | 13 | 6 | 43 |
| ከተማ | 39 | 15 | 8 | 44 | 38 | 15 | 8 | 45 | 36 | 15 | 9 | 49 |
| አገር አቀፍ | 41 | 16 | 8 | 39 | 37 | 16 | 9 | 54 | 36 | 13 | 6 | 43 |

ምንጭ፡ Mekonnen et al 2001/ በተወሰኑ ቤተሰቦች ላይ በተለያዩ ወቅቶች በተከታታይ በተካሄደው ጥናት ላይ በመመስረት ያዘጋጀው

ሰንጠረዥ 15 የገቢ ክፍፍል ያለመመጣጠንን ከሚለኩበት ስልቶች አንዱ በሆነው (Gini Coefficients) ተብሎ የሚታወቀውን መሰረት በማድረግ በ1994 የነበረው የገቢ ያለመመጣጠን በ1995 ወደ 54% ማደጉን ያሳያል። ይሁን እንጂ በ1995 በአገር አቀፍ ደረጃ የነበረው የገቢ ያለመመጣጠን በ1997 ትርጉም ያለው መሻሻል አሳይቷል። በሌላ በኩል ከ1994-1997 ጥናቱ በተካሄደባቸው ዓመታት በከተሞች የገቢ ያለመመጣጠን በ1995 በልጦ ሲታይ በ1997 ግን ከ1995ቱ ቀንሶ ይታያል። ከዚህ በተጨማሪ ሰንጠረዥ ፍጹም ድህነት በመቀነስ ላይ መሆኑን ያሳያል።

ሰንጠረዥ 16 ፦ በ1994 ከድህነት ወለል በታች የነበረበት ሁኔታ በ1997 ዝቅ ብሎ ይታያል። ይህ ሁኔታ በተወሰነ መልኩ ከነፍስ ወከፍ የፍጆታ ወጪ መጨመር ጋር ተያይዞ ተገልጿል። የፓነሉ መረጃ በሰንጠረዥ 16 እንደሚያመለክተው በተወሰኑ ቤተሰቦች ላይ በማትኮር በተከታታይና በተለያዩ ወቅቶች በተካሄደው ጥናት ከ1994-1997 ባሉት ጊዜያት ድህነት በከተማም ሆነ በገጠር በአጠቃላይ እየቀነሰ መምጣቱን ያሳያል። የድህነት ጥልቀትም በተመሳሳይ ወቅት በኢትዮጵያ የመቀነስ አዝማሚያ እንደነበረው ያመለክታል።

ሰንጠረዥ 16 ፦ በኢትዮጵያ በገጠሮችና በከተሞች ያለው ዝርዝር የድህነተ ገጽታ /1994-1997/

| ክልሎች | 1994 | | | 1995 | | | 1997 | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፍፁም ድህነት | በድህነት ጥልቀት | የድህነት ክብደት | ፍፁም ድህነት | ፍፁም ድህነት | የድህነት ክብደት | ፍፁም ድህነት | ፍፁም ድህነት | የድህነት ክብደት |
| እንሰት አብቃይ አካባቢዎች | 53.7 | 20.2 | 9.7 | 58.4 | 28.4 | 17.1 | 40.1 | 14.8 | 7.3 |
| ጥራጥሬ አብቃይ አካባቢዎች | 36.9 | 15.3 | 8.3 | 28.7 | 11.0 | 5.7 | 33.5 | 11.9 | 5.8 |
| አዲስ አበባ | 44.9 | 19.9 | 10.7 | 46.4 | 17.3 | 14.2 | 39.9 | 14.4 | 8.0 |
| አዋሳ | 59.1 | 21.4 | 12.9 | 40.4 | 14.2 | 6.5 | 33.0 | 16.7 | 10.4 |
| ጂማ | 36.7 | 12.1 | 5.8 | 25.6 | 10.6 | 5.3 | 42.9 | 15.3 | 6.9 |
| ደሴ | 36.9 | 14.1 | 6.8 | 37.2 | 14.6 | 7.0 | 37.8 | 14.4 | 7.6 |
| መቀሌ | 30.9 | 12.1 | 6.2 | 36.4 | 20.5 | 13.9 | 34.9 | 11.8 | 5.9 |
| ድሬደዋ | 18.2 | 5.8 | 2.2 | 28.6 | 8.6 | 3.6 | 36.6 | 12.3 | 5.8 |
| ባህርዳር | 26.2 | 9.4 | 5.3 | 26.1 | 9.0 | 5.0 | 24.0 | 8.7 | 4.1 |

## የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

ሰንጠረዥ 16 በግጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል ያለውን የድህነት ገፅታና በእንሰትና በእህል አብቃይ የሆኑትን ከተሞችን ለይቶ ነው የሚያቀርበው። ውጤቱም እህል አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩት ቁጥር ከ1995 ይልቅ በ1997 እንደጨመረ ያሳያል። እንሰት አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች ግን በ1995 የነበረው የድህነት ሁኔታ በ1997 እንደቀነሰ ይታያል። እርግጥ በከተሞች አካባቢ ከ1994 እስከ 1997 የድህነት ሁኔታ እየቀነሰ መጥቷል። ቢሆንም በጅማ ፣ በደሴ ፣ በመቀሌና በድሬዳዋ የድህነት ሁኔታ ሲጨምር ፣ ከ1994 እስከ 1997 በአዲስ አበባ ፣ በአዋሳና በባህርዳር የመቀነስ ሁኔታ ታይቷል።

የኢትዮጵያ መንግስት ነሀሴ 2000 ጊዜያዊ የድህነት ቅነሳ ሰነድ ማዘጋጀት ጀመረ። ይህ ሰነድ በ1995 በተለያዩ ሴክተር ፕሮግራሞች ተነሳሽነት ላይ የተመሰረተ ሲሆን የፍትህ ስርዓቱና የሲቪል ሰርቪሱን ማሻሻልን ፣ ስልጣን ከማዕከል ወደተለያዩ አካሉች የማከፋፈልና አቅም መፍጠር ፣ በመንግስታዊም ሆነ የግሉን ሴክተር አቅም (Capacity) ማጠናከር የመሳሰሉትንም አካትቷል። ሰነዱ ድህነትን በምግብ ዋስትና ያለውን ያለመመጣጎን ፣ ጤናን ፣ ትምህርትን ፣ የመጠጥ ውሃን አቅርቦትንና የመንገድን አገልግሎቱን የሚለኩ መመዘኛዎችን አካትቷል። ለ2000/01 እስከ 2000/03 የተዘጋጀው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂያዊ ሰነድ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ቅድሚያ ሰጥቷል።

### ግብርና

- የማይክሮ ፋይናንስ ተበዳሪዎችን በ20% መጨመር ፣
- የልማት ጣቢያ ሰራተኞችን በዲፕሎማ ደረጃ የሚያስመርቁ ተቋሞች መክፈት ፣
- ለማዳበሪያ አቅርቦት የውጭ ድጋፍን እስተማማኝ ማድረግ ፣
- የምርት ግብዓቶችና ውጤቶችን ገበያ ለማጠናከር መንገዶችን መስራትና ማስተሳሰር፣
- የሠዶን ዋስትና ጥናት ማጠቃለል።

### የግል እርሻ

- በመንግስት እጅ ያሉትን እርሻዎች ከመንግስት ይዞታ ማውጣት ፣
- የመሬት ሊዝ ፖሊሲ መስመር ማስያዝ ፣

### የምግብ ዋስትና

- በ1998 የምግብ ዋስትናን ፕሮግራም ላልታቀፉት ክልሎች ተመሳሳይ ፕሮግራም ማዘጋጀት ፣
- የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በየክልሉ የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ማድረግ፣

## ህዝባዊ አገልግሎት

- ለትምህርት ፣ ጤናና ግብርና በፕሮግራምም ሆነ በበጀት አመዳደብ ቅድሚያ መስጠት ፣
- በመደበኛና በካፒታል ወጪዎች አንድ ወጥነት ያለው አሰራር መከተል ፣

## ስልጣን ማከፋፈል

- በወረዳ ደረጃ በጀታቸውን በራሳቸው የማከፋፈል ስልጣን መስጠት

ከዚህ በተጨማሪ የምግብ አቅርቦትና ስርጭትን ለመጨመር የኢትዮጵያ መንግስት በ1996 የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ነደፈ። የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ በሁለት ዓላማዎች ላይ የተመሰረተ ነበር። እነዚህም ፡-

ሀ) የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥና በዓለም አቀፉ የእህል ገበያ ኢትዮጵያ የተሻለ ዕድል እንዲኖራት ለማድረግና ፣

ለ) የምግብ ዋስትና ስትራቴጂው በምግብ ራስን መቻል የሚያረጋግጥ እንዲሆን ማድረግ ይህስትራቴጂ የሚከተሉት 3 ጉዳዮችን ያካትታል። እነዚህም የኢኮኖሚ ዕድገት ማፋጠንና የስራ ዕድል በራስ መወሰን ፣ ድሆችንና ለጥቃት የተጋለጡ ወገኖችን የሚያቅፍና በነዚህ ላይ ያነጣጠረ እንዲሆን ማድረግና የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎችን ለመቋቋም የሚያስችል አቅም መፍጠር ናቸው። በዚህ የፌደራል መንግስት ስትራቴጂ ላይ በመመስረት የአማራ ፣ የደቡብ ህዝቦች ፣ የኦሮሚያና የትግራይ ክልሎች የ5 ዓመት የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ነድፈው የክልላቸውን ችግር ለማቃለል ተንቀሳቅሰዋል።

በድህነት ላይ ተፀእኖ ያላቸው ጉዳዮች

- የድህነት ምክንያቶች
- ድህነትን የሚወስኑ ጉዳዮች
    - የተለያዩ የቤተሰብ አባላት የትምህርት ሁኔታ
    - የቤተሰብ ስፋትና ስብጥር
    - መሰረታዊ ማህበራዊ የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች ማግኘት
    - በቤተሰብ የተያዙ ጥሪቶች
    - የቤተሰብ ሃላፊዎች ብሄራዊ ተዋፅኦና ፆታ
    - የመኖሪያ ቦታ መለያየት
    - የስራ ዘርፍ

## 5. ድህነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ መነሻዎችና የአፈፃፀም ስልቶች

### 5.1 የድህነት መንስኤዎች

ከድህነት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ከተለያየ አቅጣጫ መመዘን የሰዎችን ጥሪት ጥሪታቸው የሚያስገኘውን ገቢና በዚህ ውጤት ዙሪያ ሊኖር የሚችለውን ውጣ ውረድ እንድንገነዘብ ይረዳል። የሰዎች ጥሪት በሚከተሉት አይነቶች ሊገለፁ ይችላሉ።

- ሰብአዊ ሃብት ይኸውም ሊሠራ የሚችል ጤናማ አካልና ሞያ ፣
- እንደ መሬት ያሉ ተፈጥሮዊ ሃብት ፣
- መሰረታዊ የመሰረተ ልማት አውታሮች አገልግሎት የማግኘት እድል ፣
- የገንዘብ ሃብት የቁጠባና የብድር አገልግሎት ማግኘት መቻል ፣
- ማህበራዊ ሀብቶች ማለትም ፣ በችግር ግዜ ሊደርሱ የሚችሉ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረቱ ማህበራዊ ትስስሮችና በሃብት ላይ የመወሰን አቅም ፣

የማንኛውም ጥሪት ገቢ የሚገኘው በገበያ ላይ ብቻ ሳይሆን ዓለማዊ፣ አገራዊና ከባቢያዊ ጉዳዮች በገበያው ላይ በሚኖራቸው ተፅእኖ ጭምር ነው። ከዚህም በላይ ማንኛውም ገበ በገበያው ባህሪ ብቻ ሳይሆን በመንግስታዊና ማህበራዊ ተቋሞች እንቅስቃሴ ይወሰናል። የሃብት ባለቤትነትም ሆነ ከዚህ የሚገኘው ገቢ በኢኮኖሚያዊ ባህሪው ብቻ ሳይሆን እንደ መሰረታዊ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳይ መታየት ይኖርበታል። የግል ባለቤትነት የሚወሰነው በሚኖረው ህግና ደንብ መሠረት ነው። ግልጽ በሆኑ ወይም ባልሆኑ በፆታ ወይም በዘር ወይም በማህበራዊ ቦታ በሚደረጉ ተፅእኖዎች የንብረት ባለቤትነት እድል ሊታጣ ይችላል። እስካሁን የተገለፁትን ፅንሰ ሃሣቦች በሚመከተለው ስዕላዊ መግለጫ የበለጠ ለማብራራት ይሞክራል።


በገቢ የሚታየው ተለዋዋጭ ሁኔታ ለድህነት ትልቁ መንስኤ ነው። ለገቢ ማሽቆልቆል በገበያ የሚታዩ ያለመረጋጋቶች ብቻ ሳይሆኑ የአየር ጠባይ ለውጥና እንዲሁም በአንዳንድ ህብረተሰቦች እሰቸጋሪ የፖለቲካ ሁኔታዎችም አስተዋፅኦ አላቸው። ድንጋጤ የጤናን ሁኔታ እንደሚጎዳ ሁሉ ያልተረጋጋ ሁኔታም የገቢ ማሽቆልቆልን የጥሪት ዋጋ መቀነስን ተፈጥሯዊና የሰው ሃብቶችን መጎዳትንና የቁጠባ ገንዘብ መሬቆትን ሊያስከትል ይችላል።

## የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

የገጠሩ ድሃ የሚያካሂደው ባለችው ትንሽ መሬትና በማያስተማምን ዝናብ ላይ ተመስርቶ ነው። የገጠሩ ድሃ በመደበኛ ሆነ መደበኛ ባልሆነው የኢኮኖሚ ዘርፍ የስራ እድል ማግኘት አጠራጣሪ ው። ሁሉም ድሆች ለወባና ለሳምባ ነቀርሳ ለመሳሰሉት አደገኛ በሽታዎች የተጋለጡ ናቸው።

የህግ የበላይነት ያለመኖር፣ ከጥቃት የሚከላከል ዋስትና ማጣት፣ ድሃውን ዝቅ አድርጎ ማየትና ከመንግስትፃ ሆነ ከህዝብ ባለስልጣናት ጋር ያለው ግንኙነት ጤናማ ያለመሆን በሙሉ

figure 1. በኢትዮጵያ የገጠር ድህነት መንስኤዎች



በድሃው ላይ ተጨማሪ ቀንበር ይጭኑበታል። ድሆች አዲስ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ከሚፈጥረው እመቺ ሁኔታ ተጠቃሚ የማይሆኑ ከመሆናቸውም በላይ ከአካባቢያቸው ወጣ ብለው የመስራት ዋስትና የላቸውም። በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ባለስልጣኖች በሚያደርሱባቸው የተለያዩ ጫናዎች ምክንያት ህገባዊ ጉዳዮች ላይ እንዳይሳተፉና ፍላጎታቸው እንዳይደመጥ ይሆናሉ። ስለዚህም ተጠያቂነት የሌላቸውና ተገቢውን ግዴታቸውን የማይወጡ ተቋሞች ለድሃው ህብረተሰብ ችግሮች መባባስ ተጨማሪ ምክንያቶች ናቸው።

## 5.2 በኢትዮጵያ ድህነትን የሚወስኑ ጉዳዮች

በአብዛኛው በኢትዮጵያ የድህነት ምክንያት ይሆናሉ ከሚባሉት ምክንያቶች ውስጥ ፦

ሀ. የአንድ ቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ ፣

ለ. የቤተሰብ ስፋትና ስብጥር ፣

ሐ. የቤተሰቡ ሃላፊ ፆታና እድሜ ፣

መ. መኖሪያ አካባቢ (ገጠር/ከተማ) ጥቂቶቹ ናቸው።

Decon (1999,2000) Mekonnen et.al (2001) በኢትዮጵያ ያካሄዱት ጥናት እንደሚያመለክተው የበሬ ባለቤት መሆን ለድህነት የመዳረጉን እድል እንደሚያጠበው ይገልፃሉ። ለገበያ የሚቀርበው እንደ ቡና፣ ጫት እና ጤፍ የቅባት እህሎች የሚያመርቱ አርሶ አደሮችም ለድህነት የመጋለጥ እድላቸው ከሌላው ያነሰ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ያለው የቤተሰብ ሃላፊ ፆታው ምንም ይሁን ምን ከድህነት የማምለጥ እድሉ ብዙም አስተማማኝ አይደለም።

የቤተሰብ ሃላፊ እድሜ በጨመረ ቁጥር የቤተሰቡ ለድህነት የመጋለጥ ሁኔታም እንደዚሁ ይጨምራል። ሴት የቤተሰብ ሃላፊ የሆነችበትና የጥገኛው ብዛት በርካታ የሆነበት ቤተሰብ ለከፍተኛ ድህነት ይጋለጣል። በከተማም ቢሆን የቤተሰብ ስፋትና የቤተሰቡ ሃላፊ የእድሜ ሁኔታ ልክ እንደገጠሩ ለበለጠ ድህነት ያጋልጣል። ቢሆንም በከተማ የቤተሰቡ ሃላፊ ወንድም ይሁን ሴት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ያላቸው ከሆኑ ለድህነት የመጋለጥ እድላቸውን ይቀንሰዋል። እንደሚጠበቀው ሁሉ በከተሞች አካባቢ ጊዜያዊ የቀን ሰራተኞችና ስራ አጦች የድሃው ህብረተሰብ አካሎች ናቸው።

በዛ ያሉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የህዝብ ቁጥር ከማህበረ ኢኮኖሚያዊ እድገትና ከድህነት ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዳለው ያሳያሉ። ከፍተኛ የጥገኝነት ድርሻ ባላቸው አገሮች የህዝብ ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ የአገሪቱን ቁጠባ በማናጋት ኢኮኖሚውን እንዲያሽቆለቁል በማድረግ

በመጪዎቹ ዓመታትም የሰው ሃይል እድገት (Human development) ለማረጋገጥ የሚያወጣው ኢንቨስትመንት ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርገዋል።

በገቢ ማነስ የሚታየው ድህነት ከአካባቢ መበከል ጋር ተያያዥነት አለው። ድህነት የተፈጥሮ ሀብትን በመቀነስ እንደገና የድሃውን ህብረተሰብ መራር ህይወት ያባብሰዋል። ለም የእርሻ መሬት ለማግኘት ፣ ለግጦሽና ለማገዶ ተብሎ የሚካሄደው የደን ጭፍጨፋ የእርሻ አስተማማኝነትን የሚጎድና በውጤቱም የገጠሩን ድሃ ለበለጠ ችግር የሚዳርግ ይሆናል።
በኢትዮጵያ የሚታየው የህዝቡ ቁጥር መጨመር በደጋው አካባቢ የሚኖረውን አርሶ አደር የመሬት እጦት እያባባሰው ነው። ከአንድ ሄክታር በታች መሬት ያላቸው አብዛኛው አርሶ አደሮች በአንድ ሰብል ብቻ እንዲያተኩሩ በመገደዳቸውና የተለያዩ ሰብሎች ባለመጠቀማቸው ምክንያት መሬቱ ለምነት ስለማይኖረው የሚገኘውን ምርት ዝቅተኛ ያደርገዋል። በገጠር የሚገኙት ድሆች ለድርቅ በተጋለጡ አካባቢዎች የሚገኙ ፣ ከብት አርቢዎች ፣ ከግማሽ ሄክታር ያነሰ መሬት ያላቸው ወይም መሬት አልባዎቹ ናቸው።

መኮንን (2001) ባካሄደው ጥናት ጥገኛ የበዛበበት ቤተሰብና በሴት የሚመራ ቤተሰብ በድህነት የሚኖር እንደሆነ ያመለክታል። በገጠር አርሶ አደሮች የሚያመርቷቸው የሰብል ዓይነቶች ድህነት መጋለጥ ጋር ተያያዥነት አላቸው። ለምሳሌ እንሰት አምራቾች ጥራጥሬ ከሚያመርቱ አርሶ አደሮች ይበልጥ ለድህነት የተጋለጡ ናቸው። በከተሞችም በግል ድርጅቱ ተቀጥረው ከሚሰሩት ይልቅ የቀን ሰራተኞች ለበለጠ ድህነት ይጋለጣሉ።

Mekonen et.al. (2001) ጥናት ቀደም ብለው በተጠቀሱት መረጃዎች አንፃር የገቢ ያለመመጣጠን እንደሚታይ ያመለክታል። የገጠርም ሆነ የከተማ የገቢ ያለመመጣጠን ተቀራራቢ ናቸው። ምንም እንኳ ጥናቱ የሚያሳየው መረጃ የኢኮኖሚ ማገገም መኖሩን ቢያመለክትም በገጠርና በከተማ የሚታየው የገቢ ያለመመጣጠን እያደገ መምጣቱን ያሳያል። ይህ እውነታ የሚያመለክተው ነገር ቢኖር በኢትዮጵያ ያለው ድህነት በኢኮኖሚ እድገት ብቻ ሊፈታ እንደማይችል ነው።

በ1989 እና በ1995 በ15 መንደሮች የተካሄደው ጥናት (Dercon 1999) የሚያመለክተው ነገር ቢኖር የልማት አውታሮች አገልግሎት ማግኘት፣ የትምህርት አገልግሎት መሻሻልና የመሬት ባለቤትነት በድህነት የሚገኙ ቤተሰቦች ከችግሩ መውጣት ጋር ከፍተኛ ቁርጠኝነት እንዳላቸው አሳይቷል። በሌላ በኩል ሴት የቤተሰብ ሃላፊዎችና በእድሜ የሸመገሉ ሰዎች ከወጣቱና

## የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

ከወንዱ በባሰ ሁኔታ ከድህነት ጋር እንደሚኖሩ ጥናቱ ያመለክታል፡፡ Dercon (2000) ያደረገው ጥናት እንደሚያሳየው በፍጆታ የሚታየው ድህነት እየቀነሰ የመምጣት ምልክት እንዳለውና በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶችና በመሠረታዊ የጤና አገልግሎት መሻሻል እንደሚታይ ይገልፃል፡፡ Dercon and Kirshman (1998) እንደሚያሳዩት ትርጉም ያለው የሰው ሃይልና የንብረት አቅም ኖሯቸው ለትራንስፖርት አገልግሎትና ለከተሞች ቅርበት ያላቸው ቤተሰቦች የድህነት ደረጃቸው ዝቅ ያለ እንደሆነና በተነፃፃሪ የተሻለ ኑሮ እንደሚኖሩ ያመለክታል፡፡ የተሻለ የሰው ሃብት (Human Resource) ያላቸውና ለትራንስፖርት ለከተማ ቅርበት ያላቸው ቤተሰቦች በተለያዩ የምርት ወቅቶች የሚያጋጥማቸው የችግር ውጣ ውረድ ሻል ያለ እንደሆነ ታይቷል፡፡ እንደመሬት፣ በሬ ያሉ ንብረቶች ያሏቸው ቤተሰቦች በተሻለ ሁኔታ ከድህነት የመውጣት አቅም አላቸው (Dercon 2000)፡፡

## በድህነትን ለመቀነስ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች

- ድህነትን የማጥፊያ መንገዶች በዓይነታቸው የተለያዩ ናቸው።
- እድገትና የሥራ እድል መፍጠር ፡-

- ➔ የግል ባለሃብቶች ኢንቨስትመንት ፣
- ➔ አነስተኛ የብድር አገልግሎት በቀላሉ የሚገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፣
- ➔ ምርትና ምርታማነትን ማሻሻል ፣
- ➔ ኤክስፖርትን ማበረታታት ፣
- ➔ የድሃውን የጥሪት መሠረት መገንባት ፣
- ➔ የሃብት አለመመጣጠን ማሻሻል ፣
- ➔ ድህነት በሚያጠቃቸው አካባቢዎች የመሠረተ ልማቶች ማስፋፋት

ድህነትን ለማጥፋት በሚደረገው ፈርጀ ብዙ ጥረት የሚካተቱ ፓሊሲዎች ፣ መተግበር

- እድገትን የሚያበረታታና የሚያግዝ የመንግስት አስተዳደር መፍጠር ፣
- የሥልጣን ክፍፍልና የህዝብ ተሳትፎን ማበረታታት ፣
- የጾታ እኩልነትን ማበረታታት ፣
- ማህበራዊ መሠናክሎችን መዋጋት/መታገል ፣

መረጋጋትና ደህንነት ፡-

- እደጋ (ችግር ወይም ጉዳት) ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎች የማቋቋሙ ፕሮግራሞችን መንደፍ ፣
- ምርቶች ገበያ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማበቻቸት ፣
- በጠቅላላ ኢኮኖሚው ላይ መናጋትን ለመከላከል የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን መንደፍ ፣
- በማህበረሰቡ ችግር ወይም ጉዳት የሚያስከትሉ ሁኔታዎች ለመቆጣጠር የሚያስችል ብሄራዊ ሥርአት ማውጣት ፣
- የርስ በርስ ግጭት ለማስወገድ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ፣
- ኤች አይቪ ኤድስ በሽታን ለማጥፋት መዝመት ፣

ለሰም ለቀፍ ተግባሮች ህዝቡን በሚጠቅም ሁኔታ መተግበር

## 5.3 በድህነትን ለመቀነስ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች

የድህነት ምክንያቶችና መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጭ መንገዶች በአይነት የተለያዩ ናቸው። ይህም የተለያዩ ፖሊሲዎችን የሚያካትት ሰፊ እይታ ያለው ማእቀፍና የእነዚህ የተለያዩ ፖሊሲዎች አፈፃፀምን በአግባቡ ማቀናጀት ይጠይቃል። የአንድ ሰው ጤና እንዲጠበቅ ማድረግ አጠቃላይ ደህንነቱን ከማሻሻል በተጨማሪ ሠርቶ ተጨማሪ ገቢ የማግኘት አቅሙንም ያሳድጋል። የትምህርት እድልን ማስፋፋትም በተመሳሳይ ለተሻለ የጤና አጠባበቅና ለተጨማሪ ገቢ መንገድ ይከፍታል። ድህነት ለተለያዩ አደጋዎች በቀላሉ የሚያጋልጥ ስለሆነ ድሃ ሰዎችን ከነዚህ አደጋዎች ራሳቸውን እንዲከላከሉ ማገዝ በአንድ በኩል ከተጠቂነት መንፈስ ከማዳከም ያለፈ ፋይዳ አለው። የላቁ አደጋዎች ሊያስከትሉ የሚችሉ ሆኖም የላቀ ጠቀሜታ ያላቸው ሥራዎችን ለመሥራት ያሉትን እድሎች በድፍረት እንዲጠቀሙባቸው ያስችላቸዋል። ድምፃቸው ከፍ ብሎ እንዲሰማና ተሳትፎአቸው እንዲጠናከር ማድረግ የመገለል ስሜታቸው ከማስወገዱም በተጨማሪ ችግሮቻቸውን መሠረት ያደረገና ከፍላጎታቸው ጋር የሚጣጣም ተገቢ የሆነ የጤናና የትምህርት አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል። በነዚህ በተጠቀሱት ጉዳዮች መሃከል ያለውን ተያያዥነትና ተደጋጋፊነት በውል መረዳት ድህነትን ለማስወገድ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ለመቅረጽም ሆነ ለተግባራዊነታቸው ይጠቅማል (World Bank 2001) ድህነት ላይ ትኩረት ሰጥቶ የሚከናወን ተግባር ሰዎች ኑሯቸው ለማስቀጠል የሚያስችላቸው ጥሪት/ሃብት/ እንዲኖራቸው ማስቻልን ያካተተ መሆን አለበት። በሌላ አነጋገር ድህነት ሰዎች የእነዚህ ሃብቶች ባለቤት ወይም ተጠቃሚ ለመሆን ባለመቻላቸው የሚገለጽ የመብት/የይገባኛል ጉዳይ/ ጭምር ነው።

**ድህነትን ለማጥፋት የሚከናወኑ አማራጭ ተግባራት የሚመዘኑባቸው መስፈርቶች ፦**

ሀ. ከማክሮ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አላማዎች ጋር ያላቸው መጣጣም ፣

ለ. ፕሮግራሙ ድሆችን ተጠቃሚ የሚያደረግ መሆኑን ማረጋገጥ ፣

ሐ. በቀላሉ ሊፈፀም የሚችል መሆኑና አፈፃፀሙ የተወሳሰበና አስቸጋሪ ያልሆነ ፣

መ. ውጤቱ ከሚያስፈልገው ወጪ ጋር የሚመጣጠን ወይም ወጪውን የሚያካክስ መሆኑ ፣

ሠ. ቀጣይነቱ እና ፣

ረ. የአመራር ብቃት መኖር ናቸው፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የድህነት ሁኔታ በጣም አሳሳቢ ነው። ከገቢ ማጣት የሚመጣው ድህነት ከፍተኛ ነው። የተመጣጠነ ምግብ እጦት ችግር እየተባባሰ

መጥቷል። የህፃናት ሞትና ሰዎች የሚኖሩበት አማካይ እድሜ መቀነስ እየተባባሱ የመጡ ችግሮች ሆነዋል። ለዚህም ኤድስ አስተዋፅኦ አድርጓል። የትምህርት ሽፋን አነስተኛ ነው። ባለፈር ዓመታት የተገኘው ውጤትም ቢሆን ቀደም ሲል የነበረውን ማሽቆልቆል ለማካካስ በሚያስችል ደረጃ ወይም ቀጣይነት የተከናወነ አይደለም። (Mekonn Tadese ct-al (2001) ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ድህነት ምንጭ በአገሪቱ ኢኮኖሚ አደረጃጀት መሆኑን ይገልፃል። ስለሆነም የኢኮኖሚው አደረጃጀት በመሠረቱ ሳይቀር ይህንን ግዙፍ የድህነት ችግር መቅረፍ አይቻልም። ድህነት የመቀነስ ሂደት ሊያፋጥኑ የሚችሉ የተለያዩ አማራጮች አሉ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የድህነት ሁኔታ ላይ ቀጥተኛ ጫናና ውጤት ከሚኖራቸውና ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ተግባራት ውስጥ የሰው ሃይል ልማት ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት፣ የተሻሻሉ ኢኮኖሚያዊ የመሠረተ ልማት አውታሮች መዘርጋት፣ የገበያ ማበረታቻዎች ማድረግና የሰው ሃይል ገበያን ማሻሻል የሚጠቀሱ ናቸው። የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች በሦስት ሰፋፊ የተግባር ሊያተኩሩ ይችላሉ።

## 5.3.1 ኢኮኖሚያዊ እድገትና የሥራ እድል መፍጠር

ሀ. ውጤታማ የሆነ የግል ባለሀብቶች ኢንቨስትመንትን ማበረታታት ፦

ኢንቨስትመንትና ቴክኖሎጂያዊ ማሻሻል ለብዙ የሥራ እድሎች መፈጠርና ለተሻለ ገቢ ዋነኛዎቹ መነሻዎች ናቸው። የግል ኢንቨስትመንት የሚያድግበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የግል ኢንቨስተሮች ለውድቀትና ኪሳራ የሚዳርጓቸውን ሁኔታዎች የሚቻለው ያህል ለመቀነስ መጣር ያስፈልጋል። እነዚህም የተረጋጋ የፊዚካልና የገንዘብ ፓሊሲ፣ የኢንቨስትመንት የፋይናንስ ሥርአትና ግልፅ የሆነና የግልፅነት አሠራር የሰፈነበት የንግድ ሁኔታ መፍጠር ናቸው። በተጨማሪም የህግ በላይነትን ማስፈን ፀረ ሙስና እርምጃዎች በመውሰድ ሙስናን መዋጋት፣ ለሃገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ባላቸው ፋይዳ ላይ በመመስረት ለትላልቅ ኢንቨስትመንቶች ማካካሻዎችና ድጎጎዎች የሚያገኙበት ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ ለኢኮኖሚው እድገትና የስራ እድል ለመፍጠር ይረዳሉ።

ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች በገበያው ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲሳተፉ የሚያግዙ ልዩ እርምጃዎችን መውሰድ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም

እነዚህ ድርጅቶች በቢሮክራሲያዊው አሠራርና ተገቢ ያልሆነ ጥቅምና ችሮታ ለማግኘት የገንዘብ አቅሙና ግንኙነቱ ባላቸው ድርጅቶች ጥቃት በቀላሉ የሚጠቁ በመሆናቸው ነው። እነዚህ ልዩ እርምጃዎች ብድር የሚያገኙበትን መንገድ ማቃለልና ለገበያ ፣ ምርትን ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ /ለማድረስ/ ያሉ ወጭዎችን ለመቀነስ የመረጃ አገልግሎት በቀላሉ የሚጠቀሙበትንና በሰፊው የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ የኤክስፖርት ምርቶች የንግድ ትርዒት ማዘጋጀት በዘመናዊ የንግድ ሥራ ሥልጠና መስጠትና የመልክአ ምድርና የቦታ ርቀት ችግሮችን ለማቃለል መጋቢ መንገዶችን መሥራትን ያካትታሉ። የንግዱን አጠቃላይ ሁኔታ ለማሻሻል መወሰድ ካለባቸው ተቋማዊ ማሻሻያዎች institutional reforms መሃከል informal Sector /መደበኛ ባልሆነ አግባብ በሚከናወኑ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያለውን ቁጥጥርና ገደብ መቀነስ /በተለይ ደግሞ ሴቶችን የሚጎዱ/የመሬት ይዞታና ምዝገባ ሥርአት ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ጉድለቶች/ትናንሽ ኢንቨስትመንቶችን የሚያቀጭጩ የመሬት ይዞታ ስርአቶችን መለወጥ እንዳንዶቹ ናቸው። የሰው ሃይል ክህሎትን ለማሻሻል የመገናኛና ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮች ለማስፋፋት የመንግስት ኢንቨስትመንት አስፈላጊ ነው።

## የማይክሮ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥን ምቹ ማድረግ

ማይክሮ ፋይናንስ ማለት የብድር ቁጠባ ኢንሹራንስ ወዘተ የመሳሰሉትን የፋይናንስ አገልግሎቶች የሃብት እጦት ላለባቸው ግን አምራች ለሆኑ በገጠርና በከተማ ለሚገኙ ብዙሃን እንዲሁም ጥቃቅን አነስተኛና መለስተኛ ለሆኑ የንግድ ተቋማት ወጪና ውጤቱ ተመጣጣኝ በሆነና ቀጣይነት /ዘላቂነት/ ባለው መንገድ ማቅረብ ነው። በኢትዮጵያ ዋናው የማይክሮፋይናንስ አላማ በድሆች ኑሮ ላይ አዎንታዊ የሆነና በተጨባጭ ሊለካ የሚችል ለውጥ ማምጣት ነው።/ድህነት ቅነሳ/ ማይክሮ ፋይናንስ ድሆች ራሳቸው የሚያከናውኗቸው አምራችና አትራፊ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን በመደገፍና የገቢያቸውን ደረጃ እንዲያሳድጉ በመርዳት ድህነት ሊያስከትላቸው የሚችሉትን ችግሮች ያቃልላል። ይህንን የፋይናንስ አገልግሎት በቀጣይነት ማቅረብ አንድ የድህነት ቅነሳ ዋነኛ መሣሪያ ቢሆንም ከድህነት ጋር ለተያያዙ ችግሮች ሁሉ ብቸኛ መፍትሄ አይደለም።

ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ፡-በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ መሠረታዊ የሆነ ለውጥ የማምጣቱ ጉዳይ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልገው ነው። ምክንያቱም ከአፍሪካ 70% ከኢትዮጵያ ደግሞ 85% የሚሆነውን የሥራ ሥምሪት የሚሸፍንና አብዛኛው ድሃ ህዝብ የሚኖረው በገጠሩ በመሆኑ ነው። መሠረታዊ ለሆነ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ መሠረት በሆኑት የግብርና ምርትና

ምርታማነት ላይ ቀጣይነት ያለው እድገትና ከፍተኛ መሻሻል ማምጣት ካልተቻለ ድህነትን የማጥፋቱ ጥረት ሊሳካ አይችልም። ከዚህ ጋር በተያያዘ በገጠር የተንሰራፋውን ድህነት ለመቀነስ የሚነደፍ እስትራቴጂ አነስተኛ ይዞታ ባላቸውና በገጠር ድሃ ሴቶች ላይ ያተኮረና የግብርና ምርትን በማሳደግ ላይ ያለመ መሆን አለበት። በኤስያና በላቲን አሜሪካ አገሮች የታየውን አይነት አረንጓዴ አብዮት ለማቀጣጠል ለግብርና ምርምርና ለግብአቶች ስራ ሥርጭት የመንግስት ድጋፍ ወሳኝ ጉዳይ ነው። ሌላው ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ ጉዳይ ከግብርና ውጭ ያሉ (ግብርና ነክ ያልሆኑ) ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን በማበረታታትና በማገዝ መሬት አልባ የሆኑና ከኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች በተለያየ ምክንያት የተገለሉትን የተሻለ ገቢ እንዲያገኙ ማስቻል ነው።

## የግብይት አድማስን ወደ አለም ገበያዎች ማስፋት

የአለም ገበያዎች በግብርና በኢንዱስትሪና በአገልግሎት መስኮች ለገቢና የሥራ እድል ማደግ ሰፊ በር ይከፍታሉ። በከፍተኛ ደረጃ የገቢ ድህነትን ለመቀነስ የቻሉት ሃገሮች በሙሉ የአለም ንግድን በአግባቡ የተጠቀሙ ናቸው። የረዥም ግዜ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት የእውቀት ሽግግር የመሳሰሉ ጠቀሜታዎች እግረ መንገዱን ሊያመጣ ይችላል። የአጭር ግዜ የካፒታል ፍሰት ደግሞ አስቀድሞ ሊገመት የማይችሉና ወደ ቀውስና ውድቀት በፍጥነት ሊለወጡ የሚችሉ ሁኔታዎች ውስጥ ሊያስገባ ይችላል። ስለዚህም ፖሊሲዎች እነዚህን ጉዳዮች ነጣጥለው ለየብቻቸው ማየት አለባቸው።

## የድሆችን ጥሪት መገንባት

ድሆች በባለቤትነት ሊይዟቸው ወይም ሊጠቀሙባቸው የሚችሉትን ሰብአዊ፣ ቁሳዊ ተፈጥሮአዊና ገንዘባዊ ሃብቶች መፍጠር በሦስት አቅጣጫ ላይ ያተኩሩ ተግባራትን ማከናወንን ይጠይቃል። በመጀመሪያ መሠረታዊ የሆኑትን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች አቅርቦት በማስፋትና በፍጆታ በኩል ያለውን ማነቆ በማላላት የመንግስት ወጪ በተለይ የድሆችን ችግር በማቃለል ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ያስፈልጋል። መልካም አስተዳደር በማስፈንና ገበያዎችን ባግባሙ በመጠቀም ጥራት ያለው አገልግሎት ማቅረብ ሁለተኛ ጉዳይ ነው። ሶስተኛ ድሃው ህብረተሰብ የሚፈልገውን አገልግሎት በመምረጥ በማስፈጸምና በመከታተል ላይ እንዲሳተፍ በማድረግ የአገልግሎት ሰጪ አካላትን ተጠያቂነት ማረጋገጥ ነው።

## በጾታዎች ጎሳዎች ዘሮችና በማህበራዊ ክፍፍሎች መሃከል ባለ የሃብት አለመመጣጠን ላይ ትኩረት አድርጎ መንቀሳቀስ

በማህበራዊ ቦታ ላይ የተመሠረቱ የሃብት አለመመጣጠንን ትኩረት ሠጥቶ መሥራት በብዙ ማህበረሰቦች አስፈላጊ ተግባር ነው። ፖለቲካዊናና ማህበራዊ ጉዳዮች የሚፈጥራቸዉ አስቸጋሪ ሁኔታዎች በዚህ ረገድ ለውጥ ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት አንዳንድ ግዜ የሚደናቅፉ ቢሆንም በተግባር ውጤት ሊያስገኙ የሚችሉ የአሰራር ዘዴዎች በእብነት መጥቀስ ይቻላል። ይኸውም የድሆችን ተሳትፎ በማጠናከር ተቋማዊ ለውጥ በማምጣተና የተለያዩ አይነት የመንግስት ወጪዎች አዋህዶ ለዚህ አላማ በመጠቀም ውጤት ማምጣት ይቻላል። ከዚህም ሌላ በቦታ ርቀትና በባህላዊ ምክንያት ከኢኮኖሚው እንቅስቃሴ የተገለሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች ችግር ለመፍታት መንቀሳቀስ ይፈልጋል።

## መሠረተልማት አውታሮችና እውቀት ድሆች ወደሚኖሩባቸው አካባቢዎች ማድረስ

ትራንስፖርት መገናኛዎች ት/ቤቶች የጤና አገልግሎትና የኤሌክትሪክ ሃይል እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የመሠረተ ልማት አውታሮች ራቅ ባሉ ድሃው ህብረተሰብ በሚኖርባቸው አካባቢዎች መዘርጋት ይኖርባቸዋል። በኢትዮጵያ ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ የተለያዩ የፖሊሲ ማሻሻያዎችና እርምጃዎች ተግባራዊ ሆነዋል። ኢኮኖሚው በነፃ ገበያ መርህ እንዲቀሳቀስ የልማት ድርጅቶች ወደግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ እንዲዛወሩ የዋጋ ቁጥጥር እንዲነሳ የተወሰዱት እርምጃዎች የኢንቨስትመንት ሁኔታ እንዲሻሻል አድርገዋል። የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ የሚመራ ግብርና-መር የኢንዱስትሪ ልማት በሚል የሚታወቅ ስትራቴጂ ተነድፎ ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል። የኤክስፖርት ማስፋፊያ ኤጀንሲ እድገትና ልማትና ለማበረታታት ከተቋቋሙት ድርጅቶች አንዱ ነው። የመንገድ ፣ የጤና፣ የትምህርት የሌሎችም ክፍለ ኢኮኖሚው የልማት ፕሮግራሞች ተቀርፀው ተግባራዊ ሆነዋል። ሆኖም እነዚህን ፕሮግራሞች ተግባራዊ ለማድረግ የተደረገው እንቅስቃሴ በተቋማዊ ፣ ሰብአዊ በመሠረተ ልማታዊና የፋይናንስ አቅም ውስንነት የተነሣ በሚገባ የተፈለገውን ያህል ውጤታማ አልሆኑም። በነዚህ እርምጃዎች በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ የተከናወኑት የግል ኢንቨስትመንት ሥራዎች በአብዛኛው በዋና ከተማውና በጥቂት የከተማ ማዕከሎች የተወሰኑና የኤክስፖርቱን መሠረት ለማስፋት የተደረገው ጥረት ባለመሳካቱ አሁንም ዋነኛውና ወሳኙ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኘው ምርት በዚያው በኋላ ቀር ቴክኖሎጂ የሚመረተው ቡና ነው። የምርታማና ተስማሚ ቴክኖሎጂዎች እጥረት በመኖሩ የግብርና ምርትና ምርታማነትን አሁንም በዝቅተኛ

ደረጃ ላይ የሚገኝና የአየር ሁኔታ መለዋወጥ ለሚያደርሰው ጫና በከፍተኛ ሁኔታ የተጋለጠ ነው።

### 5.3.2 የድህነት ቅነሳ ዓላማን ማካተት ያለባቸው ፖሊሲዎች

የመንግስትንና የማህበራዊ ተቋማትን እንቅስቃሴ ለማሻሻልና ለማጠናከር የሚወሰዱ ተግባራዊ እርምጃዎች ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግና ኑሮን ለማሻሻል በሚደረግ ጥረት ላይ ቢሮክራሲያዊና ማህበራዊ ማነቆዎችን በማቃለል እድገትና የሃብት መመጣጠን ለማምጣት ያግዛሉ። ከዚህ አንፃር የሚካተቱ ፖሊሲዎች የሚከተሉትን ሊመለከት ይችላል።

- **ድሆችን የሚያካትት ልማት ለማምጣት የሚያስችል ፖለቲካዊና ህጋዊ መሠረት መጣል።**

የመንግስት ተቋማት ለሁሉም ዜጋ ግልፅና ተጠያቂ መሆን አለባቸው። ማለት ግልፅ አሠራር ያላቸው ተቋማት ውሣኔዎች የሚሰጡበትና አፈፃፀማቸውን የሚከታተሉበት አግባብ አሳታፊና ዲሞክራሲያዊ አሰራርን የተከተለ እንዲሁም በህግ ፊት የሁሉን ዜጋ እኩልነት በሚያከብርና ኢኮኖሚያዊ እድገትን የሚያበረታታ የህግ ሥርአት መኖርን ያጠቃልላል። የዲሞክራሲ መኖር መሰረታዊ የሆኑትን ሃሳብን በነፃ የመግለፅና መረጃ የማግኘት መብር ለመጎናፀፍ ብቻ ሣይሆን ለኢኮኖሚ እድገትም እጅግ አስፈላጊ ነው።

- **የኢኮኖሚ እድገትና ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍልን የሚያረጋግጥ አስተዳደር መመስረት፣**

ከሙስና ወይም ከቢሮክራሲያዊ ወከባ በፀዳ አሠራር ፖሊሲዎች የሚያስረጽሙ የመንግስት አካላት ለህዝቡ የሚሰጠው አገልግሎት የተሻለና ያለው መሆን ይኖርበታል። ይህ አሰራር ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ እድገት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። ተስማሚ የሆኑ የአፈፃፀም ብቃት ማበረታቻዎች መኖር ለተጠቃሚዎች ፍላጎት ምላሽ የሚሰጥና ተጠያቂ የሆነ የመንግስት አካል ለመፍጠር አስፈላጊ ናቸው። የበጀት መረጃ ማግኘት ተጠቃሚውን የሚያሳትፉ የበጀት አመዳደብና የተለያዩ መንግስታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት ብቃት ደረጃ የመስጫ አግባቦች ቢኖሩ ዜጎች መንግስትን በፍላጎታቸው

የመቅረፅና የመከታተል አቅማቸውን ከማሳደጉም በላይ ሙስና ሊፈፀም የሚችልባቸውን አጋጣሚዎች የሚቀንስና ሊከሰት የሚችልበት መጠን ያሳንሰዋል። አስተዳደራዊ መዋቅሩና ሌሎች እንደ ፓሊስ የመሳሰሉት አካላት አደረጃጀትና አሠራር በማሻሻል ለድሃ ሰዎች ፍላጎቶች ምላሽ ሰጪነታቸውና ተጠያቂነታቸውን ማጠናከር በድሃው ህዝብ የእለት ተለት ኑሮ ላይ ከፍተኛ ሊያመጣ ይችላል።

➢ የሥልጣን ክፍፍልና ማህበረሰባዊ እድገት ማበረታታት ፣

የሥልጣን በየደረጃው ወደታች መከፋፈል አገልግሎት ሰጪ አካላትን ወደ ህዝቡ የሚያቀርብ በመሆኑ አገልግሎት አሠጣጡ የመቆጣጠር አቅማቸውን የማጠናከር እድል ይሰጣቸዋል። ይህም አካባቢያዊ አቅምን ማጠከርና የገንዘብ ሀብትን ወደነዚህ አከባቢዎች ማሰራጩት ይጠይቃል። በተጨማሪም ገንዘቡም ሆነ ሥልጣኑን በአካባቢው የሚታወቁና ንቁ የሆኑ እንዲሁም የመናገር ችሎታ ባላቸው ጥቂት ሰዎች እንዳይነጠቅ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም ሲባል ለምሣሌ በትምህርት ቤት አስተዳደር ወላጆች እንዲሳተፉ በማድረግ በገጠር መጠጥ ውሃና በመስኖ ሥራዎች የተጠቃሚዎች ማህበር በማቋቋምና በመሳሰሉት መንገዶች ወደ ታች በተዋረድ የተሰጠውን ሥልጣን ህዝቡ እንዲጠቀምበትና የሃብት አጠቃቀምና የፕሮጀክቶች አፈፃፀም በህዝቡ ምርጫና ተሳትፎ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል።

➢ ለፆታ እኩልነት የሚደረግን ትግልን ማገዝ ፣

በፆታዎች መሃከል የሚታየው በእኩልነት ላይ ያልተመሠረተ ግንኙነት ሰፋ ባለመልኩ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉት እምነቶችና እሴቶች አካል ነው። የፆታዎች እኩልነት በራሱ የሚመረጥና የሚፈለግ ቢሆንም በተጨማሪም ድህነትን ከመቀነስ አኳያ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች አሉት። በትምህርትና በጤና መስኮች መሻሻሎች የታዩ ቢሆንም አሁንም ብዙ መሥራት ይጠበቃል እስከ አሁን በተገኘው ልምድ ይህን ችግር ለመፍታት የተለያዩ ፓለቲካዊ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃዎች አዋህዶ መወሰድ አስፈላጊ ነው።

➢ ማሕበራዊ መሰናከሉችን ማስወገድ

ድሆች ከድህነት ለመውጣት ማህበራዊ እምነቶችና የግንኙነት መረቦችን /መስመሮች/ እንደ ቁልፍ መሣሪያዎች ይጠቀሙባቸዋል። ስለሆነም ከነዚህ የድሆች ማህበራዊ መዋቅሮች ጋር በመሥራት እነሱን መርዳት እንዲሁም ከሌሎች አገናኝ ድርጅቶች ሰፊ

ገዘያዎችና የመንግስት ተቋማት ጋር እንዲተሳሰሩ በማድረግ እንዲጠናከሩ ማድረግ ጠቃሚ ነው። ይህን ማድረግ የህግ የቁጥጥርና ተቋማዊ ሁኔታዎች ድሆችን ለሚወክሉ ስብስቦች አመቺነት በሚፈጥር መንገድ ማሻሻልን ይጠይቃል።

ህዝቡ የራሱን ጉዳይ በራሱ እንዲወስንና እንዲሣተፍ ለማስቻል ያለሙ ዲሞክራሲን የማጠናከር ፣ ሥልጣን ወደ ክልሎች የማከፋፈል ፣ የኘሬስ ነፃነትና የፆታ እኩልነት እውን እንዲሆኑ የተለያዩ እርምጃዎች ተወስደዋል። ሆኖም ከ90% የሚበልጡት የፌዴራልና የክልል ምክር ቤቶች መቀመጫዎች በአንድ ፓርቲ የተያዙ መሆናቸው እነዚህ እርምጃዎች ያመጡትን ጠቀሜታ ውስን አድርጎታል። የመንግስትን ሥራዎች ለመቆጣጠርና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ድምፅ እንዲሰማ ለማድረግ የሚያስችሉ የሲቪክ ማህበራት ማቋቋም አልተቻለም። ፖሊሲዎች ከመውጣታቸው በፊት መደበኛ በሆነና ባልሆነ መንገድ ህዝባዊ ውይይትና ክርክር እንዲደረግባቸው የሚያስችሉ አሰራሮች ውስን ናቸው። ህዝቡ በሙስናና ቢሮክራሲያዊ አሠራሮች ያማርራል። የዳኞች እጥረትም የፍትህ ሥርዓቱን ደካማ አድርጎታል። ይህ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ድህነት ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረት ይወስነዋል።

### 5.3.3 መረጋጋትና ዋስትና ፣

የተሻለ ዋስትናን ለማረጋገጥ በአጠቃላዩ ኢኮኖሚ ወይም ክልል ደረጃ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉ እርምጃዎች መወሰድና ድሆች በግለሰብ ደረጃ ሊገጥሙአቸው የሚችሉ ኢኮኖሚያዊ መናጋቶች መቋቋም እንዲችሉ መርዳት ያስፈልጋል።

ሀ. **ድሆች ለችግር የሚያጋልጣቸው ሁኔታዎች ለመቋቋም የሚያስችላቸውን ስልት መንደፍ** ፣ እንደ አንድ አገር ተቋማዊ አቅምና ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ አደጋዎች አይነት ማህበረሰቦችና ቤተሰቦች እነዚህን አደጋዎች ለመቋቋም የሚያስችሏቸው የተለያዩ እርምጃዎች መውሰድ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

በአነስተኛ ደረጃ የሚከናወኑ የኢንሹራንስ ፕሮግራሞች ለድሃ ቤቶች ከሚሰጡ የብድር አገልግሎት ጋር ተጣጥመውና ተደጋግፈው ሊካሄዱ ይችላሉ። በአንድ አካባቢ ወይም በአገር ደረጃ የሚያጋጥሙ አደጋዎችን ለመቋቋም በመንግስት ድጋፍ የሚከናወኑ ህዝቡ የሚሳተፍባቸው የልማት ሥራዎች ሊስፋፉ ይችላሉ። በምግብ

እህልና በሌሎች ሃብቶች ድጋፍ የሚፈፀሙና በህዝቡ ፍላጎት መሠረት የተቀረፁ ፕሮጀክቶች እደጋን በመቋቋም ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ።

ለ. **ድሆች ምርቶቻቸውን በተሻለ ዋጋ ለመሸጥ የሚችሉበትንና ገበያ የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር፣** ድሆች የሚያጋጥማቸው ችግር የማምረት ብቻ ሣይሆን ላመረቱት የተሻለ ገቢ የሚያስችላቸው ዋጋ ማግኘትም ነው። አነስተኛ አምራቾች ምርታቸውን የሚሸጡት በየግላቸው ለሚያገኙት ነጋዴ ከሆነ ሁልጊዜም የተሰጣቸው ዋጋ ከመቀበል ውጪ ምርጫ አይኖራቸውም። ስለዚህም በጋራ ቢደራጁ ምርቶቻቸውን አቀይተው የተሻለ ዋጋ በሚገኝበት ግዜና ቦታ በመሸጥ የበለጠ ጥቅም ማግኘት ይችላሉ።

ሐ. **በማክሮ ደረጃ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተፈጥሮአዊና ኢኮኖሚያዊ አደጋዎች /መናጋቶችን/ ለመከላከል ፣** አስቀድሞ ለመዘጋጀትና ለመቋቋም የሚያስችል ፕሮግራም መንደፍ የፋይናንስና የንግድ ሁኔታዎች መዛባት የሚያመጡ አደጋዎች ተቋቁሞ ለማለፍ ትክክለኛ የሆኑ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ፖሊስና ጠንካራ የፋይናንስ ሥርዓት መሰረት ናቸው።

መ. **እድገትን የማይገቱና ማህበራዊ አደጋዎችን ለመቋቋም የሚያስችሉ ብሄራዊ ሥርዓቶችን መዘርጋት ፣** ማህበራዊ አደጋዎችን ለመቋቋም የሚያስችሉ ብሄራዊ ሥርአቶች መዘርጋት በአለም ደረጃ አስፈላጊነቱ እየታወቀ መጥቷል። ሆኖም በአንድ በኩል እድገትን የማይቀይዱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ድሃውን የሚጠቅሙ አድርጎ መቅረጽ አስቸጋሪ ወይም ፈታኝ ሥራ ነው። ለዚህ እብነት የሚሆኑ ድሆች ላልሆኑ ዋስትና የሚሰጡና ለድሆች ማህበራዊ የጡረታ ዋስትናን የሚካተቱ እንዲሁም ለሥራ የሚያተጉ ሥርአቶች መዘርጋት ይቻላል። እንደዚህ አይነት ሥርዓቶች የሚሰጡትን ጥቅም በተሟላ መልክ ለማግኘት ኢኮኖሚዎች እነዚህን ሥርዓቶች ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገው ተቋማዊ አቅም እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

ሠ. **ለርስ በርስ ግጭቶች ማስወገድ ትኩረት መስጠት ፣** የርስ በርስ ግጭቶች በሚከሰቱበት ግዜ በድሆች ላይ እጅግ በጣም አውዳሚ ጉዳት ያደርሳሉ። የሰው ህይወት ከማጥፋት በተጨማሪ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ውድመትና አሉቃቂ የሆነ የስነልቦና ማህበራዊ ጠባሳ ጥለው ያልፋሉ። ጥምር የሆኑ ተቋሞችን ማጠናከር ማለትም የውሁዳንን መብቶች መደገፍና ቅራኔዎች በሰላማዊ መንገድ የሚፈታባቸው

ተቋማዊ መሰረት እንዲኖር ማድረግ የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው የሚያረጋግጡ መረጃዎች አሉ። ሁሉን በሚያካትቱና በሚያሳትፉ ፓሲቲካዊና ሲቪክ ማህበራት ግጭቶች እንዳይከሰቱ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እርስ በርስ እንዲገናኙ የሚጠቅሙ ናቸው።

ረ. **የኤች አይቪ/ኤድስ ወረርሽን መዋጋት** ፣ የበሽታውን ሥርጭት ለመከላከል፣ ህይወት የሚያራዝም መድሃኒት በማሰራጨትና በበሽታው የተጠቁትንም ለመንከባከብ ጠንካራ አመራርና ማህበራዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል። ይህም ስለፆታ ግንኙነትና ስለ ኤች አይቪ/ኤድስ በግልፅ መነጋገር ነውር የሚያደርገውን ባህል ፊት ለፊት መጋፈጥ በዚህ በሽታ በቀላሉ ለሚጠቁ እንደ ሴተኛ አዳሪዎች ላሉ የህብረተሰቡ ክፍሎች መረጃና ድጋፍ መስጠትና በበሽታው ለሚሰቃዩት ሰብአዊ ርህራሄ ያልተለየው እንክብካቤ ማድረግን ያካትታል። በዚህ ረገድ በቁርጠኝነት መሥራት ከተቻለ የሚገኘውን ውጤት ምን ያህል የተሳካ ሊሆን እንደሚችል ኡጋንዳና ሴኔጋል ጥሩ አብነቶች ናቸው።

የተሻለ መረጋጋትና ደህንነት በኢትዮጵያ ለማረጋገጥ ያለው ወናው ማነቆ ተቋማዊና የሃብት አቅም ውሱንነት ነው። በድርቅ የሚጠቃው የህዝብ ቁጥር ከአመት አመት እየጨመረ መጥቶ ከ8-10 ሚሊዮን በመድረሱ ሃገሪቱ በራሷ አቅም ብቻ ልትቋቋመው ከምትችለው በላይ ሆኗል። በአስቸኳይ የእህል እርዳታ ድጋፍ የሚካሄዱ የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤና ወይም የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ ፕሮግራሞች ዘላቂነት አጠያያቂ እየሆነ መጥቷል። በበቂ የፋይናንስና የሰው ሃይል ድጋፍ የሚካሄዱና እነዚህን ሃብቶች በጠንካራ የባለቤትነት ስሜት ይዞ የሚንቀሳቀስ ህዝብ አለመኖር ዋናውዎቹ እንቅፋቶች ሆነዋል። ጥርት ባለመንገድ የተቀመጠ የመሬት ይዞታ መብት አለመኖሩ መሬት ለማግኘት ከመሬቱም የተሻለ ምርት እንዳይገኝ የበኩሉን ሚና እየፈጠረ ይገኛል። በቂ የገበያ/ዋጋ ማረጋጊያ ስልት ባለመዘርጋቱ ገበሬው በደህና ጊዜ ለሚያገኘው የምርት ጭማሪ የተሻለ ገቢ ማግኘቱ ቀርቶ የምርቶቹ ዋጋ በጣም ስለሚያሽቆለቁሉ ለግብአቶች ግዥ የተበደረውን መመለስ የማይችልበት ደረጃ ሲደርስ ይስተዋላል።(ምሣሌ በዚህ አመት) የወባ በሽታ የሚከሰትበት ድግግሞሽ በአየር ሁኔታ ለውጥ ምክንያትና በሽታውን ለመቆጣጠር ያለው ተቋማዊ አቅም በቂ ባለመሆኑ ምክንያት እየጨመረ የበሽታው ስርጭትም እየሰፋ የሚያደርሰውም ጉዳት የዚያኑ ያህል እየከፋ መጥቷል። አሁን ባለው ሁኔታ ኤች አይ ቪ/ኤይድስ በየትኛውም ደረጃ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ፈጥሯል።

### 5.3.4 በአለም አቀፍ ደረጃ ሊወሰዱ የሚችሉ/የሚገባቸው/ እርምጃዎች

ደህንነትን በፍጥነት ለማቃለል በአካባቢና በሃገር ደረጃ የሚወሰዱ እርምጃዎች ብቻ በቂ አይደሉም። ድሃ አገሮችና በነዚሁ አገሮች የሚገኙ ድህነት የሚያጠቃቸው ህዝቦችን የሚጠቅሙ በአለም አቀፍ ደረጃ በተለይም በኢንዱስትሪ በበለፀጉት አገሮች ሊወሰዱ የሚችሉ የተለያዩ እርምጃዎች አሉ። ከነዚህም ውስጥ የዕዳ ቅነሳ እንዲሁም ከነዚህ ጋር አብሮ የሚሄደው በእርዳታ አማካኝነት የሚደረገው የልማት ትብብር የላቀ ውጤት ማስገኘት ይችላሉ።

ዓለም አቀፋዊ ሃይሎች ድሆችን ለመጠቀም በአለም አቀፍ ደረጃ እርምጃዎች ሊወሰዱባቸው የሚገቡ አምስት ቁልፍ ጉዳዮች አሉ።

- ታዳጊ አገሮች ምርቶቻቸውን በበለፀጉት ሃገሮች ገበያዎች መሸጥ የሚችሉበት መንገድ ማመቻቸት ማስፋት ፣
- የኢኮኖሚ ቀውሶች የሚደርሱትን አደጋ መቀነስ ፣
- በአለም አቀፍ ደረጃ በስፋት በህዝብ የሚፈለጉና ድሃውን ህዝብ የሚጠቅሙ የሸቀጦች ምርት ማበረታታት ፣
- የድሃ አገሮች ድምፅ በአለምአቀፍ መድረኮች እንዲሰማ ማድረግና
- በአለም አቀፍ እርዳታ አሰጣጥ ላይ ያለውን ጥርጣሬ ማስወገድ ፣

# 6. ድህነት ለመቀነስ የሚያስችሉ ፓሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች የማስፈፀሚያስልቶች

## 6.1 ድሃውን ለይቶ የማወቅ ሥራ

ድሃውን መለየት

- ሰፋ ባለ መስፈርት መለየት
- ጠበብ ባለ መስፈርት መለየት
- ድህነትን የመለያ አግባቦች

  - ህዝቡ የሚሳተፍበትን ድሃውን የመለየት ሥራ ፣
  - ራስ በራስ የሚደረግ የመለየት ሥራ ፣
  - በገበያ አማካኝነት የሚደረግ መለየት ፣
  - አስተዳደራዊ የመለየት ሥራ ፣
  - አሳታፊ በሆነ መንገድ የሃብት ደረጃ ማውጣት ፣
  - ስታስቲካዊ አግባቦች ፣

ጠበብ ባሉ መስፈርቶች የመለየት ሥራ የሚያጋጥሙት ችግሮች ፦

- ድሃ ያልሆኑ እንደ ድሃ የሚለዩበት ሰፊ እድል መኖር ፣
- ውጤታማ የሆነ የመለየት ሥራ የሚያስከትለው ከፍተኛ ወጪ፣
- ትጋትን የሚቀንሱ የመለየት ስልቶች፣

## 6.1.1 ሰፋት ባለውና ጠበብ ባሉ መስፈርቶች መሠረት የሚፈጸም ድሆችን የመለየት ሥራ (Targeting)

የኢኮኖሚ እድገት ለደሀነት ቅነሳ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ይታመናል። ነገር ግን እስካሁን የኢኮኖሚ እድገት በማምጣት የተቃኙ ፖሊሲዎች በሃብታሙና በድሃው ላይ የሚያስከትሉት ውጤት በተለይም ድህነትን በመቀነስ አኳያ አመርቂ ውጤት አላሳየም። ስለሆነም የልማትና እድገት ንድፈሃሳቦች በሃብት ክፍፍል ላይ ትኩረት ሳያደርጉ ቆይተዋል። ሆኖም በዚህ ምእተ አመት ማገባደጃ ለሃብት አለመመጣጠን ፣ ለድህነት ቅነሳና ድሆችን የመለየት ሥራ የሚሰጠው ትኩረት የጨመረ መጥቷል። እንዲያም ሆኖ በነፃ ገበያ ወደሚመራ የኢኮኖሚ ልማት የሚደረግ ሽግግር ድህነትን በማቃለል የሚያስገኘው ውጤት በጥርጣሬ የሚታይ ነው። ድህነትን ለመቀነስ ባለው ፍላጎት ምክንያት ይህን ዓላማ ለማሳካት መንግስታዊ በሆኑና ባልሆኑ ድርጅቶች አማካኝነት የተለያዩ ተግባራት መፈፀም አስፈላጊ ሆኗል። እዚህ ላይ ዋናው ጥረት የኢኮኖሚ ዕድገት በመገኘቱ ወዲያው ከእድገቱ ተጠቃሚ መሆን የማይችሉት ድሃ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሃብት ክፍፍል/ዝውውር/ በማድረግ ተጠቃሚ ለማድረግ ነው። ከዚህም በላይ ድሆችን የመለየቱን ሥራ ከአጭር ግዜ አኳያ የሚጎዱ ክፍሎችን (ከረዥም ጊዜ አኳያ ሊጠቀሙ ቢችሉም) ከጉዳት ለመጠበቅ ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል። ይህ ድሆችን የመለየት ሥራ ውሱን የሆነውን የመንግስት ሃብት ድሆች ወይም ተጨባጭ በሆነ የኢኮኖሚ እድገት ተጠቃሚ ባልሆኑ ቤቶች ላይ እንዲውል ያደርጋል።

### ድሆችን የመለየት ሥራ በሁለት አግባብ ሊፈፀም ይችላል።

ሀ. ሰፋ ባለ መልክ ድሆችን የመለየት ሥራ ፦

በዚህ አግባብ እያንዳንዱን ድሃ ግለሰብ ለመድረስ ጥረት አይደረግም። በአጠቃላይ ድሆችን በጣም ይጠቅማሉ ተብለው ለሚታመኑ ተግባራት አስፈላጊውን ወጪ በመመደብ በነዚህ ተግባራት ውጤት ድሆች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ይህ ድሆችን የመለየት አግባብ የሚመሠረተው የመንግስት በጀት ተመድቦላቸው ከሚፈፀሙ ተግባራት ውስጥ የተወሰኑት ድሆችን ከሌሎች ተግባራት በበለጠ ወይም በተለየ ይጠቅማሉ በሚለው መርህ ላይ ነው። ለምሣሌ መሠረታዊ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለመሥጠት የሚደረጉት ወጪዎች ብዙውን ግዜ ድሆችን ሲጠቅሙ ይታያሉ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለማስፋፋት የሚመደብ ወጪ በአብዛኛው ከድሃ ቤተሰብ የመጡ ተማሪዎችን ይጠቅማል። ከድሃ ቤተሰብ የመጡ ተማሪዎች በአመዛኙ ሁለተኛና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ለመከታተል አቅሙም ዕድሉም ስለሌላቸው ትምህርታቸውን ስለሚያቋርጡ እነዚህ የትምህርት ደረጃዎችን ለማስፋፋት የሚደረግ ኢንቨስትመንት ድሆችን በብዛት ሊጠቅም አይችልም። በተመሳሳይ መንገድ የጤና አገልግሎት

ለማስፋፋት በሚደረግ ትኩረት ለጤና ኬላዎች ትኩረት መስጠት በሃብት ደረጃ ልዩነት ባያደርግም በተነፃፃሪ ድሆች መሠረታዊ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ሰፊ እድል ይሰጣቸዋል። ሆስፒታሎች አገልግሎት የሚሰጡት በአብዛኛው የተሻለ ገቢ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ነው። የተሻለ የጤናና መሠረታዊ ትምህርት የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦትና መሠረታዊ የመሠረተ ልማት አውታሮች መኖር ድህንነት ይቀንሳል። ምርታማነታቸውንና ገቢያቸውንም ሊያሳድግ ይችላል።

ይህ ሰፋ ያለ ድሆችን የመለየት ስራ ቀደም ሲል የተገለፁት ጠቀሜታዎች ቢኖሩትም የድህነት ቅነሳ ስልት ተደርጎ መወሰድ የለበትም ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ። የሚያቀርቧቸው ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

- ሀ. ከፍተኛ ወጪ ይጠይቃል ፣
- ለ. ለመሠረታዊ አገልግሎቶች የሚሰጠው ድጎማ ድሃ ያልሆኑትን ሊሸፍን ይችላል፤
- ሐ. በድህነት/የእስከፊነት/ ደረጃዎች መሃከል ልዩነት እያደርግም ስለዚህም በድህነት ከፋኛ ለተጠቁት ቅድሚያ አይሰጥም እና
- መ. የተወሰኑ ክፍሎች በጅምላ በሚሰጡ መሠረታዊ ማህበራዊ አገልግሎቶች ወይም ሌሎች ወጪ የሚመደብላቸው ተግባራት የማይሸፈኑ ፍላጎቶች ሊኖራቸው ይችላል። በሌላ አነጋገር በአካባቢ የተወሰኑና የተለዩ ችግሮችን ለይቶ በመፍታት ደካማ ሊሆን ይችላል።

## ለ. ጠበብ ባለ መልክ የሚፈፀም ድሆችን የመለየት ሥራ :-

ይህን አግባብ በመደገፍ የሚቀርበው መሠረታዊው ክርክር ይህ አግባብ ሃብትን በቁጠባ ለመጠቀም ያስችላል። በዚህ አግባብ መሠረት የሚነደፉ ፕሮግራሞች ጥብቅ በሆነ መስፈርቶች ድሆችን በመለየት የሚጠቅሙና ድሃ ያልሆኑትን የሚያገሉ በመሆኑ አላስፈላጊ ወጪን እጅግ ይቀንሳሉ የሚል ነው። ሆኖም መሠረታዊ የትምህርትና ጤና አጠባበቅ አገልግሎትና የውሃ አቅርቦት ለሁሉም መዳረስ አለበት የሚል ጠንካራ ክርክር መኖሩን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ከአቅርቦቱ በኩል ሲታል ደግሞ የመንግስትና መነግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ያላቸው ሃብት ውስን በመሆኑ ድሆችን የመለየት ሥራ አስፈላጊነትና ፋይዳ በጣም ግልፅና ቀጥተኛ ያደርገዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ድሆችን የመለየትና ተግባራዊ የማድረግ ሥራ የሚጠይቀው ወጪ ከፍተኛ ነው። ብዙዎቹ የሴፍቲኔትና ፀረ ድህነት ፕሮግራሞች ዓላማቸው ድሃውን በተለይ መርዳት ቢሆንም በመጨረሻ ውጤታቸው የጠቀሙት ድሃ ያልሆነው ነው። /leakage/ አንዳንድ ሰዎች ድሆችን በመለየት ሥራ ምትክ ሌሎች መንገዶችን መጠቀም ይቻላል። የሚል ሙግት ያቀርባሉ። ለምሣሌ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ለድሆች ሳቢ የተሻለ ገቢ ላላቸው ሳቢ ያልሆኑ አገልግሎቶችን በማዘጋጀት መስጠት ይችላሉ። ሌሎች ደግሞ በአንድ አካባቢ ያሉት የመጨረሻ ድሃ ሰዎችን ለመለየት የሚያስችል የአሠራር ስልት ሊኖር አይችልም ወይም ከፍተኛ ወጭ ይጠይቃል በማለት የሚሟገቱ አሉ።

### 6.1.2 ድሆችን የመለየት ስልቶች

#### በህዝቡ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ ድሆችን የመለየት ሥራ ፦

ይህ አሰራር ህዝቡ ራሱ በመለየቱ በመሳተፍ የምግብ እህል እርዳታ የብድር አገልግሎት የመሳሰሉትን ማግኘት ያለባቸውን ሰዎች እነማን እንደሆኑ በመወሰን ያሳትፋል። ይህ የአሠራር ሥልት የገጠር ሸንጎዎች በተነፃፃሪ ጠንካራ በሆኑበት በትግራይ ክልል ሰሜናዊ ኢትዮጵያ/በስፋት ይጠቀሙበታል። ህዝቡ በተሰበሰበበት ግልጽ ውይይት ተደርጎ የመለየቱ ሥራ ይከናወናል።

ራስን በራስ መለየት ፡ -

በነዚህ ፕሮግራሞች የምግብ እርዳታ ለማግኘት ወይም መንግስት በሚያካሂዳቸው የልማት ሥራዎች ለመቀጠር አልያም አነስተኛ ብድር የማግኘት ዕድል ለሁሉም ማለትም ድሃ ለሆኑትም ላልሆኑትም ይሰጣል። ሆኖም እነዚህ ፕሮግራሞች የሚሰጡአቸው አገልግሎቶች መጀመሪያውኑ ሲቀረፁ በባህሪያቸው ድሃ ያልሆኑትን እዳያበረታቱ ይደረጋል። ለዚህ ጥሩ አብነት የሚሆነው በማይክሮፋይናንስ ተቋማት የሚሰጠው አነስተኛ የብድር መጠን ነው። የብድሩ አነስተኛነት ድሃ ያልሆኑትን በሂደቱ ለመሳተፍ ፍላጎት እንዳይኖራቸው ያደርጋቸዋል።

### በገበያዎች አማካኝነት የሚፈፀም የመለየት ሥራ ፦

የተመረጡ ሸቀጦችን ዋጋ አቅርቦትና ፍጆታ በሚፈልገው መንገድ ከፍና ዝቅ በማድረግ በቀጥታ በገበያ ውስጥ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት ነው። ለዚህ እዛነት የሚሆኑት የተመረጡት ሸቀጦች የድሆች ምግብ የዋጋ ድጎማና የማረጋጋት እርምጃዎች መወሰድ ናቸው። ይህ የአሠራር ሥልት የተወሰኑ ክፍሎችን ብቻ ለመጥቀም ታስቦ የሚደረግ አይደለም።

### አስተዳደራዊ የመለየት ሥራ ፦

ወደ ህዝቡ የቀረቡ የመንግስት ተቋማት (እንደ ቀበሌ ያሉት) እና ከዚያ ከፍ ያሉ የመንግስት ሃላፊዎች በአንድ ላይ ሆነው ለተለያዩ አገልግሎቶች ማለትም በምግብ እህል እርዳታ በሶፍቲኔትና በምግብ ለሥራ ፕሮግራሞችና በአነስተኛ ብድር አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ ሰዎች የሚለዩበትን መመዘኛ ያወጣሉ። እነዚህ መመዘኛዎች የቤተሰቡ የሃብት ደረጃ (መሬት፣ ከብት ወዘተ) ገቢ የቤተሰብ ብዛት በአባወራው ላይ ጥገኛ የሆኑት ቁጥርና የመሳሰሉት ናቸው። በዚህ የአሠራር ሥልት የተወሰነ ክፍተት መኖሩ አይቀርም። ቢሆንም በዚህ ክፍተት የሚፈጠረው የሃብት ብክነትና ከዚህ የተሻለ የአሠራር ስልት በሚጠይቀው ተጨማሪ ወጪ መሃከል ያለው ልዩነት መመዘን አለበት። አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን በሃገሪቱ በድርቅ የተጠቁ አካባቢዎችን ለመለየት የሚጠቀምበት የምርት ሁኔታ የሚገመግምበት ዘዴ ጂኦግራፊያዊ/ከባቢያዊ/ የመለየት ሥራ ምሣሌ ነው።

### የአንድ ቤተሰብ መኖሪያ አጥር ግቢ በመመልከት የመለየት ስራ ፦

ይህ ስልት ብዙውን ግዜ የቤቶቹን ጣራ በመመልከት የቆርቆሮ ከሆነ ከሣር ክዳን ባለው ቤት ከሚኖሩት የተሻሉ ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል። ይህ ስልት ቀላል ወይም ፈጣንና የሚያሳስቱ ሊሆን ስለሚችል እንደ የመለየት ሥራው አላማ በጥንቃቄ መጠቀሙ ይበጃል።

### ተሳትፎአዊ የሃብት ደረጃ የመስጠት ስልት ፦

እዚህ ላይ የደረጃ አሰጣጡ በአካባቢው የሚኖሩ ተሰባስበው መመዘኛ ሊሆኑ ይችላሉ ብለው የሚያምኑባቸውን መስፈርቶች አውጥተው የድህነትና ሃብት ደረጃ የሚሰጡበት አሠራር ነው። የመስክ ሠራተኛ ድጋፍ ባይለያቸውም ነጥብ ወይም ደረጃ የሚሰጡት የአካባቢው ነዋሪዎች ናቸው። ይህ ስልት በሰነሰ ሃሳብ ደረጃ ቀላልና ግልፅነት ያለው ነው። እነሽን

የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

ኬይድ ኢትዮጵያ በሚንቀሳቀስባቸው ማለትም በዳሉቻና ኮይሻ የልማት ፕሮግራሞች ተጠቅሞበታል። በነዚህ የፕሮጀክት አካባቢዎች የሚካሄዱትን የምግብ ዋስትና ፕግራሞች ለመገምገም የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ እድሉ ነበረኝ። በኔ የግምገማ ውጤት ይህ ስልት ድሃ የሆኑትንና ያልሆኑትን በመለየት ውጤታማ ነበር። የዚህ ስልት ውሱንነት በዋንኝነት ይህን ሂደት የሚያግዙ ወይም ለሂደቱ ሁኔታዎችን የሚያመቻቼ ብዙ ሠራተኞች ማስፈለጉና ይህን የደረጃ አሠጣጥ ለማካሄድ በተሳታፊ መሃከል መተማመን ለመፍጠር ረዥም ግዜ መጠየቁ ናቸው። በተጨማሪ ይህን ለመፈፀም የወጣው ወጪ ከፍተኛ ነበር።

ስታስቲካዊ አግባቦች ብዙ አይነት ቢሆንም እነዚህን ስልቶች በኢትዮጵያ ሁኔታ በተለይም በመንደር ወረዳና ዞን ደረጃ ለመጠቀም የሚጠይቀው ገንዘብና አቅም የለም። እነዚህ ስልቶች የእርዳታና ሌሎች ፕሮግራሞቸ ለታለሙት ህብረተሰብ በትክክል መተቀማቸውን ለማረጋገጥ የምርምርና ጥናት ባለሞያዎች ሰዎች የሚጠቀሙባቸው ናቸው። ወልዳይ/1998/ ባካሄደው ጥናት Logit Model በመጠቀም በዳሉቻ ያደረገው ግምገማ ውጤት እንደሚያሳየው በፕሮጀክቱ ያሉ ድሆች የሚከተሉት መለያ ባህርያት ይታዩባቸዋል።

ሀ. እርጅና ፣

ለ. በሴቶች ብቻ የሚመሩ ቤተሰቦች ፣ (አባወራ አልባ)

ሐ. ማንበብ መፃፍ የማይችሉ/መሃይሞች ናቸው/ ፣

መ. ከፍተኛ የቤተሰብ አባላት

ሠ. መሬት አልባ ወይም እጅግ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ፣

ረ. በጣም ጥቂት የከብት ቁጥር ፣

ሰ. ዘመናዊ ግብአቶች ጭራሽ አይጠቀሙም ወይም እጅግ በጥቂቱ ፣

ሸ. የቤተሰብ ምጣኔ አይጠቀሙም። እንዲያውም ሆን እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ድሃ የሆኑትንና ያልሆኑትን ለመለየት እነዚህ ስልቶች እንደግብ የተያዙትን የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞች ከመፈፀማቸው በፊት ለመጠቀም አስቸጋሪ ነው።

### 6.1.3 ጠበብ ባለ መልክ በሚካሄድ የመለየት ሥራ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች

1. **ድሃ ያልሆኑትን የመጥቀም ሰፊ ክፍተት :-**

ሀ. ይህ ክፍተት ድሆች ያገኙትን ሁሉ ድሃ ካልሆኑት ጋር የሚካፈሉ መሆናቸው ባህላዊ ከሆነ ጉዳይ ሊመነጭ ይችላል።በሌላ አነጋገር በአማራ

ትግራይና ሌሎች ክልሎች የሚገኙው ድሃ ያልሆነው ድሃ እንደ ሆኑት ሁሉ የምግብ እርዳታ ያገኛል ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ድሃ የማይባሉት በአካባቢው ያሉ ድሆችን በችግር ግዜ በመርዳትና ከጉዳት በመጠበቅ ቀልጣፋና በቀጣይነት እንደ ሴፍቲ ኔት የሚያገለግሏቸው ናቸው።

ለ. የዚህ ክፍተት ምንጮች አጠቃላይ መርሆዎች አጠናክሮ ተግባራዊ አለማድረግ እንደሁኔታው ስልት መቀያየር አለመቻል ቤተሰቦች ባላቸው እጦት ሳይሆን በሚታዩባቸው ባህርያት ተመሥርቶ ድሆችን የመለየት ሥራ መሥራት እንዲሁም ለአንዳንድ ክልሎች ከሌሉች ለይቶ የበለጠ የእርዳታ እህል መስጠት ሊሆኑ ይችላሉ (Clay et.al 1998)።

## 2. ውጤታማ የሆነ የመለየት ሥራ ወጪ ከፍተኛ መሆን :-

ቀደም ሲል እንደተጠቀመው አክሽን ኤይድ ኢትዮጲያ የልማት ፕሮግራም በሚያካሂድባቸው አካባቢዎች የተጠቀመበት የሃብት ደረጃ አሠጣጥ ስልት ውጤታማ ነበር። ነገር ግን ሂደቱን የሚያቀላጥፉ ሠራተኞች ማሰልጠንና የሃብት ደረጃ አሠጣጡን በአጠቃላይ ለማከናወን ከፍተኛ የሆነ ወጪ ጠይቋል።

## 3. ትጋትን የማጥፋት ውጤት ያላቸው ስልቶች :-

ግለሰቦችንም ሆነ አካባቢዎችን በተለያዩ ፕሮግራሞች ለማሳተፍና ተጠቃሚ ለማድረግ ድህነትን የመለየቱ ሥራ የሚጠቀምባቸው መስፈርቶች ህዝቡ የሚያውቃቸው በመሆኑ እነዚህ መሥፈርቶች ለማሟላት በማሰብ ነዋሪዎች የሚፈፅሟቸው ተግባራት የማይፈለጉ ይሆናሉ። የሚከተሉት የነዚህ ድርጊቶች አብነቶች ናቸው።

ሀ. በአላባ ሲራሮ ወረዳ ውስጥ (ሥሙን መጥቀስ ጠቃሚ አይደለም) በአንድ መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት የሚካሄድ ፕሮግራም ነበር። ይህ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት/ሙያዊ ለመሥራት ያቀደው የደን ሽፋኑ የተመናመነበት አካባቢዎች ወይም ቀበሌዎች ውስጥ ነው። ይህ ድርጅት በአንድ አካባቢ በገባ ቁጥር የምግብ ለሥራ ፕሮግራም እንደሚኖር ህዝቡ አውቋል። ይህ የምግብ ለሥራ ፕሮግራም የገበሬዎቹን ገቢ አሳድጎታል። በዚህም ምክንያት

ድርጅቱ ባልገባባቸው ቀበሌዎች የሚገኙ ገበሬዎች የድርጅቱን መስፈረት ለማሟላትና ትኩረቱን ለመሳብ በማሰብ በአካባቢያቸው ያሉትን ዛፎች መመንጠር ይጀምራሉ።

ለ. በአንዳንድ ወረዳዎች የሚገኙ ገበሬዎች አመዝኮ የአመጋገብ ሁኔታን በሚዳስሰው ጥናቱ የልጆቻቸውን በምግብ እጦት መጎዳት ቁመትና ክብደት ሲለካ የእህል እርዳታ (ተጨማሪ አልሚ ምግብ) እንደሚሰጥ ያውቃሉ። ይህን ፈተና ለማለፍ ሲሉ ለልጆቻቸው ያነሰ የምግብ መጠን የሚሰጡ ገበሬዎች አሉ። ይህ የአመጋገብ ሁኔታን ገምጋሞ የእርዳታ እህል ይገባዋል አይገባውም ብሎ ለመወሰን ጥቅም የዋለው ስልት ውሱንነት እጅግ በጣም ቅር ያሰኛቸው ሰዎች አጋጥመውኛል። ለኔ እንደነገሩኝ በባህላቸው የተወሰነ የተረፈ እህል ካለ ለህፃናት እንደሚሰጥ በችግር ግዜ የሚራቡት አዋቂዎች ማለትም አባትና እናት እንደሆኑ ገልፀውልኛል። ይህ መረጃ ትክክለኛ ከሆነ ጥናቱ ማተኮር ያለበት በልጆች ላይ ሳይሆን በወላጆች ላይ መሆን አለበት ብለዋል።

ሐ. እርዳታ ያልተሰጣቸው እርዳታ የሚያገኙት በሚያገኙት ላይ የሚያሳዩት መጥፎ ስሜት በአንዳንዱ አካባቢዎች ጉልቶ የሚታይ ችግር ነው። እከሽን ኤይድ ኢትዮጵያ በሚንቀሳቀስባቸው አካባቢዎች የሃብት ደረጃ አሰጣጡ ነዋሪዎችን በሚያሳትፍ መንገድ ተከናውኗል። ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግባት በቅድሚያ ድሃውን በቡድን ማደራጀት ጀመሩ። በመጀመሪያ አካባቢ አንዳንድ ድሃ ገበሬዎች ከነዚህ የድሃ ገበሬዎች ቡድኖች ጋር መሰባሰቡ አሳፈራቸው። ይህም ማለት ሀብታሙ ይህን ቡድን የማይረቡ የህብረተሰቡ ክፍል አድርጎ ስለሚቆጥረው ከነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር አብሮ መታየትን አንዳንዶች አልፈለጉም።

መ. በአንዳንድ ሁኔታዎች ድህነትን የማጥፋት አላማ ያላቸው የመ.ያ.ድ ፕሮግራሞች ከመንግስት የመስመር (ሴክተር) መ/ቤቶች ሥራዎች የሚጨበት አጋጣሚ አለ። ለምሣሌ እከሽን ኤይድ ኢትዮጵያ በዳሎቻ አካባቢ በገንዘብ ክፍያ የሚያሠራው የተፈጥሮ አካባቢ እንክብካቤ ሲኖር በአካባቢው የሚገኘው የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ተመሳሳይ ሥራ በነፃ የህዝብ ተሳትፎ ያሠራል። በዚህ ሁኔታ የወረዳው ግብርና ጽ/ቤት ያቀዳቸውን ሥራዎች ለማስፈፀም የሚያጋጥመው ችግር በግልፅ የሚታይ ነው።

## 4. ከአሠራር ሥልቶች ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሙ ችግር

ሲዳማ ውስጥ በአይሪሽ ኤይድ ዴቨሉፕመንት ፕሮግራም ሴቶችን ራሳቸውን ለማስቻል የሚካሄድ የአነስተኛ ብድር ፕሮግራም በምገምገምበት ጊዜ ተበዳሪዎችን በቡድን አደራጅቶ ቡድኑን እንደመያዣ ዋስትና መወሰድ ድሃ ቤተሰቦችን የማግለል ገፅታ እንዳለው ማየት ተችሏል።

በድህነት ቅነሳ ፕሮግራም የተሳትፎ ጠቀሜታ

→ ተሳትፎአዊ በሆነ መንገድ የሚደረግን የድህነት ግምገማና ውጤቱን በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር ፣

- ስለድህነት ያለውን ግንዛቤና ትንተና ማዳበር ፣
- የተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች በአጋርነት እንዲሰሩ ማስቻል፣
- ለድህነት ቅነሳ እንቅስቃሴዎች የየአካባቢውን ህዝብ የባለቤትነት ስሜትና ልባዊ ድጋፍ የሚቻለውን ያህል ማሳደግ ፣
- የድህነት ግምገማዎች የአካባቢውን ሁኔታ በትክክል የሚገልፁ እንዲሆኑ መጣር፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ክፍሎች
- ባለጉዳዩች አቅም እንዲኖራቸው ማስቻልና ወደሚቀጥሉት ተከታታይ ተግባራት መምራት
- በድህነት ገፅታ ላይ ያተኮረና ለድሆች ያለውን ትርጉም የሚገልፁ መረጃዎች መስጠት
- ድሆች የሚያጋጥሟቸው ማነቆዎችን ማሳየት
- የፖለቲካ ሰዎች የድህነትን ጉዳይ ችላ ማለት እንደሌለባቸው እና ድህነትን ለማጥፋት ለሚወጡ ፖሊሲዎች የመንግስት ድጋፍ እየመጨረ መምጣት እንዳለበት።

## 6.2 በድህነት ቅነሳ የባለጉዳዮቹ ወይም የሚመለከተው (Stakeholders) ተሳትፎ ፣

ድሆች በራሳቸው ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮችና ግንዛቤያቸውን ለመለየት የመንግስት ተቋሚት ለህዝብ ያለባቸውን ተጠያቂነት ተግባራዊ ለማድረግና ፕሮግራሞችን ከተሳታፊ እይታ አንፃር ለመገምገም ባለጉዳዮችን ማሳተፍ ጠቃሚ መሆኑ ቢታወቅም በብዙዎቹ በመንግስር የሚካሄዱ ፕሮግራሞች ላይ በሰፊው ተግባራዊ አልሆነም። ባለጉዳዮችን ማሳተፍ እነሱን ለማደራጀት የሚያስፈልገው ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ ፕሮግራሞቹን የመንደፍ ሂደቱን ስለሚያራዝመውና ስለሚያወሳስበው መንግስታት ይህን ለማድረግ ብዙውን ግዜ ሲያመነቱ ይስተዋላሉ። ሆኖም መሠረታዊው ችግር ቴክኒካዊ እውቀት ባላቸው ባለሙያዎች ከላይ ተነድፎ ለአፈፃፀም ወደታች የማውረዱ አሰራር ከአካባቢው ሰዎች እውቀት ይበልጣል ተብሎ በሚታመንበት ሁኔታ ባለጉዳዮቹን የማሳተፍ አቅጣጫ ይህን ሥር የሰደደ የአሠራር ልምድ በመሠረቱ ስለሚፈታተነው ወይም ጥያቄ ውስጥ ስለሚያስገባው ነው።

በመሰረቱ ሰዎች የራሳቸው የሆኑ እውቀት ችሎታና ስትራቴጂዎች ያላቸውና አዲስ ነገር ማምጣት የሚችሉ ናቸው በሚል እምነት ላይ መመስረት ይኖርበታል። ስለዚህ ተሳትፎአዊ የሆነ አግባብ መጀመር ያለበት ሰዎች ካሉበት ሁኔታ እንጂ እንዲሆኑ ከምንፈልግበት/ከምንመርጥበት/ መሆን የለበትም። ባለው ላይ ተመስርቶ የመጀመር መርህ ሁለት ነገሮች ማለትም የአካባቢ ህዝብ ስለሚጠቀምባቸው ስትራቴጂዎችና ስላሉባቸው ማነቆዎች ትክክለኛ ግንዛቤ ለማግኘትና ይህን ትክክለኛ ግንዛቤ በመጠቀም ጥቅም ላይ ያልዋሉ ሃብቶችና ሃሳቦችን ለመለየት ይጠቅማል።

የባለጉዳዮች ተሳትፎ በሚመለከት የሚያጋጥመው ሌላው ከባድ ችግር የባለጉዳዮችን ፍትሃዊ ውክልና የሚያረጋግጥ አሠራር በተግባር ላይ ለመጠቀም አስቸጋሪ መሆን ነው። ድሃ ገበሬዎች በአግባቡ የተደራጁ ስላልሆኑና ፖለቲካዊ ውክልናቸው እናሳ ስለሆነም በምክክር ግዜ ያላቸው ተሰሚነት በጣም ደካማ ነው።

በድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞች የባለጉዳዮች ውጤታማ ተሳትፎ መኖሩን ማረጋገጥ አሁን ከሚሰጠው ትኩረት በላይ ሊሰጠው ይገባል። እስከ አሁን ያለው ተሞክሮ

እንደሚያሳየው የባለጉዳዮች ተሳትፎ የተሳካ የሚሆነው ከእውነተኛው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ጋር ሲተሳሰር ነው።

ባለጉዳዮች የራሳቸውን ፍላጎት ራሳቸው መለየት አለባቸው። እንዲሁም ፕሮግራሞችን በሚመለከት ጠቃሚ የሆኑ ውሳኔዎች ከመደረጋቸው በፊት ባለጉዳዮችን ማማከር ይገባል የሚል መርህ በግልፅ የተቀመጠ አሠራር መሆን አለበት። በጣም ውጤታማና ብዙሃኑን የሚያካትት አሳታፊ የአሠራር ሥልት መንደፍ ያስፈልጋል። የፍላጎቶቻቸው ማራመጃ ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ የድሃ ገበሬዎች ድርጅቶችን በመርዳትና በማበረታታት የድሆችን ተሳትፎ ማረጋገጥ ይቻላል። በአላባ ሲራሮ ወረዳ/1992/ ባካሄድኩት ጥናት በድሃው ህዝብ ውስጥ ለሚካሄድ ማንኛውም ልማት ተሳትፎ ያለው ጠቀሜታ ለማየት ችያለሁ። በ1991 በአላባ ሲራሮ ወረዳ ውስጥ (የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ) የእህል ገበያ ጥናት አካሂዳለሁ። መንግስቱ ሃ/ማርያም ወደ ሃራሬ መሰደዳቸውን በሬድዮ ከሰማሁ በኋላ የመስክ ጥናቱን ለማቋረጥ ተገድጄ ነበር። ሁኔታዎች ተረጋግተው ከሦስት ወራት በኋላ ወደ መንደሩ ስሄድ ት/ቤቱ የአገልግሎት ማህበር ጽ/ቤቱ ክሊኒኩና ወፍጮ ቤቱን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈራርሰዋል። ይህን ሁሉ ውድመት ለምን በነዚህ የአካባቢው አገልግሎት ተቋማት ላይ እንደፈፀሙ ስጠይቃቸው የሰጡኝ መልስ ተቋማቱ የመንግስት እንጂ የነሱ እንዳልሆኑ ነው። ይህ መልስ ለኔ አሳማኝ ስላልነበር አጥጋቢ መልስ ለማግኘት ምርምሬን ቀጠልኩ። አንዳንድ መልሶችን ማግኘት ጀመርኩ። ለምሣሌ ት/ቤቱ የተገነባበት ቦታ የአንድ ግለሰብ የግል ይዞታ የነበረው ነው። መሬቱ የተወሰደው ያለግለሰቡ ፈቃድ ነበር። ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም የቤተሰቦቹንና ወዳጆቹን ትብብር ት/ቤቱን ከመሬቱ ላይ አነሱት ይህ በማንኛውም የልማት ጥረት ጥቂቶች እንኳን አንድን የልማት ፕሮጀክት ከተቃወሙ የነዚህ ውሁዳን የህብረተሰብ ክፍል የማማከር አስፈላጊነትን የሚያሳይ ነው።

በፕሮግራሞች ቀረፃ ዝግጅት አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ የድሆች ተሳትፎ መኖር ለማንኛውም የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም መሳካት አስተዋፅኦ አለው። ሙሉጌታ በዛብህ(1995) ባደረገው ጥናት ተሳትፎና ሥልጣንን ወደ ታች ማከፋፈል በሌለበት ሁኔታ የገጠር ልማት ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ መሞከር ውጤቱ የግብርና ቀውስ ነው ሲል ይደመድማል። "ኢትዮጵያ የተለያየ የትኩረት ደረጃና መጠን ያላቸው የተለያዩ የተቀናጁ ፓኬጆች በተግባር ሞክራለች። እነዚህ ፓኬጆች የሚጋሯቸው ባህሪያት የአቀራረፅ ሂደት ከውጭ የተቀዳ፣ ተጠቃሚዎችን ተሳትፎ በፍፁም ግምት ያላስገባ ትኩረቱ በምርት ከታ/በቁጥር የሚገለፁ ግቦች ላይ ብቻ

ያደረገ እንደ ትቤቶች ጤና ጣቢያዎች መንገዶችና መገናኛዎች ብድርና የገበያ ሁኔታ፣ የቤተሰብ ምጣኔ፣ በሚመለከት ተግባራዊ ምርምርና የመሳሰሉ ደጋፊ ጉዳዮችም ትኩረት ያልሰጡ መሆኑ ናቸው። ውጤቱም ምንም ነገር ያላሳካ በቢሮክራሲያዊ መንገድ የተደራጀ አባካኝ ትርጉም የለሽና ተጠያቂነት የሌለበት የእቅድ ዝግጅትና አገልግሎት አሠጣጥ ስርአት ነው። ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት የድህነት ቀውስ መውጣት ከፈለገች የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞችን ከማቀድና ከመፈፀም እኳያ ዋናው የትኩረት ማእከል የወረዳዎች አስተዳደር መሆኑን ችላ በማለት ሊሆን አይችልም። ይህን ማድረግ መጀመሪያ ላይ ከባድ ቢመስልም ይህን ማድረግ ከቻለ በኋላ ነው ልማት ትርጉም የሚኖረው።

በቀበሌ ደረጃ የሚደረግ ማንኛውም ተሳትፎ ግልፅነት ያለውና አድልዎ የሌለው የሃብት አጠቃቀም እንዲኖር በማድረግ ተጠያቂነትን ያጠናክራል። ከዚህ በላይ የምግብ ዋስትናው ስትራቴጂ የሚሳካው ሥልጣንን በየደረጃው ወደታች ባከፋፈለ የውሳኔ አሠጣጥ ሂደት ውስጥ የህዝቡ ሰፊ ተሳትፎ ሲኖር ነው። በተጨማሪም በተገቢው መንገድ በግልፅ የተቀመጠ ዲሞክራሲያዊ ሂደት የምግብ ዋስትና ደረጃን ከፍ ለማድረግ የሚደረግ ጥረትን ያበረታታል። ህዝቡን ከታች ጀምሮ ለማሳተፍ ወይም ለማንቀሳቀስ የሚደረገው ጥረት በቤተሰብ (ማለትም ተጨባጭ ጥቅም በሚገኝበት) ደረጃ በመንደርና በተፋሰስ ደረጃ እውን ማድረግ ይችላል።

የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ በመፈፀምና በመከታተል የህዝብ ተሳትፎ ያለውን ጠቀሜታ ላይ ከተስማማን የሚቀጥለው ጥያቄ የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል የሚለው ነው። የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም የመቅረፅ ጉዳይ የወሰድን እንደሆን የህዝቡን ችግር ህዝቡ ራሱ እንዲለይና ማድረግና ቴክኒካዊ የሆነውን ፕላኑን የማዘጋጀት ሥራዎች ብለን ብሉ ለሁለት መክፈል ይቻላል።

በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች ውስጥ ተሳትፎ የሚመራባቸው መርሆች ፦

**በአገር ደረጃ መኖር ስላለበት የባለቤትነት ስሜት**

ውጤታማ ለሆነ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች ዝግጅትና አፈፃፀም የመንግስት ቁርጠኝነት አመራርና ሰፊ የሆነ በሃገር ደረጃ ያለ የባለቤትነት መንፈስ መኖር ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው።

**ግልፅነት** ፦በክልልና በሃገር ደረጃ የሚደረግ ምክክርና የተገኙ ውጤቶች አዘጋገብ ግልፅነት የተላበሰ መሆን ከሲቪል ማህበረሰቦችና ከሌሎች ጉዳዩ ያገባናል ከሚሉ አካላት ጋር መተማመን የባለቤትነት መንፈስንና መደጋገፍን ያጠናክራል።


**ሁሉንም በሂደቱ ማሳተፍ /እንዲሳተፉ ማድረግ/** የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሂደት የበለጠ ውጤታማ የሚሆነው የድሆችንና ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ክፍሎችን በተለይም የሴቶችን ጨምሮ የተለያዩ ባለጉዳዮችን እውቀትና ልምድ በጥቅም ላይ በማዋልና የነሱን እይታ ሥርአት ባለው መንገድ በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂው ዝግጅትና አፈፃፀም ውስጥ በማካተት ነው። ለህዝብ ተሳትፎ ዋጋ መስጠት ይህንንም በሰፊው ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን ከዚህ እልፎ የሃገሪቱ ሁኔታ የሚፈቅደውን ያህል ባለጉዳዮችን በውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ማሳተፍ አስፈላጊ ነው።

**የአመራር ብቃትን ማጠናከር**፦ የማሳተፉ ሂደት በተቻለ መጠን ባለው የአስተዳደር የፖለቲካ ሥርአት ላይ የሚመሠረትና አብሮ የሚሄድ እነሱን የሚያጠናክር መሆን እንጂ እየተሰራባቸው ያሉትን የተሳትፍና የውክልና ሂደቶች የሚተካ መሆን የለበትም። ይህም ሌሎች ተጨማሪ መዋቅሮች ጎን ለጎን እንዳይኖሩ ከመርዳቱም በላይ በህዝብ የተመረጡ የአካባቢና ሃገራዊ ምክር ቤቶች አስተያየቶች በሂደቱ እንዲካተቱና ቀደም ሲል በተሳትፎው ሂደት የተገኙ ተመክሮዎች በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ዝግጅት ውስጥ ጥቅም ላይ ለማዋል ያስችላል።

**ቀጣይነት (ዘላቂነት)** ፦ ባሉ አሰራሮች ላይ ተመስርቶ የሚዘረጋ አሳታፊ የሆነ ኘሮግራም ተቋማዊ መልክ የመያዝና ቀጣይ የመሆን ዕድሉ በጣም ሰፊ ነው። በተመሳሳይ የፖሊሲ ማሻሻያዎች ስለድህነትና መንስኤዎቹ በብዙዎቻችን ዘንድ ካለው ግንዛቤ ጋር የሚጣጣሙ ከሆኑ የሚኑሱ ከሆኑ የተቀባይነትና የተፈፃሚነት ዕድላቸው ሰፊ ነው።

**ቀጣይነት ያለው መሻሻል፡-** የድህነት ቅነሳው ሂደት አንድ ቀጥ ያለ መስመር ሣይሆን በየደረጃው ተግ/ቆም/ እያለ ሲያስፈልግም ወደኋላ እየተመለሰ የሚያይ የተሳትፎ ምላሽ/Feedback/ የሚያቅድ አፈፃፀሙንና ውጤቱን ከተቀመጡ ግቦችና የውጤት ጠቋሚዎች አንፃር የመገምገም ሂደት ነው። በመደበኛ ሁኔታ የሚካሄድ የህዝብ ተሳትፎ ድህነትን ለመቀነስ የሚከናወኑ ተግባራት እቅድና አፈፃፀምን በቀጣይነት እየተሻሻሉ እንዲሄዱ በማድረግ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ከዚህ በላይ የማንኛውንም ባለጉዳይ ፍላጎት እንዳለ ተቀብሎ ከማስተናገድ ይልቅ እርስ በርስ የሚጋጩ ፍላጎቶችንና ማጭበርበርን እያጣሩ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።

ሥዕል 2 የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች በመቅረፅና በመፈፀም ሂደት ውስጥ ያለ ተሳትፎ



## የተሳትፎ ማነቆዎች

- ስለተሳትፎው ሂደት ስለድህነትና ድህነትን ለመቀነስ ስለሚደረገው ጥረት ጠቀሜታ የተለያዩ ባለጉዳዮች ያላቸው ግንዛቤ በጣም የተለያየ መሆን ፣
- አንዳንድ ባለጉዳዮች የተሳትፎው ሂደት ስለሚያስገኘው ውጤት ያላቸው የተጋነነ ግምት ፣
- በተሳታፊው መሃከል በቂ የሆነ የመረጃ ልውውጥ አለመኖር ፣
- መጨረሻቸው ያልተቋጨ/በውል ያልታወቀ እና በቂ በጀት ያልተመደበላቸው ወይም በአደራጆቹ እንዳው ለይምሰል የሚደረጉ በአግባቡ ያልታቀዱ የተሳትፎ ሂደቶች ፤
- ሥልጣን ወይም ተቀባይነት በማጣት ሥጋት በመንግስት ወኪሎች ሰፊ ተሳትፎ እንዲኖር በጎ ፍላጎት አለመኖር ፣
- የጊዜ የአቅምና የፋይናንስ እጥረት
- በምክክሩ ሂደት መሰላቸት(መታከት) ፣

## በአካባቢዎችና በሃገር ደረጃ የሚኖር ትስስር

የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ የመንደፉ ሥራ በአገር አቀፍ ደረጃ ሊከናወን ይችላል። ሆኖም የሥልጣን ወደ ታች መከፋፈልና አገር አቀፍ ፖሊሲዎችን በመፈፀም የክልል መንግስታት ሚና እያደገ መምጣት የክልል መንግስታት ስትራቴጂዎችን በመንደፍ ሥራ ማሳተፍ የግድ አስፈላጊ ነው። በነዚህ በተለያዩ የመንግስት ደረጃዎች መሃከል የሚፈጠር ትስስር የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎችን በመፈፀምና በመከታተል የክልሎች ቁርጠኝነት ለማረጋገጥ ይረዳል።በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ክፍል እንደተገለፀው/ ሆኖም ክልሎችን ማሳተፍ የሚያስከትለው የወጪና ትራንስፓርት ጉዳይ ታሳቢ መሆን አለበት።
የክልል መንግስታት በተለይም የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂው ዋና ዋና ተግባራት የመፈፀም ሃላፊነት እንዲሰጣቸው ማድረግ ጠቀሜታ አለው። በከፍተኛ የመንግስት ደረጃ ያለ አካል ከሥሩ ያሉትን አካላት ሲያማክር አስተያየታቸውን ሲያዳምጥ ምላሽም ሲሰጧቸው በየአካባቢው የሚገኙ ሃላፊዎች የስትራቴጂው ባለቤቶች መሆናቸው ይሰማቸዋል እነሱም በተራቸው ሌሎችን ለማማከርና ስትራቴጂውን ከራሳቸው አካባቢ ሁኔታ በማጣጣም ተግባራዊ ለማድረግ ይነሳሳሉ።

ሥልጣንን በተዋረድ መከፋፈል

- ፅንሰ ሃሳቡ
- ጠቀሜታው ምንድንነው?
- ሥልጣንን በተዋረድ ማከፋፈል በኢትዮጵያ ምን ይመስላል?

## 6.3 የስልጣን በተዋረድ መከፋፈል

የስልጣን በተዋረድ መከፋፈል ድህነት ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል። የአካባቢ መስተዳድር የሚሠራው ለህዝቡ ቅርበት ባለው መንገድ ነው። ለድሆች ጥያቄና ችግር ቶሎ ምላሽ መስጠት ይችላል። ከሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ጋርም በአጋርነት የመሥራት ብቃት ሊኖረው ይችላል። ነገር ግን ሥልጣን በተዋረድ የማከፋፈሉን ፕሮግራም ውጤታማነት ሊቀንሱ የሚችሉ አንዳንድ ማነቆዎች አሉ። የመጀመሪያው በአካባቢ ደረጃ በሚኖረው አስተዳደራዊ አቅም ደካማ መሆን ነው። ሁለተኛው ማዕከላዊ መንግስት በተግባር ብዙ ሥልጣንና ሃብት ለአካባቢ መስተዳድሮች ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆንና ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሃገር ደረጃ ትድሚያ በተሰጣቸው ተግባራትና በየአካባቢው በተነደፉ ፕሮግራሞች መሃከል ግጭት ወይም አለመጣጣም እያደገ ሊመጣ ይችላል። ሦስተኛው የፋይናንስ ማኔጅመንትና የክፍያ ሥርአቶች ብዙውን ጊዜ በጣም የተማከሉ በመሆናቸው በየአካባቢው ለሚካሄዱ ፕሮግራሞች አፈፃፀም ተስማሚ አይሆኑም። በመጨረሻም የአካባቢ መስተዳድሮች የባለጉዳዮችን ተሳትፎ የሚጋብዙና አገልግሎታቸውን ለሚጠቀሙ ደንበኞች የበለጠ ተጠያቂ ስለመሆናቸው ዋስትና የለም። የአካባቢ መስተዳደር ባለሥልጣናት መከታተልና እዲት ማድረግ አስቸጋሪ ነው። በየአካባቢው ሙስና ሊፈፀም የሚችልበት አደጋ አለ። ወይም የተወሰኑ ቡድኖች በአካባቢው የሚፈፀሙ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ ተገቢ ያልሆነ ሚና የማድረግ ሃይል ሊያገኙ ይችላሉ። እንደዚህ ዓይነት ጉድለት የሚታይባቸው የሥልጣን ክፍፍል ፕሮግራሞች የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞችን አጠቃላይ ውጤታማነትና በድህነት ላይ የሚፈጥሩትን ለውጥ ለማዳከም የሚችሉ አደጋዎችን በውስጣቸው የተሸከሙ ናቸው።

እነዚህን ችግሮች ለመቋቋም በርካታ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን መጋፈጥ ያስፈልጋል። የሠራተኞች ዝውውርና የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን በማካሄድ በአካባቢው ያለው የሰው ሃይል ደረጃውን ከፍ ማድረግ አንዱ ወሳኝ ተግባር ነው። በተጨማሪም ለየአካባቢው በቂ ሃብት መመደብና ማዕከላዊ መንግስትና የአካባቢው የአስተዳደር ሚናና ሃላፊነቶችን በዝርዝር በግልፅ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። የክፍያ ሥርአቶች ከአካባቢ አስተዳደር አካላት አሠራር ጋር በሚስማማ መንገድ እንዲስተካከሉና ወጥ እንዲሆኑ ጥረቱ መቀጠል ይኖርበታል። ከሁሉም በላይ ተሳትፎ ዲሞክራሲያዊ፣ አሠራርና ተጠያቂነት መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

### 6.3.1 የሥልጣን ክፍፍል ፅንሰ ሀሳብ

ስልጣንን በተዋረድ ማከፋፈል ሀብትን ተግባራንና የመወሰን ስልጣንን በአመዛኙ ወይም ሙሉ በሙሉ ከማዕካለዊ መንግስት ነፃ ለሆኑና በዲሞክራዊያዊ መንገድ ለተመረጡ በዝቅተኛ ደረጃ ላሉ ባለስልጣኖች በተዋረድ መስጠት ማለት ነው፡፡ Karijin de Jong et.al 1999)። የፖለቲካ የአስተዳደር የፊሲካልና የገበያ ጉዳዮችን በየደረጃው ወደ ታች ማውረድን ያካትታል፡፡ ፖለቲካዊ ገፅታው ዜጎች ወይም የመረጧቸው ተወካዮች መንግስታዊ በሆነ ማለትም ህገመንግስታዊ ማሻሻያዎችን የፖለቲካ ድርጅቶች ስለመኖራቸው የህግ አወጣጥ ስለማጠናከር ወዘተ የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የላቀ (የበለጠ) ስልጣን በመስጠት ላይ ያለመ ነው፡፡ አስተዳደራዊ የሆነው ደግሞ ስልጣንን ሀላፊነቶችንና የፋይናንስ ሀብቶችን (ህዝባዊ) አገልግሎቶችን ለሚሰጡ በተለያየ ደረጃ ለሚገኙ የመንግስት አካላት ማከፋፈል ነው፡፡ አስተዳደራዊ የተዋረድ የስልጣን ክፍፍል በሶስት አበይት መልኮች ይፈፀማል፡፡

ሀ) የተከማቸው መበታተን (Deconcentration)፦ በአንድ አካል ላይ የተከማቹትን ስልጣን የፋይናንስና ማኔጅመንት ሀላፊነቶች የተለያየ ደረጃ ላላቸው የማዕከላዊ መንግስት አካላት ማከፋፈል ፤

ለ) የስልጣን ውክልና ፦ ማዕከላዊ መንግስት ከፊል አቶኖሚ ላለው ወይም ሙሉ በሙሉ ለማይቆጣጠረው ግን በመጨረሻ ለሱ ተጠያቂ ለሆነ ድርጅት ውሳኔ የመስጠት ሀላፊነትን መንግስታዊ ስራዎች የማስተዳደር ስልጣኑን በውክልና የሚሰጥበት ነው፡፡

ሐ) ስልጣን ወደታች በማካፈል የሚያምኑ መንግስታት ውሳኔ የመስጠት ስልጣንን ፋይናንስና ማኔጅመንት ስራን በተወሰነ ደረጃ አቶኖሚና የኮርፖሬት ደረጃ ላላቸው የክልል መንግስታት አካላት ይሰጣሉ፡፡ ( World Bank 1999)

የፊሲካል የስልጣን ክፍፍል በግብርና በመሳሰሉት መልክ የሚሰበሰቡ የመንግስት ገቢዎችና በነዚህ ላይ የመወሰን ስልጣንን በማዕከላዊና ክልል መንግስታት መሀከል ማካፈልን ያጠቃልላል። የኢኮኖሚ ወይም የገበያ የስልጣን ክፍፍል የመንግስት ተግባራትና ሀላፊነቶች ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ለየተለያዩ የህዝብ ቡድኖች የህብረት ስራ ማህበራት ሲቪል ማህበረሰቦችና ለሌሎች መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሚሰጡበት ሁኔታ የሚያካትት ነው፡፡ በመንግስት የተያዙ ድርጅቶች (የንግድ ወይም የልማት) ወደ ግሉ ማዛወርና የዋጋ ቁጥጥር ማንሳት የኢኮኖሚ ወይም የገበያ ስልጣን ክፍፍል ጥሩ አብነቶች ናቸው፡፡

ሥልጣን ማከፋፈልን በመደገፍና በመቃወም የሚቀርቡ በዛ ያሉ ክርክሮች አሉ። በድጋፍ በኩል የሚቀርቡት ሥልጣን ማከፋፈል የሃብት አመዳደብን ቅልጥፍናን ያሻሽላል ለምርትና ለድህነት ቅነሳ ያተጋል የሚሉ ናቸው። በተጨማሪም በየአካባቢው ያሉ ፈፃሚዎች ስለ አካባቢው ሰዎች ችግር የተሻለ ግንዛቤ አላቸው በተሻለ ሁኔታም ለችግሮቹ ምላሽ መስጠት ይችላሉ። በዚህም የሚገኘው እርካታና ደህንነት ይሻላል እንዲሁም ከማዕከላዊ መንግስት አካላት ባነሰ ዋጋ(ውጪ) ሸቀጦችና አገልግሎቶችን ማቅረብ ይችላል ። (Suzanne Pirion-sall, 1997)

የሥልጣን ክፍፍል ጠቃሚነት ለማሳመን የሚቀርቡት ማስረጃዎች ፓለቲካዊ/ህዝባዊ ተሳትፎ/ እና ኢኮኖሚያዊ/ቅልጥፍና/ ተብለው ሊመደቡ ይችላሉ። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል።

- ውሳኔ በመስጠትና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት/ጉዳዮች/ በመለየት ላይ የህዝቡን ተሳትፎ በማሻሻል መንግስታዊ አስተዳደርንና ህዝቡ በራሱ ጉዳይ ላይ የመወሰን አቅሙን ማሻሻል ፣

- ለህዝቡ ችግሮች መፍትሄ የሚሰጡ ተቋማትን ማቋቋም ፣
    - የምግብ ዋስትና የድህነት ቅነሳና እድገትን በማምጣት ለሚያተኩሩ ተግባራት ለማስፈፀም የሚውሉ ሃብቶችን/ጥሪቶችን/ለማቅረግ ህዝቡ በሃብቶቹና በተቋማቱ ላይ ያለውን ቁጥጥር ከፍ ማድረግ ፣

    - የመሠረታዊ አገልግሎቶች ለህዝቡ በቀጥታ የሚቀርቡበትን ሁኔታ ማሻሻል

- ነፃ ለሆኑትና አቶኖሚ ላላቸው ክልሎች የሚደረገው የሃብት አመዳደብ ቅልፍጥናን ማሻሻል ፣
- የአሠራር ግልፅነትና ተጠያቂነት ክትትልና በክልሎች ያለውን የምግብ ዋስትና ማጣት እንዲሁም የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች ማኔጅመንት ውጤታማነትን ማሻሻል ፣
- ድሃ ቤተሰቦችንና አካባቢያዊ / Preferences/ ምርጫዎች የመለየት ሥራ የጠራ ማድረግ ፣ የተሳሳተ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ አመራር፣ ሙስና፣ አላስፈላጊ ቢሮክራሲየዊ መዋቅር መፍጠር በክልሎች መሃከል የሚኖረው የገቢ ልዩነት መስፋትና የመሳሰሉትን ሊመጡ የሚችሉ አደጋዎችን በማመላከት የሥልጣን ክፍፍል ሊያከናውን ስለሚችለው ውጤት በጣም የተጋነነ እንዳይሆን አንዳንድ ምሁራን ያስጠነቅቃሉ። ሥልጣን የማከፋፈሉ ሂደት እንዲሳካ የክልል መንግስታት ተፈላጊ

የሆኑትን ሃብት፣ ሥልጣን፣ የተጠያቂነት አሠራርና የሥልጣን ክፍፍሉን ሂደት የመቅረፅና የመፈፀም አቅም ሊኖራቸው ይገባል።

## 6.3.2 የሥልጣንን ክፍፍል በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ከአንድ ምዕተ አመት በላይ በጣም የተማከለ የአስተዳደር ሥርአት ነበራት። የሥልጣን ክፍፍሉ ዋነኛ መነሻ ፖለቲካዊ አጀንዳ ነው። ትርጉም ያለው የሥልጣን ክፍፍል የተጀመረው በ1991 ዓ.ም. ወዲህ ነው። አላማውም ለተለያዩ የነፃነት ንቅናቄዎች ምቹ ፖለቲካዊ ሁኔታ በመፍጠር በሃገሪቱ ያለውን የፖለቲካ ግጭት ለመፍታት በሚደረገው እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ለማድረግ ነው። ይህም በሽግግሩ ወቅት በወጣው ቻርተር አንቀፅ ሁለት ላይ በግልፅ ተቀምጧል (ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1, ሐምሌ, 1983) የብሔሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ተረጋግጧል። ይህን ለማሳካት እያንዳንዱ ብሄር ብሄረሰብና ህዝብ የሚከተሉት መብቶች ተረጋግጠውለታል።

ሀ. ማንነቱን የማስከበር ባህሉንና ታሪኩን የማዳበር ቋንቋን የመጠቀምና የማሣደግ ፣

ለ. በግልፅ በተከለለ የራሱ አካባቢ የራሱን ጉዳይ በራሱ ማስተዳደርና ነፃ ፍትሃዊና ተገቢ በሆነ ውክልና በማዕከላዊ መንግስት የመሳተፍ ፣

ሐ. እነዚህ መብቶች ተጥሰዋል ወይም ተሸራርፈዋል ብሎ ባመነ ግዜ የራሱን እድል በራስ የመወሰን መብቱ ተጠቅሞ የመገንጠል ፣

የዚህ አዋጅ አንቀፅ 13 ቋንቋን መሠረት ያደረጉ ብሄራዊና ክልላዊ መንግስታት እንደተቋቋሙ ይገልፃል። ይህ አጠቃላይ መርህ በተከታታይ በወጡ አዋጆች እንዲጠናከር ተደርጓል። ኢትዮጵያ ከረዥም ግዜ በኋላ ሥልጣን ማከፋፈልንና ዲሞክራሲን የመገንባት ሥራ ከምር በተግባር እየሞከረች ነው።

አዋጅ ቁጥር 7/1992 በተዋረድ ስላሉት ሦስት የስልጣን አካላት ማለትም የማዕከላዊ ክልልና የወረዳ ሥልጣናት ይዘረዝራል። ይህም ከመከላከያ ውጭ ጉዳይ ገንዘብ ማተምና የውጭ ኢኮኖሚ ግንኙነት ውጭ ያሉትን የማእከላዊ መንግስት ሃላፊነቶች ባልተገደበ አቶኖሚ ለክልልና ወረዳ መስተዳድር አካላት ሰጥቷል። አዋጅ ቁጥር 33/92 ስለታሰበው የሥልጣንን ክፍፍል ተጨማሪ ማብራሪያ በመስጠት ከግብር የሚገኘው ገቢ ስለሚከፋፈልበት ማዕቀፍና

## የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

ክልሎች ስለሚበደሩበትና ስለሚያበድሩበት ሁኔታ ይዘረዝራል። አዋጅ ቁጥር 41/93 ደግሞ በማእከላዊ መንግስትና በክልል አስፈፃሚ አካላት ስላለው የሥልጣን ክፍፍል ክልሎች ግብር ለመሰብሰብና በጀት ለማዘጋጀት ሥላላቸው ስልጣን ይዘረዝራል።

ከፖለቲካዊ የሥልጣን ክፍፍል አኳያ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለመመሥረት የሚያስችለው ህገመንግስት የፀደቀው በ1994 ዓ.ም. ነው። በኢትዮጵያው ኀገመንግስት አንቀጽ 47 መሠረት 9 ክልሎችና ሁለት ልዩ ክልሎች የመንግስት አስተደደር የማቋቋም ክልላዊ ህገመንግስትና ሌሎች ህጐች የማውጣት ክልላዊ የልማት ፖሊሲዎች=ን የመንደፍና የመፈፀም መሬትና ሌሎች የተፈጥሮ ሃብቶችን የማስተዳደር ታክስ የመሰብሰብና ለመንግስት በተሰጡ ምንጮች ላይ ግብር መጣል የመንግስት በጀት የማስተዳደር በክልሉ ውስጥ ህግና ስርአትን የማስከበር ሥልጣንና ተግባራት አሏቸው። የክልል መንግስታት 66 ዞኖችና 556 ወረዳዎች አሏቸው።

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ህገመንግስት አንቀፅ 79 ወረዳዎች የመሬት ግብር መጣልና መሰብሰብ ከግብርና ሥራ የሚገኝ ገቢ ግብርና ከተወሰኑ የንግድ አገልግሎቶች ግብር መሰብሰብ እንዲችሉ ስልጣን ይሰጣቸዋል። የህዝብ ብዛት የእድገት ደረጃ የሚያስገባው ገቢና በመሳሰሉት መስፈርቶች አካትቶ በሚሠራ ቀመር መሠረት ማዕከላዊ መንግስት ለክልሎችና ዞኖች ከፍተኛ የሆነ የበጀት/ፋይናንስ/ ድጐማ ያደርጋል።

የሥልጣን ማከፋፈሉ ሂደት ዝግጅትና አፈፃፀም ከላይ ወደታች በሆነ መንገድና ህዝቡን በአግባቡ ሳያማክርና ሳያሳትፍ የተከናወነ ነው። ሥርነቀል ከሆነው ከዚህ የሥልጣን ክፍፍል ሂደት በተጨማሪ ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን የሚመለከቱ የተለያዩ የማሻሻያ እርምጃዎች ወስዳለች።

በማቀዱ ሂደት በተለይ ችግሮችን በመለየት በቀበሌ ደረጃ የሚታይ የህዝብ ተሳትፎ አለ። ችግሩ የህዝቡን ችግሮች መለየቱ ሣይሆን እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የተቀረፁ ፕሮጀክቶች ለማስፈፀም የሚያስፈልገው የፋይናንስ ሃብት ማግኘት ነው። ብዙዎች ወረዳዎች ከፌደራሉ መንግስት ከሚሰጠውና ዞኖች በሚመድቡላቸው በጀት ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጥገኛ ናቸው። ለምሣሌ ለመንግስታዊ ሥራዎች በአወበል ወረዳ ከሚያስፈልገው በጀት 59% የተሸፈነው ከዞኑ በተመደበ ገንዘብ ነው።

የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ

→ የክትትል ተግባር

→ የግምገማ ተግባር

- በመካከል የሚደረግ ግምገማ
- የመጨረሻ ድርሻ ግምገማ
- ከተጠናቀቀ በኋላ የሚደረግ ግምገማ

## 6.4 ተሳትፎአዊ የሆነ ክትትልና ግምገማ

ጠንካራ የአፈፃፀምና ክትትል ሥርአት ተግባራዊ የማድረግ ጉዳይ በሁሉም የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞች ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ይህ የመረጃ ሥርአት የፕሮግራሙ የፊዚካል አፈፃፀም የወጪዎች ክትትል ሥርአት የሠራተኞች ሥራ አፈፃፀም የተጠቃሚዎች ግምገማና የደንበኞች እርካታ ዳሰሳ እና የሁሉም ሴክተሮች አፈፃፀምን ደረጃ የሚያካትት ነው። እነዚህ ውጤቶች ደግሞ እንደገና የምላሽ መረጃ (feedback) በመሆን ፖሊሲዎች ለማውጣትና ቀዳሚ ተግባራትን በመለየት ሥራ ግብአት ይሆናሉ።

በአሁኑ ለክትትል ተግባር የሚሰጠው ትኩረት እናሳ ነው። ይህም የሚሆነው ድህነትን መለካት በራሱ ከባድ ስለሆነና ይህን በሚመለከት ያሉ ጥሬ መረጃዎች እጅግ በጣም ውስን ስለሆኑ ነው። በቀላሉ ሊከሉ በሚችሉ የአፈፃፀም ገፅታዎች የበለጠ ትኩረት የመስጠት አደጋ አለ። ስለዚህ በመጠንና በአይነት ድህነትን ለመለካት የተጠናከረ ጥረት መደረግ አለበት። በፍጆታ ላይ የተመሠረቱ የድህነት ምዘና የተጠቃሚዎች ግምገማ እና ተሳትፎአዊ የሆነ የገጠር ምዘና በአፈፃፀም ክትትል ውስጥ የላቀ ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል።

የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞችን አፈፃፀም በአግባቡ ለመከታተልና ፕሮግራሞቹ በሚስተፈው ማህበረሰብ ላይ የሚያመጡትን ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ለመገምገም እንዲቻል የፕሮራሙ አፈፃፀም ከመጀመሩ በፊት አሳታፊ የሆነ የክትትልና የግምገማ ሥርአት በግልፅ ተቀምጦ መዘርጋት አለበት። በመሠረቱ የክትትልና የግምገማ ተግባራት የሚገናኙ የተያያዙ ቢሆንም አንዱ ካንዱ የተለየ ትርጉም አለው። የፖሊሲና የፕሮግራም ተግባራት ከአገሪቱ የረዥምና የአጭር ጊዜ ዓላማዎች ጋር እንዲጣጣሙ ተደርገው በተመረጡ መሠረታዊ መመዘኛዎች (indicators) በመጠቀም ሊገመገሙ ይገባል።

ፕሮግራሞች (ፕሮጀክቶች) የተጠቃሚዎች መሆናቸው ተቀባይነት ያገኘ ጉዳይ ነው። የፕሮጀክቶች ቀጣይነት/ዘላቂነት/ ዞሮ ዞሮ የሚወሰነው ተጠቃሚዎች ምን ያህል የፕሮግራሞቹን አፈፃፀም መከታተልና መገምገም ይችላሉ በሚለው መለኪያ ነው። ይህም እውን የሚሆን ከሆነ ሁሉም ባለጉዳዮች ፕሮጀክቶቹ ከታሰቡበት(ከተፀነሱበት) ግዜ ጀምሮ በፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ መሳተፍ አለባቸው። ይህም የክትትልና ግምገማ ክህሎት እንዲያዳብሩ ይረዳል። ስለሆነም የክትትልና ግምገማ ሥርአት የባለጉዳዮችን (Stakeholders) ተሳትፎ የሚቻለውን ያህል ለማሳደግ በሚያስችል መንገድ መቀረፅ አለበት።

የማምገማና የክትትል ሥርአቶች ለተጠቃሚዎች ቀላልና ያልተወሳሰቡ ከሆኑ  የህዝቡን ተሣትፎ ማሳደግ ይቻላል። በክትትልና ግምገማ የማህበረሰቡ ተሳትፎ ፡-

- ችግሮችንና የቀዳሚ ተግባራት አቀማመጥን በግልፅ ያስቀምጣል።
- በፕሮጀክቶች ላይ የባለቤትነት ስሜት ይፈጥራል ያበረታታል።
- ሀብትን ለማንቀሳቀስ በአግባቡ በአግባቡ ለመጠቀም ሁኔታዎችን ያመቻቻል።
- ከባለጉዳዮች በቂና ፈጣን ድጋፍ ያስገኛል።
- የረዥምና አጭር ጊዜ አላማዎችን ጥርት ባለመንገድ ለማስቀመጥ ይረዳል።
- የተሻሉ መረጃዎችን ምርቶችንና ውጤቶችን ለማግኘት ይረዳል።
- የማህበረሰቡን አቅም በመገንባት አስተዋፅኦ ያደርጋል።
- በውሳኔ አሰጣጥ ተጠቃሚው በራሱ ጉዳዮች የመወሰን አቅሙን ያሳድጋል።
- የልማት ስራዎች ቀጣይነትን /ዘላቂነት/ ያጠናክራል ተብሎ ይታመናል።

ተሳትፏዊ የሆነ  ክትትልና ግምገማ የፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞችን ግስጋሴ ውጤታማነት ምርቶችና የሚያስገኟቸው ለውጦችን ለመመርመር/ለመፈተሽ/ የሚያስችል መረጃዎች የማሰባሰብና የመተንተን መስተጋብራዊ ሂደት ነው።

ክትትልና ግምገማ እርስ በርስ /የተሳሰሩ/ ግን የተለያዩ ፅንስ ሃሳቦች ናቸው። ክትትልና ግምገማ ፕሮጀክቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት የምንጠቀምባቸው መረጃዎች የሚሰበሰቡና የሚተነተኑ ትንተናዊ ፣ ሂደቶች ናቸው። ሆኖም የራሳቸው ትኩረቶችና ስትራቴጂዎች አሏቸው።

ክትትል በፕሮጀክቶች ዝርዝር ተግባራት የሥራ ግዜ ሰንጠረዦች ውጤቶች ወዘተ ላይ በማተኮር ቀጣይ ወይም በተወሰነ የጊዜ ልዩነት የሚደረግ የፕሮጀክት አፈፃፀምን መለስ ብሎ የሚያይ/የምልሰት እይታ/ ነው። ውጤታማና ቀልጣፋ የፕሮጀክት አፈፃፀምን ለማረጋገጥ የሚያስችል የምላሽ መረጃ (feed back) ለመስጠት/ለማቅረብ/ የሚቀረጽ ነው። ክትትል በፕሮጀክቶች አፈፃፀሞች የሚያጋጥሙ ዝንፈቶችን ከወዲሁ ለመለየትና ለማረም/ለማስተካከል ያስችላል። ይህም ጉዳት ከመድረሱ ወይም ከመባባሱ በፊት ያልተፈለጉ ሁኔታዎችን ለማስተካከል ወይም ለመፍታት እድል ይሰጣል።

ግምገማ የፕሮጀክት አፈፃፀም ውጤታማነትና ያመጣው ለውጥ ለማየት በተወሰነ ጊዜ ልዩነት የሚደረግ ስልታዊ ምዘና ነው። ግምገማ አንድ ፕሮጀክት ከተጠናቀቀ በኋላ እንደ ግምገማው አላማ ከተወሰኑ ወይም ከብዙ አመታት ሊካሄድ ይችላል። የፕሮጀክቱ ዋጋ ውጤቶችና ያመጣቸው ለውጦች ላይ ብይን በመስጠት /በመመዘን/ የሚያተኩር ነው።

ተሳትፏዊ ክትትልና ግምገማ የሚከተሉትን ነጥቦች የሚያካትቱ ቁልፍ መለያ ጠባዮች/ገፅታዎች/ አሏቸው።

- ተሳትፏዊ ክትትልና ግምገማ በፕሮጀክቱ የሚሳተፉትን ማህበረሰቦች የመወሰን አቅም ለማሳደግ አልሞ መስራት አለበት።
- የተሳትፎአዊ ክትትልና ግምገማ ቀዳሚ ትኩረት ችግሮችና ማነቆችን በመለየት ላይ ሣይሆን ለተሻሻለ አፈፃፀም በሚረዳ በተመክሮ የተገኙ ልምዶች /ትምህርቶች በመለየት ላይ መሆን አለበት።
- ክትትልና ግምገማ በሥራ አመራሩና በባለጉዳዮች የሚፈለጉ መረጃዎችን ማቅረብ/መስጠት አለበት።
- የክትትልና ግምገማ ሥርአቶች የፕሮጀክቱ ሂደት አንድ አካል መሆን አለባቸው።
- የክትትልና ግምገማ ሥርአቶች ለውሣኔ አሰጣጥ የሚያግዙ መረጃዎችን ለማቅረብ የምንጠቀምባቸው የማኔጅመንት (የሥራ አመራር) መሣሪያዎች ናቸው።
- ክትትል የሚደረገው በውስጥ ሲሆን ግምገማ ግን በውስጥና በውጭ ይደረጋል።
- ክትትልና ግምገማ በባለጉዳዮች መሃከል ያለው የመረጃ ልውውጥ እንዲሻሻል አስተዋፅኦ ማድረግ አለበት

### 6.4.1 ክትትል

የክትትል ተግባራት በዋናኛነት የሚያተኩሩት/ የሚመለከቱት/ ፕሮጀክቱ/ፕሮግራሙ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ ይሳካሉ ተብለው የተገለፀ ራዕዮችና የተቀመጡ የረጅም ጊዜ አላማዎች ላይ ለመድረስ የታቀዱ የፕሮጀክት/ፕሮግራም ዝርዝር ተግባራትና ግብአቶች በተገቢው መንገድ መፈፀማቸውን በማረጋገጥ ላይ ነዉ። ይህም ማለት ፈፃሚው አካል የአፈፃፀሙን እርምጃ እንዲገመግምና በግዜ ሰሌዳው መሠረት መጓዙን ለማረጋገጥ ይችል ዘንድ ወቅታዊ ውሣኔዎች ለመውሰድ የሚያስችሉትን መረጃዎች ማቅረብና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ነው። በተግባራዊ ውጤቱ የክትትል አላማ የተቻለውን ያህል ከወዲሁ መቆጣጠርና ተገቢ እርምጃዎችን መወሰድ ማለት ነው። ቁጥጥሩ በፊዚካል በፋይናንስ ሊሆን ይችላል። የሁለቱም ዓይነት ቁጥጥሮች አላማዎች በዋናነት ፦

- በፕሮጀክቱ/ፕሮግራሙ የአፈፃፀም እቅድ / Action plan/ ውስጥ አስቀድሞ በተቀመጠው ግብ ወይመ ግምት ውስጥ መሆኑን መከታተል፣
- በታቀደው የአፈፃፀም የግዜ ሰሌዳ መሠረት ሲከናወን የሚከሰቱ ነገሮች የሚያስከትሉዋቸውን አሉታዊ ውጤቶች/ለማስተናገድ/ ለመቋቋም እንዲቻል ክስተቶችን መመዘን ታሳቢ ማድረግ እርምጃዎችን መወሰድ ፣

ለተወሰኑ ጊዜያት አላማዎችና ደረጃዎች የተወሰኑ መረጃዎችን ለማስገኘት የሚካሄዱ የተለያዩ የትክክልና የግመገማ አይነቶች አሉ።

## የክትትል አይነቶች

**የተግባር ክትትል፦** በሚፈጸሙ ተግባራት ላይ የሚታዩ ስህተቶችንና የማስተካከያ እርምጃዎችን የሚጠቁም ነው።

**የፋይናንስና ፊዚካል ክትትል፦** የተደረጉ ወጪዎች የተከናወነ ፊዚካል ሥራ ከእቅዱ ውጪ የተሰሩ/የተዛነፈ/ እና ለነዚህም የሚያስፈልገው እርምጃ ላይ ያተኩራል።

የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

**ልዩ የፍተሻ ጥናቶች፡-** በፕሮጀክት ሥራ ውስጥ እፈፃፀምን ይለያይ ይተነትናል ለመሻሻል የሚጠቅሙ ሃሳቦችን ያቀርባል።

**የተጠቃሚዎች ተሳትፎና በእካል በመገናኘት የሚደረግ ክትትል፡-** የሚፈለገውን ያህል የተሳትፎ ደረጃ መኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ማሻሻያዎችን ለማድረግ የተጠቃሚዎችን የተሳትፎ ደረጃ ተከታትሎ ለማወቅ የምንጠቀምበት ነው።

## የክትትል ሥርዓትን (ለመዘርጋት) መሪ መጠይቆች

1. በፕሮጀክቱ ላይ ክትትል የሚደረግባቸው ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
2. የፕሮጀክቱ ክትትል የሚደረገው ለማን ነው?
3. ምን ጉዳዮችና (ተግባራት) የስራ ፍሰቶች (ሂደቶች) ክትትል ይደረግባቸዋል?
4. እነዚህ ጉዳዮችና የስራ ፍሰቶች መቼ ክትትል ይደረግባቸዋል?
5. እነዚህ ጉዳዮችና የስራ ፍሰቶች እንዴት ክትትል ይደረግባቸዋል?
6. ጥሬ መረጃ እንዴት ይሰበሰባል?
7. ማን ይሰበስባቸዋል?
8. ጥሬ መረጃው እንዴት በአንድ ቦታ ተከማችቶ ይቀመጣል?
9. ጥሬ መረጃውን ማን ይተነትናል?
10. የተተነተነው ጥሬ መረጃ መቼ ይፈለጋል?
11. ውጤቶቹ እንዴት ይቀርባሉ?
12. ውጤቶቹ ለማን ይቀርባሉ?
13. ውጤቶቹን ማን ያቀርባቸዋል?
14. ውጤቶቹ ከቀረቡ በኋላ ምን ይደረጋል?

### 6.4.2 የግምገማ ተግባራት

ግምገማ በሚጠበቁ ምርቶች (Output) ውጤቶች (Effect) ለውጦች (Impact) መልክ የተቀመጡ ዓላማዎች (የአጭር ጊዜ) መሳካታቸውን ወይም ሊሳኩ የሚችሉ መሆኑን በማረጋገጥ ላይ ያነጣጠረ ነው። ይህም የተገኙ ውጤቶችን ወደ መመዘንና በሌላ አካባቢ ወደፊት ለሚካሄዱ ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች የሚበጁ ተሞክሮችን ወደ መለየት ያመራል። የምርት (Output) ደረጃዎች ማለት ፕሮጀክቱ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸው ቡድኖች (ክፍሎች) ግብዓቶችን ተጠቅመው ያመጡት ውጤት ስፍር (Measures) ማለት ነው። ይህን በሚመለከት ግመገማ ከፊዚካላዊ (ቁሳዊ) ምርቶች ዘልቆ ፕሮጀክቱ በተጠቃሚው

ማህበረሰብ ህይወት ላይ ያመጣውን ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ይለካል (ይሰፍራል)። በተጨማሪም በማህበረሰቡ ህይወት የመጣው ለውጥ ላይ ተፅዕኖ ያላቸውን ውጫዊ (ከፕሮጀክቱ ውጭ የሆነ) እና ውስጣዊ (በፕሮጀክቱ ውስጥ ያሉ) ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ። (ታሳቢ ያደርጋል)

የልማት ፕሮግራሙ ያመጣውን ለውጥ በትክክል ለመወሰን አፈፃፀሙ ከመጀመሩ በፊት ሁሉንም የሚዳስሱ (Cross-Sectional) እና ለፕሮግራሙ ዓላማዎችና ግብዓቶች ትርጉም ያላቸው(ተያያዥነት) ማህበረ-ኢኮኖሚ የመነሻ መስመር (Baseline) ጥሬ መረጃዎች ስብስብ መዘጋጀት አለበት። ይህም በልማቱ ስራ አፈፃፀም ውጤት ከማስገኘቱ በፊት ወይም በኋላ እንዲሁም በመሃል የማወዳደሪያ መሰረት ሆኖ ያገለግላል። በግምገማው ተመሳሳይ መረጃዎችን ሰብስቦ አንድ ላይ መያዝ አስፈላጊ መሆኑ እፅንኦት ሊሰጠው (ሊሰመርበት) ይገባል። በሚፈለገው መንገድ የተዘጋጀ የመነሻ ወሰል ጥሬ መረጃዎች ስብስብ መኖር በፕሮግራም አፈፃፀም ግመገማ ግዜ የተገኘውን ለውጥ ለማወዳደር የሚያስችል በጣም እውነተኛ (ትክክለኛ) መሰረት መሆኑን አረጋግጧል ለዚህም ነው (PA') ላይ በተለይ ያተኮረ የ IGAs potentioal & need assessment base line survey? የተግባር እንቅስቃሴ (intervention focus section) ትኩረት በሚለው የዚህ ክፍል ሪፖርት ውስጥ የተካተተው።

የግምገማ መለያ ባህሪያት አንዱ በውጭ አካል የሚፈፀም መሆኑ ሲሆን ክትትል የፕሮጀክት አፈፃፀም ዘር አንድ አካል የሆነ ተግባር ነው። ግመገማ የምርቱ (Output) (መነሻና) + ውጤት እና እነዚህን መነሻናውጤቶች በማስከተል ረገድ የፕሮጀክት ስራ አመራርና (ማኔጅመንት) የክትትል ስርዓቱ የነበራቸው ሚና በትክክል ያስቀምጣል።

አንድ የልማት ፕሮግራም እንዲገመገም ለተወሰነ ጊዜ ሲካሄድ መቆየት አለበት የተገኙት ምርቶች በሰዎች ህይወት ላይ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ ለመስጠት ይቻል ዘንድ ፕሮግራሙ በሚጀመርበትና ግምገማ በሚካሄድበት መሃከል በቂ ጊዜ እንዲያልፍ ማድረግ ያስፈልጋል። ፕሮጀክቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ በሚካሄዱ ተከታታይ ግመገማዎች መሀከል በቂ ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል። በዚህም መሰረት አንድ ፕሮግራም ከመጠናቀቁ በፊት ሁለት ግመገማዎችና ከተጠናቀቀ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ደግሞ አንድ ግምገማ ሊካሄዱ ይችላሉ።

## የግምገማ ዓይነቶች

**የመነሻ ግምገማ** - ፕሮጀክት ሃሳብን ለማዳበር የሚያስፈልጉ ጥሬ መረጃዎችን በቅድሚያ የማሰባሰብ ስራ ያካትታል።

**በሂደት የሚደረግ ግምገማ** - ቁልፍ የሆኑ ውሳኔ ሰጪዎች በሚያስፈልጓቸው መረጃዎች ላይ ያተኩራል። ለምሳሌ በፕሮጀክት ዕቅድ ለውጥ ማድረግ። በዚህ በደረጃ የሚኖር ግምገማ የመካከለኛ ጊዜ ውጤቶች ለመመዘንም ይደረጋል።

**የማጠቃለያ (የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ) ግምገማ** - ይህ ፕሮጀክቱ መገባደጃ ላይ የፕሮጀክቱን አጠቃላይ ውጤት ወይም ጠቀሜታ ለመመዘን የሚካሄድ ነው። ፕሮጀክቱ የአጭር ጊዜ ከሆነ ወይም ሌላው ቀጣዩ የፕሮጀክቱ ምዕራፍ ከመጀመሩ በፊት ከሆነ የድህረ-ግምገማ ምትክ ሆኖ ሊከናወን ይችላል።

**የድህረ-ፕሮጀክት ግምገማ** - ይህ ዓይነት ግምገማ ፕሮጀክቱ የሚያስገኛቸው ጥቅሞችና ለውጦች ዕውን ይሆናሉ ተብሉ በሚጠበቀው ጊዜ ማለትም ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ የሚደረግ ነው። በዚህ ደረጃ የሚደረግ ግመገማ አጠቃላይ ውጤቶችን ይመዝናል። ለቀጣይ የፕሮጀክት ዕቅዶች ግብዓት የሚሆኑ ተሞክሮች (ትምህርቶች) ይሰጣል።

## በፕሮግራም ግምገማ በጣም አስፈላጊ የሆኑ መጠይቆች :-

1. ግብዓቶቹ በበቂ ሁኔታ ዝርዝር ተግባራቱን ለመፈፀም አገልግለዋል (ጠቅመዋል)?
2. ዝርዝር ተግባራቱ ወደሚፈለጉት ውጤቶች አድርሰዋልን?
3. የተገኙት ውጤቶች (የረዥም ጊዜ) አላማዎችን ለማሳካት ምን ያህል ጠቅመዋል?
4. በተግባር የፕሮጀክቱ የተለያዩ ክፍሎች (አካላት) አቀማመጥ ትርጉም ያለው (የሚሰጥ) ነበርን?
5. (ያልተፈለጉ/ያልታቀዱ) ምን ሌሎች ውጤቶች ከፕሮጀክቱ ተገኝተዋል?
6. በአሁኑ ጊዜ ምን ለውጦችና አዝማሚያዎች በተጠቃሚውና በአጠገቡ ባሉ አካባቢዎች ይታያሉ?
7. እነዚህ አዝማሚያዎች ፕሮጀክቱ የሚያሳርፈው ተፅዕኖ ከከተመ በኋላ የሚቀጥሉ ናቸውን?

8. የተገኙት ጠቀሜታዎችለሁሉም በሚገባ የተዳረሱ ናቸውን?
9. በፕሮጀክት ቀረፃውና አፈፃፀም ውስጥ ምን ነገሮች በትክክል ወይም በጥሩ ሁኔታ ሄደዋል?
10. የትኞቹ ግምቶች (Assumputions) ዕውን የትኞቹ ደግሞ አልሆኑም?
11. ምን ነገሮች በተሳሳተ ወይም ጥሩ ባልሆነ መንገድ ሄዱ ወይም ተበላሹ? ለምን?
12. ከሌሎች ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች አኳያ የተሻለ ወይስ የባሰ አከናወንን? እና ለምን?
13. በሌሎች ፕሮጀክቶች ምን ነገሮች በተለየ መንገድ እንሰራለን?
14. የፕሮጀክታችን ውጤቶች የችግር ትንተናችንና የተሳታፊዎች ትንተናችንን ትክክለኛነት አረጋግጠዋልን?
15. የፕሮጀክታችን ውጤቶች (የአጭር ጊዜ Objectives) ዓላማዎቻችን ለይተን ያስቀመጥንበት ሁኔታ ትክክለኛነት አረጋግጠዋልን?
16. የክትትል ሥርዓታችን ፕሮጀክቱን በሚገባ አገልግሏልን? ካልሆነ በምን መንገድ ሊሻሻል ይችል ነበር?
17. የትኞቹ ድርጅቶች/ተቋማት ለፕሮጀክቱ ድጋፍ ሰጡ ወይም መሰናክል ሆኑ? እና ለምን?
18. የፕሮጀክቱን እንቅስቃሴና ውጤቶች ያገኙ ወይም የደገፉ ምን ሰወች ነበሩ?

ሰንጠረዥ 3 :- በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች ውስጥ ዋና ዋና ጉዳዮች ችግሮችና የመፍትሄ ሀሳቦች ማጠቃለያ :-

| ርዕስ ጉዳይ | ችግር | የመፍትሄ ሀሳቦች |
|---|---|---|
| ድሃውን የሚደግፍ የመንግስት ወጪ መመደቡን ማረጋገጥ (የመለየት ስራ) | አንዳንድ ድሃን ለመደገፍ የሚወጡ ወጪዎች ከቀልጣፋ አሰራርና ከዕድገት ዓላማዎች ጋር የሚጋጩ ሊሆኑ ይችላሉ። | የመንግስት ወጪ ህዝቡ በስፋት የሚፈልጋቸው ድሃ ገበሬዎች የማይፈልጋቸው ሸቀጦች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ፣ |
| | | በክልሎች መሀከል ያሉ በመንግስታዊ ወጪዎች ረገድ ያለ አለመመጣጠን ማስተካከል ለክልሎች የሚመደበው ወጪ ባለው የድህነት ሁኔታና በድሆች ቁጥር ከኢንቨስትመንት ዝቅተኛነት እና አማራጮች የሚያቀርቡ መኖር አለመኖር (የግሉ ሴክተር) መሰረት መወሰን ፣ |
| | | በጣም ለራቁና ዝቅተኛ የማደግ ወይም የሀብት አቅም ላላቸው አካባቢዎች የተለየ ትኩረት መስጠት መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከግሉ ሴክተር ጋር አጋርነት በመመስረት ገበያዎችና አገልግሎቶች የሚያገኙበትን ዕድል (መንገድ) ለመክፈት መጣር፣ |
| ስልጣንን በተዋረድ ማከፋፈል | በተዋረድ ታች ባሉ አካላት የሚካሄዱ ፕሮግራሞች ከድሃው ችግርና ከገበሬዎች ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ ችግሮቻቸውን ለመፍታት የበለጠ ተስማሚ ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም የአካባቢ መስተዳድሮች የሴክተር ፕሮግራሞች ለመፈፀም የሚያስችላቸው በቂ ስልጣንና ሀብት ላይሰጣቸው ይችላል። ብዙ ጊዜ በአካባቢ ደረጃ አቅም ደካማ ነው። የክፍያና አዲት ስርዓቶች ተስማሚ ላይሆኑ ይችላሉ። | ለአካባቢ መስተዳድሮች በቂ ሀብት መመደቡን ማረጋገጥ፣<br><br>የማዕከላዊና የአካባቢ መንግስታት ተግባርና ኃላፊነቶችን ግልፅ አድርጎ መለየት ፣<br><br>በአካባቢ ደረጃ አቅም ማሳደግና ባለሙያዎች (ሰራተኞች) ከማዕከላዊ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ወደ የአካባቢው ማዛወር ፣<br><br>በአካባቢው መስተዳድሮች ወጥ የሆኑ የወጪ የማድረጊያ ቅደም ተከተልና ጠንካራ የኦዲት አሰራር ተግባራት ማድረግ፣ |
| የባለጉዳዮች ተሳትፎ | የባለጉዳዮች ተሳትፎ ቀደሚ ተግባራትን ለመለየት ተጠያቂነት ለማረጋገጥና የፕሮግራም አፈፃፀም ለመገምገም ጠቃሚ ነው። ሆኖም መንግስታዊ አካላት ብዙውን ጊዜ እውነተኛ ተሳትፎን ለመጋበዝ ያመነታሉ።<br><br>የሁሉንም ባለጉዳዩች በቂ ውክልና ማረጋገጥ አስቸጋሪ ነው። ቢያንስ ድሃ ገበሬዎች በአግባቡ ተወክለዋል፣ | በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ባለጉዳዮችን የማማከር አስፈላጊነት የሚጠይቁ አሰራሮች ማስገባት ፣<br><br>ተስማሚና ሁሉን የሚያካትቱ ባለጉዳዮችን የማመከሪያ ስልቶችን ማውጣት ፣<br><br>የድሃ ገበሬዎች በማንኛውም ደረጃ እንዲደራጁ ንቁ ድጋፍ መስጠት ፣ |

| ርዕስ ጉዳይ | ችግር | የመፍትሄ ሀሳቦች |
|---|---|---|
| የድሆችን ፍላጎት የሚያሟሉ ቅድሚያ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚለዩበት ሁኔታ ማሻሻል (ማስተካከል) የመለየት ስራ፣ | ህዝባዊ አገልግሎት ሰጪዎች ድሃውን በማገልገል ያስመዘገቡት ውጤት ደካማ ነው። የሚሰጡትም አገልግሎት የድሆችን ፍላጎት የሚመለከት አልነበረም። | እያንዳንዱ ህዝባዊ አገልግሎት ቀዳሚ ተግባራት የህዝቡን ፍላጎት የሚያንፀባርቁ መሆኑን ማረጋገጥ |
| ዋጋን ማስመለስ | ማንኛውም አገልግሎት ዋጋውን በሚመልስ አግባብ የሚሰጥ ከሆነ የህዝባዊ አገልግሎቶችን ውጤታማነት ከማሳደጉም በተጨማሪ የግሉ ሴክተር የሚያቀርባቸውን አገልግሎቶች እንዲያሳድግ ያበረታታል። ሆኖም ድሃ ገበሬዎች እነዚህን አገልግሎቶች እንዲያሳድግ ያበረታታል። ሆኖም ድሃ ገበሬዎች እነዚህን አገልግሎቶች ለመግዛት አቅም ላይኖራቸው ይችላል። | ለድሃ ገበሬዎች የአገልግሎት ክፍያ የማይከፍሉበትን አማራጭ አሰራር ማየት በድህነት በጣም በተጎዱ አካባቢዎች ዋጋን የማስመለስ አጠቃለይ ደረጃን መቀነስ ፣<br><br>ለመሰረታዊና ለልዩ አገልግሎቶች የሚመደበውን የአገልግሎት ክፍያ ደረጃ የተለያዩ ማድረግ ፣ |
| የአፈፃፀም ግምገማ | የአፈፃፀም ክትትል ስርዓ ቶች ከድህነት ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች የላቀ አፅንኦት መስጠት አለባቸው። | የድህነት ጥሬ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለመተንተን ስራ ከፍተኛ አፅንኦት መስጠት (አሃዛዊ ስፍሮች (Measures) የተጠቃሚዎች ግምገማ ተሳትፏዊ ይሁንታ (approval) ወዘተ. |

## ሠንጠረዥ 4 ፦የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ አወጣጥ እርምጃዎች

| እርምጃ | ዝርዝር ጉዳዮች | ማን/ይፈፅማል/ | ለተቋማዊ አቅም እንድምታዎች |
|---|---|---|---|
| ድህነትና ችግሮችን መገንዘብ | አይነታዊ /አሃዛዊ ያልሆኑ/ አሳታፊ የድህነት ምዘና አሳታፊ የገጠር ምዘና አሁን ያሉ አገልግሎት አቅራቢዎች ፖሊሲዎች ወዘተ… | መንግሥት ለዩኒቨርስቲ መንገዶችና ለአገር ውስጥ አማካሪዎች ኮንትራት መስጠት ፣ የመንግስት ሃላፊዎችን ማሳተፍ ፣ | አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የአገር ውስጥ እውቀት መጠቀም በእለም አቀፍ ባለሙያዎች እንዲደገፍ ማድረግ ከረዥም ጊዜ አንፃር እነዚህን አገልግሎት የሚሰጡ አገር በቀል ተቋማት መፍጠር ማጠናከር |
| ከባለ ጉዳዮች ጋር ምክክር ማድረግ | ባለጉዳዮችን መለየት ብሄራዊ ከሆኑ ባለጉዳዮችና ተጠቃሚዎች ጋር ምክክር ዋጋ መመለሳቸውን ማረጋገጥ ድሆች የራሳቸውን ችግር /ፍላጎት መለየት አለባቸው | አካባቢያዊና ብሄራዊ መንግስት ከተቻለ መያዶች ማህበረሰባዊ መሠረት ያላቸውን ድርጅቶች ጋር በመሆን ማህበረሰቡን በሰፊው የሚወክሉ አካላት /ስብሰቦች/ ማቋቋም | የድሃው ድምፅ ማሰማትና እንዲሰማ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ህዝቡን በሰፋት በአካልነት ያቀፉ ድርጅቶችን አቅም መገንባት ፣ |
| ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ችግሮችና ተግባራት መለየት ፣ | የባለጉዳዮችን አመለካከት /አስተያየት/ ማንፀባረቅ አለባቸው ፣ | ኮሚቴና እርዳታ ሰጪዎች ፣ | የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የፖሊሲ ክፍል አቅም ማጠናከር ፣ |
| ከእርዳታ ሰጪዎች ጋር ምክክር ማድረግ | በፖሊሲ አቅጣጫ ላይ የእርዳታ ሰጪዎችን ስምምነት ማግኘት እንዲሁም እርዳታው የሚሰጥበት ዘር የበጀት አመት ስለሪፖርት አቀራረብ ይዘት፣ በራስ ተነሳሽነት የባለቤትነት ስሜት ስለሚፈፀሙ ተግባራት፣ (በእርዳታ ሰጪዎች ሳይሆን በመንግስት) | ኮሚቴና እርዳታ ሰጪዎች ፣ | ብዛት ያላቸውን እርዳታ ሰጪዎችና ተግባራትን ለማስተባበር ቀላል ነው። |
| አሁን በመካሄድ ላይ ባሉ ፕሮግራሞች ላይ የሚያስፈልጉ ለውጦችን መዳሰስ | ለውጦቹን ማጠናቀቅና መውጣት እንደገና ማዋቀር ወይም እንዳሉ ማስቀጠልን ወዘተ ሊያካትቱ ይችላሉ። | መንግስትና ሌሎች ሙያዊ ዕውቀት ፣ | አሁን ባሉ ተቋማት የሚታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ለይቶ ማወቅ ተስማሚ የሆኑ ተቋማዊ አቅምን የሚጠናከር ሥራ መሥራት። ለምሳሌ ሥልጣን የሥራ አመራር ሥርዓት ፣ |
| ፕሮግራም ማፅደቅ | | የካቢኔት የፓርላማ ኮሚቴዎች | |

| እርምጃ | ዝርዝር ጉዳዮች | ማን/ይፈፅማል/ | ለተቋማዊ አቅም እንድምታዎች |
|---|---|---|---|
| የሙከራ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ማድረግ (ማካሄድ) | በትንሹ ጀምሮ ከልምድ እየተማሩና አስፈላጊውን ማስተካከያ ማድረግ ፣ | በኮንትራት መስጠት ለወረዳ ወይም ለሌላ መንግስት ሰራተኞች ፣ | ሙከራዎች የፈፃሚ አካላትን አቅም ያጠናክራሉ ፣ |
| መከታተልና መገምገም | የተገኙ ለውጦች (Impact) ምዘናን ማካተት | ተጠቃሚዎች ፈፃሚ አካል(ላት) የአካባቢው መስተዳድር) | የማኔጅመንት መረጃ ስርዓቶች የአቅም ግንባታ |

(ደባል) መድብል 1 ፡- በኢትዮጵያ የገጠር ድህነት ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት

| ተቋማዊ ድጋፍ | ማነቆ | መደረግ የሚገባው |
|---|---|---|
| ፌደራል | | |
| ዘመናዊ ግብዓቶችን ዘላቂነት ባለው መንገድ ማሰራጨት ፣ | በግብዓት ስርጭት ውስጥ ሊሳተፍ የሚችል ዘላቂነት ያለው ተቋም አለመኖር ፣<br><br>ውስጥ የምርምር አቅም፣<br><br>ቀርፋፋ (ቀልጣፋ ያልሆነ) የምርትና ግብዓት ግብይት ፣<br><br>ዘመናዊ ግብዓቶች ለመጠቀም የሚያስችል በቂ ስልጠናና ትምህርት አለመኖር ፣ | የህብረት ስራ ማህበራት ማጠናከር ፣<br><br>የገጠር ፋይናንስን ማጠናከር ፣<br><br>የኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን ጥራት ማሻሻል፣<br><br>የምግብ ዋስትና ችግሮች የሚቀርፍ ምርምር ማካሄድ፣<br><br>የግብርና ሚኒስቴርንና ክልላዊ የምርምር ተቋማትን አቅም መገንባት፣<br><br>ለግብዓት መግዣ የሚሰጠውን ብድር በፋይናንስ ረገድ በማይጎዳ መንገድ ማስተዳደር፣ |
| ምቹ የትራንስፖርትና መገናኛ | በደንብ ያልተገነቡ መንገዶች ፣<br><br>በትርፍ አምራች አካባቢዎች ለግብረና ምርቶች ያለው ዋጋ ዝቅተኛ መሆን ፣<br><br>የበቂ ምርት ጉድለት ባለባቸው አካባቢዎች ለግብርና ምርቶች ያለው ዋጋ ከፍተኛ መሆን ፣ | የአዳዲስ መንገዶች ግንባታ ፣<br><br>የመንገዶች ጥገና<br><br>የገበያ መረጃ ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ ፣ |
| የገጠር ፋይናንስ | በመደበኛ ባንኮች ለድሆች የሚሰጠው የፋይናንስ አገልግሎት ውስን መሆን ፣<br><br>የብድርና ቁጠባ ህብረት ስራ ማህበራት ቁጥር ውስን መሆን ፣<br><br>የህብረት ስራ ማህበራትን የሚከታተለው የመንግስት አካል አቅም ውስን መሆን ፣ | |
| | የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት የአገልግሎት አድማስ ውስን መሆን ፣<br><br>መደበኛ ላልሆነውና በከፊል መደበኛ የኢኮኖሚው ክፍል የሚሰጠው ትኩረት ውሱን መሆን | የብድር ካፒታል ማቅረብና የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማትን አቅም መገንባት ፣<br><br>መደበኛ ባልሆነው ሴክተር ምርምር (ጥናት) ማድረግ |

| ተቋማዊ ድጋፍ | ማነቆ | መደረግ የሚገባው |
|---|---|---|
| ምርምር | ደረቅና በከፊል ደረቅ በሆኑ አካባቢዎች የሚደረገው ምርምር ውሱን መሆን ፤<br><br>በምርምርና በኤክስቴንሽን መካከል ደካማ ትስስር ፤<br><br>የምርምር ተቋማት አቅም ውሱንነት ፤ | በየክልሉቹ ላሉት የምርምር ተቋማት ድጋፍ መስጠት ፤<br><br>የምርምር ተቋማትን አቅም መገንባት ፤<br><br>በምርምርና ኤክስቴንሽን መሀከል ትስስሩን ማጠናከር ፤ |
| የህዝብ ብዛት | ከፍተኛ የህዝብ ዕድገት (ምጣኔ) ፤<br><br>በቤተሰብ ዕቅድ አኳያ ያለው ስራ ውስን መሆን ፤ | የቤተሰብ ዕቅድን ተግባራዊ ማድረግ ፤<br><br>ስራተኛው (ህዝቡ) ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ ለመስራት ያለበትን ማነቆዎች ማስወገድ ፤ |
| የሴቶችን ሁኔታ ማሻሻል | በቤተሰብ ደረጃ ለሚያዙ እንደ መሬት ያሉትን ለማግኘትና ለመጠቀም ያላቸው ዕድል ውሱን መሆን ፤<br><br>በልማት ስራዎች የሴቶች ተሳትፎ አናሳ መሆን ፤<br><br>በልጅነት ማግባት (ያለ ዕድሜ ጋብቻ) | ለሴቶች የፋይናንስ አገልገሎት ማቅረብ ፤<br><br>ሴቶችን ማስተማር ፤<br><br>ስልጠና መስጠት ፤<br><br>ስለ ፆታ ጉዳዮች እውቅና መፍጠር፡<br><br>ስለሴቶች አዎንታዊ የሆነ የማስተዋወቅ ስራ መስራት ፤ |
| የገቢ ማስገኛ ስራዎች | ውሱን የሙያ ዕውቀት ወይም የስልጠና ማጣት ፤<br><br>የመንቀሳቀሻ ገንዘብ (ካፒታል) እጥረት ፤<br><br>ውሱን (ጠባብ) ገበያ፤ | በመያዶችና በመንግስት ተቋማት ወይም በሌሎች አማካይነት ስልጠና መስጠት ፤<br><br>የፋይናንስ ሀብት የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፤<br><br>በመሸጥ ሆነ በመግዛት (በግብይት) marketing ድጋፍ መስጠት፡ |
| የከብት ሀብት | ውሱን የመኖ ሀብት፤<br><br>የምርቶቻቸው እምቅ አቅም ዝቅተኛ የሆኑ ዝርያዎች ፤<br><br>በሽታ ፤<br><br>ባህላዊ (ተለምዷዊ) የሆነ አያያዝ ፤<br><br>በቂ ገበያ(ግብይት) አለመኖር ፤ | ምረምር ፤<br><br>የከብት ሀብት ኤክስቴንሽን ማሻሻል ፤<br><br>ሥልጠና ፤<br><br>የከብት ገበያ ማሻሻል፡ |
| የምርቶች ግብይት | ደካማ የንግድ ሴክተር<br><br>(ውስን ውድድር ያለበት) በሞኖፖል የተያዘ የምርቶች ግብይት ፤<br>ውሱን ካፒታል ፤<br>ውሱን ስልጠና ፤ | የግሉን ሴክተር በልምድ ልውውጥ ጉብኝቶችና ስልጠና ድጋፍ መስጠት ፤<br><br>ብድር በቀላሉ የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር ፤<br>ስልጠና መስጠት ፤<br>የገበያ መረጃ ስርዓትን ማጠናከር፡ |
| የምግብ እርዳታ | ትጋትን የመቀነስ ወይም የማዳከም ውጤት ፤ | ተገቢ የመለየት ስራና ክትትል፤ |

| ተቋማዊ ድጋፍ | ማነቆ | መደረግ የሚገባው |
|---|---|---|
| በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስተናን መከታተል፣ | ያልተሟላ (በቂ ያልሆነ) የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ፣<br><br>ደካማ የመለየት ስራ | በየአካባቢው በጥቃትን ደረጃ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ማደራጀት ፣ |
| መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ) ተግባራት | ከየአካባቢው መስተዳድር ጋር ያላቸው የትብብር ስራ ደካማ መሆን ፣ | በመንግስትና በመያዶች መሀከል አዲስ አጋርነት መፍጠር (ማቋቋም) |
| የመሬት ይዞታ | በይዞታ (ዋስትና) አለመኖር ፣<br><br>በመሬቱ ላይ ኢንቨስት ለማድረግ (ለመንከባከብ) ፍላጎትና ትጋት ማጣት ፣<br><br>የመሬት ለምነት መሟጠጥ ፣<br><br>የመሬት ይዞታ እያነሰ መሄድ ፣<br><br>የመሬት መበጣጠስ ፣<br><br>ወደ ግብርና የሚፈሰው የግል ኢንቨስትመንት ውሱን መሆን ፣ | አሁን ባለው የመሬት ይዞታ ላይ ምርምር (ጥናት) ማካሄድ ፣<br><br>ለየክልሉች የሚስማማ የተለያየ የመሬት ይዞታ ስሪት ማውጣት |
| በማክሮ ደረጃ የፖሊሲ አጠቃላይ ሁኔታ ፣ | በሚከተሉት ተስማሚያዊ ባልሆኑ ፖሊሲዎች ምክንያት በማክሮ ኢኮኖሚው ውስጥ ያሉ መዛነፎች ፣<br><br>የክትትል ፖሊሲ ፣<br><br>የፊሲካል ፖሊሲ ፣<br><br>የንግድ ፖሊሲ ፣<br><br>የልውውጥ (Exchange) ፖሊሲ | የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በቤተሰብ ደረጃ ባለ የምግብ ዋስትና ላይ ያላቸው ተፅዕኖ (ውጤት) ማጥናት ፣ |

ደባል (መድብል) 2 ፦ ዕለታዊ የነፍስ ወከፍ ካሎሪ በምግብ መደብ መኖሪያ

| የምግብ መደብ | ዕለታዊ የነፍስ ወከፍ ካሎሪ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አገር | | ከተማ | | ገጠር | |
| | 95/96 | 99/00 | 95/96 | 99/00 | 95/96 | 99/00 |
| ጥራጥሬዎች | 1313 | 1413 | 1349 | 1486 | 1114 | 978 |
| የወጥ እህሎች | 225 | 178 | 229 | 186 | 204 | 128 |
| የቅባት እህሎች | 11 | 7 | 12 | 7 | 4 | 2 |
| የዳቦና ፓስታ ምርቶች | 34 | 38 | 11 | 10 | 160 | 205 |
| ስጋና ዓሳ | 14 | 18 | 9 | 15 | 42 | 41 |
| ወተት ፣ እይብና እንቁላል | 24 | 24 | 25 | 26 | 16 | 15 |
| ዘይቶችና ቅባቶች | 50 | 37 | 34 | 23 | 142 | 119 |
| ቅጠላቅጠሎችና ፍራፍሬዎች | 37 | 34 | 37 | 34 | 38 | 34 |
| ቅመማ ቅመሞች | 43 | 25 | 42 | 24 | 47 | 27 |
| ድንች ፣ እንሰትና ሌሎች ስራስሮችና ግንዶች ፣ | 113 | 170 | 123 | 421 | 60 | 71 |
| ከቤት ውጭ የሚወሰዱ ምግቦች | - | 7 | - | 4 | - | 23 |
| ሌሎች ምግቦች | 35 | 29 | 29 | 22 | 71 | 73 |
| ቡናና ሻይ | 36 | 26 | 39 | 29 | 18 | 11 |
| ለስላሳ መጠጦች | 5 | 6 | 5 | 6 | 6 | 11 |

Zenaselassie Siyoum (2001)

ደባል/መድብል/ 3 ፦ የቤተሰቦች ስርጭት በፐርሰንት ከአቅራቢያው ት/ቤት ያላቸው ርቀት በኪ.ሜ በመኖሪያ ቦታ በት/ቤቶች ደረጃና በጥናት ዓመት

| የት/ቤት ደረጃ/ የመኖሪያ ቦታ | ከአቅራቢያው ት/ቤት ያለው ርቀት በኪሎ ሜትር | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከአንድ ያነሰ | 1-4 | 5-9 | 10-14 | 15-19 | ሃያና ከሃያ በላይ |
| አገር/አንደኛ ደረጃ | | | | | | |
| 1996 | 26.9 | 44.3 | 19.9 | 5.8 | 1.8 | 1.3 |
| 1998 | 24.7 | 46.0 | 22.5 | 4.1 | 1.9 | 0.9 |
| 2000 | 19.9 | 54.1 | 20.9 | 3.3 | 1.0 | 0.5 |
| ሁለተኛ ደረጃ | | | | | | |
| 1996 | 709 | 10.4 | 14.0 | 9.8 | 13.5 | 43.5 |
| 1998 | 5.1 | 13.0 | 14.4 | 11.8 | 13.4 | 42.2 |
| 2000 | 4.4 | 14.6 | 14.8 | 13.2 | 13.2 | 39.9 |
| ገጠር/አንደኛ ደረጃ | | | | | | |
| 1996 | 19.1 | 46.9 | 23.4 | 6.9 | 2.2 | 1.6 |
| 1998 | 19.2 | 46.7 | 26.1 | 4.7 | 2.2 | 1.0 |
| 2000 | 0.9 | 6.8 | 16.0 | 15.5 | 15.2 | 45.3 |
| ሁለተኛ ደረጃ• | | | | | | |
| 1996 | 1.0 | 5.0 | 15.1 | 11.4 | 15.4 | 50.6 |
| 1998 | 1.1 | 6.3 | 15.6 | 13.8 | 15.4 | 47.8 |
| 2000 | 0.9 | 6.8 | 16.0 | 15.5 | 15.2 | 45.3 |
| ከተማ/አንደኛ ደረጃ | | | | | | |
| 1996 | 70.4 | 29.2 | 0.3 | - | - | 0.1 |
| 1998 | 54.4 | 41.5 | 0.6 | - | - | 0.3 |
| 2000 | 48.1 | 50.5 | 1.0 | - | - | - |
| 1996 | 43.7 | 40.6 | 5.7 | 0.9 | 3.2 | 5.9 |
| 1998 | 29.4 | 53.5 | 7.4 | 0.2 | 1.1 | 8.2 |
| 2000 | 24.9 | 61.1 | 7.6 | 0.1 | 1.4 | 4.5 |

Zenaselassie Siyoum (2001)

ደባል/መድብል/ 4 ፦ በላፉት ሁለት ወሬት የጤና ችግር ያጋጠመው የሀዝብ ብዛት ሥርጭት ፐርሰንት በወጪ፣ qurnitile, የመኖሪያ ቦታና የጥናት ዓመት

| ወጪ ኩንታሊ | የመኖሪያ ቦታና የጥናት ዓመት | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አገር | | | ገጠር | | | ከተማ | | |
| | 1996 | 1998 | 2000 | 1996 | 1998 | 2000 | 1996 | 1998 | 2000 |
| 1 | 20.9 | 36.9 | 30.5 | 21.0 | 36.9 | 30.8 | 2.2 | 37.7 | 27.5 |
| 2 | 19.0 | 35.5 | 27.8 | 19.1 | 36.0 | 28.6 | 18.0 | 30.6 | 20.2 |
| 3 | 18.6 | 35.4 | 26.6 | 18.9 | 36.0 | 27.6 | 15.8 | 30.3 | 18.5 |
| 4 | 18.0 | 35.7 | 27.0 | 18.9 | 37.1 | 28.3 | 12.6 | 27.3 | 18.5 |
| 5 | 14.1 | 32.5 | 24.9 | 15.3 | 35.1 | 27.2 | 11.5 | 23.1 | 17.7 |
| ድምር/ጠቅላላ/ | 18.1 | 35.1 | 27.2 | 18.8 | 36.4 | 28.4 | 14.3 | 27.1 | 19.5 |

ምንጭ፡ ሄና ሥላሴ ሰዮም /2001/

ደባል/መድብል/ 5 ፦ የጤና ሁኔታ ምክር ባለፉት ሁለት ወሬት ያገኘ ህዝብ ብዛት ስርጭት ፐርሰንት በወጪ qunitile እና የመኖሪያ ቦታ እና የጥናት ዓ መት

| ወጪ ኩንቲሊ | የመኖሪያ ቦታና የጥናት ዓመት | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አገር | | | ገጠር | | | ከተማ | | |
| | 1996 | 1998 | 2000 | 1996 | 1998 | 2000 | 1996 | 1998 | 2000 |
| 1 | 30.4 | 35.4 | 32.4 | 30.8 | 34.5 | 30.2 | 47.7 | 47.7 | 53.6 |
| 2 | 40.7 | 40.2 | 38.6 | 37.8 | 38.7 | 36.8 | 70.6 | 61.2 | 64.4 |
| 3 | 48.5 | 42.4 | 39.5 | 47.0 | 39.9 | 37.6 | 65.8 | 68.3 | 64.6 |
| 4 | 59.5 | 44.3 | 44.3 | 57.8 | 41.2 | 41.6 | 75.8 | 68.9 | 70.5 |
| 5 | 69.4 | 53.4 | 49.6 | 65.1 | 48.0 | 45.0 | 82.1 | 76.1 | 72.5 |
| ድምር ጠ | 49.1 | 43.4 | 41.1 | 46.4 | 40.5 | 38.3 | 70.7 | 68.3 | 66.6 |

ደባል/መድብል/ 6 ፦ ኤሌትሪክን ለበበራት የተጠቀሙ ቤተሰቦች ብዛት ፐርሰንት በመኖሪያ ቦታ በጥናት ዓመት ።

የድህነት ሁኔታ በኢትዮጵያ

| የመኖሪያ ቤት | የመብራት ምንጭና የጥናት ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የኤሌክትሪክ | | | ሌላ ምንጭ | | |
| | 1996 | 1998 | 2000 | 1996 | 1998 | 2000 |
| አገር | 9.3 | 11.0 | 10.8 | 90.7 | 89.0 | 89.2 |
| ገጠር | 0.7 | 1.2 | 0.9 | 99.3 | 98.8 | 99.1 |
| ከተማ | 57.4 | 70.1 | 70.0 | 42.6 | 29.9 | 30.0 |

Zenaselassie Siyoum (2001)

Schubert R. (1994). Poverty in developing countries: Its definition, extent and implications. Economics. A biannual collection of German studies Vol 49/50 PP. 17-40

Suzanne Piriou-Sall (1997) decentralization and rural development: A review of evidence (draft) World Bank

Transitional Government of Ethiopia, Transitional period charter of Ethiopia, Negaret Gazeta No. 1 50 year Addis Ababa.

Transition Government of Ethiopia proclamation to provide for the establishment of national/regional self-government proclamation No. 7/1992"Negarit Gazeta" No. 2/51 year Addis Ababa.

Transitional government of Ethiopia " A proclamation to define the powers and duties of the central and regional executive organs of the Transitional Government of Ethiopia "Proclamation No. 41/93 Negarit Gazeta 51[nd] year No. 7 Proclamation 33/92 Addis Ababa.

Transitional government of Ethiopia " A proclamation to define the powers and duties of the central and regional executive organs of the Transitonal Government of Ethiopia "Proclamation No. 41/93 Negarit Gazeta 52[nd] year

Wolday Amha (1998) Addressing food security constraints in rural Ethiopia. A study for FAO's Special Program for Food Production (SPFP) and the Ministry of Agriculture, Addis Ababa

World Bank (1999) Decentralization: on line sourcebook. Regional TOT workshop on decentralization, Kampala, Uganda

World Bank (2001) World Developmetn Report 2000/2001: Attaching Poverty. The World Ban, Washington D.C

World Bank (2001) Economic and Socail conditions of Ethiopia. A paper presented in a workshop and training course on public intervention for poverty reduction and PRSP in Ethiopia. ECA Addis Ababa.

World Bank (2001) can Afrca claim the 21st countury? The World Bank, Washigton D.C.

**References:**

Ababe Shimeles (2001) Theory and methods of poverty analysis. A paper presented in a workshop and training course on public intervention for poverty reduction and the PRSP in Ethiopia, ECA, Addis Ababa

Alemayehu Assefa (1998), Participatory Monitoring, Evaluation and Reporing, PACT-Ethiopia, The Ethiopian NGO Sector Enhancement Initiative

Bambergor M. (1996) key issues in the design and management of targeted poverty alleviation programs. In: M. Bamberger, A. Yahie, and G.Matovu. The Design and management of poverty reduction programs in Anglophone Africa. The world Bank Washington D.C

Bereket Kebede and Mekonnen Tadess (1996). The Ethiopian Economy: Poverty and Poverty allevation. Proceedings of the Fifth annual conference on the Ethiopian Economy: Addis Ababa

Clay D.C Molla D. and Habtewold D. (1998) Food aid targeting in Ethiopia: A study of household food security and food aid distribution. Working paper 12, GMRP, Ministry of Economic Development and Cooperation, Addis Ababa

Dercon S (1999) Linking qualitative and Quantitative information on changes in poverty in rural Ethiopia 1989-1995: Preliminary findings. Centre for the study of African Economies, Oxford.

Dercon S (2000) Changes in poverty and social indicators in Ethiopia in the 1990s: (at lest) some good news from Ethiopia.

Dercon S and P. Krishanan (1998) Changes in Poverty in rural Ethiopia in the 1989-1995: Measures, robustness tests and decompostiton. Centre for the Study of African Economies Oxford.

Dercon S and P Krishman (1996) A consumption based measure of poverty for rural Ethiopian in 1989 and 1994. In Bereket Kebede and Mekonnen Taddesse (eds). The Ethiopian Economy: Poverty and Poverty alleviation. Proceedings of the fifth annual conference on the Ethiopian economy. Addis Ababa

Edgerton. J. K. McClean, C.Robb, P. Shah S. Tikare (2000), Participatory process in the Poverty Reduction Strategy. (Draft)

Hailu Wondafrash (2001) Household based rural micro-entrprises development program. A study prepared for CARE/Ethiopia.

Karijn de jong, christane Loquai, and Jina Soiri (1999) decentralization and poverty reduction: Exploring the linkages. IDS, University of Helshinki, Helsinki,

Lipton M. (1985) The poor and the poorest: Some interim findings, World Bank Discussion papers. The World Bank Washington D.C

Lipton M and Ravllion M (1993) Poverty and Policy Research Working papers. The World Bank. Washington D.C

Mekonnen Taddesse, Abebe Shimeles and Bereket Kebede (2001). Poverty profile of Ethiopia. A paper presented in a workshop and training course on public interventions for poverty reduction and the PRSP in Ethiopia ECA, Addis Ababa

Ministry of Economic Development and Cooperation (1999). Poverty situation in Ethiopia. Welfare monitoring unit. Addis Ababa

Mulat Demeke (2001) Off-farm income generation opportunities in Ethiopia with particular reference to food insecure Woredas. Addis Ababa

Mulat Demeke , Wolday Amha, Simeon Ehui, and Tesfaye Zegeye (1995) Food Security, nutritation and Poverty allevaiation in Ethiopia: Problems and Prospects: Preoceedings of the First Annual Conference of the agricultural economics society of Ethiopia. Addis Ababa

Ravallion M and B. Bidani (1994). How robust is a poverty line: World Bank Economic Review 5:57-84

Ravallion M (1992) Poverty comparisons: A Guide to concepts and methods: Living standard measurement study working paper No. 88. The World Bank Washington D.C

Prud' homme, R (1995), The dangers of decentralization. The World Bank Research obsever 10 (August) 210-26

Sharp kay (1997) Targeting food aid in Ethiopia. Consultancy report for save the Children Fund (UK) Addis Ababa.

Subbarao K.et.al (1997) Safety net programs and goverty reduction; Lessons from cross country experience. The World Bank. Washington D.C